በአዲስ አበባ ከተማ
የስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን

# ስነ ምግባርና መልካም አስተዳደር

## (የማሰልጠኛ ሞጁል)

በኮሚሽኑ የተዘጋጀ

ሙስና ስጋት የማይሆንባት አዲስ አበባን እንፈጥራለን!

አዲስ አበባ
ጥር 2016

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

የሞጁሉ አጠቃላይ መግለጫ ---------------------------------------------------------------- 4

የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ-----------------------------------------------------------------6

**1. መልካም አስተዳደር** .......................................................................... 7

ክፍል አንድ .......................................................................... 8

1.1 የአስተዳደር ሥርዓትና መልካም አስተዳደር .......................................................................... 8

**1.1.1 የአስተዳደር ሥርዓትና መንግሥታዊ አስተዳደር ጽንሰ-ሃሳብ**.......................................... 9

**ለ. መንግሥታዊ አስተዳደር** .......................................................................... 11

**1.1.2 የመልካም አስተዳደር ጽንሰ-ሃሳብ**.......................................................................... 12

**1.2 የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ መርሆዎችና አስፈላጊነት** .......................................... 15

**1.2.1 የመልካም አስተዳደር መሰረታዊ መርሆዎች**.......................................................... 16

የመርሆዎች ቁርኝት ስዕላዊ መግለጫ...................................................21

**1.2.2 የመልካም አስተዳደር አስፈላጊነት**.......................................................................... 22

*መልካም አስተዳደር ለምን ያስፈልጋል?* .......................................................................... 22

**1.3 የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶች እና መልካም አስተዳደርን መገንባት**............................ 26

**1.3.1 የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶች**.......................................................................... 27

**3. የቢሮክራሲ ችግሮች** .......................................................................... 29

**4. ሙስናና ብልሹ አሠራር** .......................................................................... 30

**1.3.2 መልካም አስተዳደርን መገንባት**.......................................................................... 32

**1.3.3 በመልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ተዋንያን እና ሚናቸው**............................ 37

**1.3.3.1 በመልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ተዋንያን**.............................................. 37

**1.3.3.2 በመልካም አስተዳደር ግንባታ ከፍተኛ ሚና ያላቸው አካላት**.............................. 40

**1. በታችኛው እርከን ላይ ያለው የመንግስት አካል** .......................................... 40

**2. የሲቪል ማህበራትና መያዶች** .......................................................................... 43

**3. መገናኛ ብዙሃን**.......................................................................... 44

**2. ሥነ ምግባርና መልካም አስተዳደር** ........................................ 49

2.1 **የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦችና የመልካም አስተዳደር ትስስር** ........................................ 51

2.2 **የሥነ ምግባር መርሆዎችና መልካም አስተዳደር** ........................................ 58

**2.2.1 የሥነ ምግባር መርሆዎች** ........................................ 59

**2.2.2 የሥነ ምግባር መርሆዎች ማዋቀሪያ አምዶች** ........................................ 60

**2.2.3 የሥነ-ምግባር ደንብና የሥራ ሥነ-ምግባር** ........................................ 64

**2.2.4 የሥነ-ምግባር ደንቦች ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸው ጠቀሜታ** ........................................ 66

2.3 **በህዝባዊ ተቋማት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚጠቅሙ ቁልፍ ጉዳዮች** ........................................ 67

2.4 **ሥነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎች እና መልካም አስተዳደር** ........................................ 73

# የሞጁሉ አጠቃላይ መግለጫ

የበርካታ አገራት የልማት እና የዲሞክራሲ እድገት ወይም ውድቀት ዋነኛው መንስኤ የመልካም አስተዳደር ች ግ ር እንደሆነ በመታመኑ ዛሬ መልካም አስተዳደር ማስፈን የልማትና የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን መመለሻ እና እንደ አንድ የአስተዳደር መሳሪያ ተደርጎ ይወሳዳል፡፡ በአገራችንም የተጀመረውን የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን ከዳር እንዳይዳረስ ጋሬጣ በመሆን እንዲሁም ህዝባችን የልማቱ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዳይሆን እንቅፋት ከሆኑበት ችግሮች መካከል የመልካም አስተዳደር እጦት አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

ለመልካም አስተዳደር እጦት መሰረታዊ ምክንያትና የችግሮቹ መነሻ ደግሞ የስነ-ምግባር መጓደል፣ የመልካም እሴቶች መሸርሸር፣ የሞራል መዝቀጥ የሚያስከትላቸው ባህሪያትና ተግባራት ውጤት እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ስለሆነም መልካም አስተዳደር ህዝባዊ ጉዳዮችን የምንመልስበት እንዲሁም የህዝብን ሀብት የምናስተዳደርበት ዘይቤ በመሆኑ ያለ ስነ-ምግባር መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በከፍተኛ የስነ-ምግባር ደረጃ የተገነባ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ለህብረተሰቡ አገልግሎቶችን ዉጤታማ በሆነ መልኩ እና ያለ አድልዎ ይሰጣል፤ ከህብረተሰቡ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ይሰጣል፤ ለልማትና ለህዝባዊ አገልግሎት የተመደበ ሀብትና ገንዘብ ከሙስናና ምዝበራ በጠራ መንገድ በአግባቡ ጥቅም ላይ ያውላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሥነ ምግባር መጓደል የመንግስት ተማትና ሰራተኞች ለህዝብ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታቸዉን እንዳይወጡ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ስለዚህም የስነ-ምግባር መዳበር በሀገራችን መልካም አስተዳደርን ለመገንባትና ለማስፈን አንዱና ዋነኛዉ ቅድመ ሁኔታ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአገራችን የተጀመረውን ልማትና እድገት ቀጣይነት በማረጋገጥ ህዝቡን የልማትና የዲሞክራሲ ፍትሃዊ ተጠቃሚ ለማድረግ ስነ-ምግባር የተላበሰና በሙያዊ ብቃት የተካነ የመንግስት ሰራተኛና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት የመንግስት አስተዳደር መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሥነ-ምግባርና በመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብ፣ አስፈላጊነት፣ መርሆዎች እና ትግበራ ዙሪያ መሠረታዊ እውቀትና ክህሎት ያላቸው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ሙያዊ ሃላፊነታቸውን መወጣት የሚችሉ፣ ከፍተኛ የሞራል ደረጃ እና ቁርጠኝነት ያላቸው የመንግሥት ባለሥልጣናትና ሠራተኞችን ማፍራት ያስፈልጋል፡፡

ለዚህም ሲባል በቅድሚያ ስለ መልካም አስተዳደር ምንነት፣ ግንባታና አስፈላጊነት ቀጥሎም ስለ ሥነ- ምግባር ጽንሰ ሃሳብ እንዲሁም ሥነ-ምግባር ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ያለዉን አሰተዋፅኦና ትስስር ዙሪያ መሠረታዊ እውቀትና ክህሎት መገንባት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ በተለይ ለመንግሥት ሠራተኞችና የሥራ መሪዎች በስነ-ምግባርና መልካም አስተዳደር ላይ የሚያተኩር ስልጠና ለመስጠት ይህን የስነ-ምግባርና የመልካም አስተዳደር ማሰልጠኛ ሞጁል አዘጋጅቷል፡፡ ሞጁሉ ሥነ-ምግባርና መልካም አስተዳደርን የሚመለከቱ ሁለት ሰፋፊ ሀሳቦችን የያዘ ቢሆንም ሁለቱ ርዕሰ ጉዳዮች እርስ በርሳቸው ያላቸውን ቁርኝት በሚያሳይ መልኩ ቀርበዋል፡፡ ለአቀራረብ እንዲያመች ሞጁሉ በሁለት የትምህርት ምዕራፎች የቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ መልካም አስተዳደርን ሲመለከት ሁለተኛው ምዕራፍ ሥነ-ምግባርን ይመለከታል፡፡ በዚህ መሰረት የመጀመሪያው ምዕራፍ አራት ክፍሎች ይዟል፡፡ በክፍል አንድ የአስተዳደር ሥርዓት እና የመልካም አስተዳደር ጽንሰ-ሃሳብ፣ በክፍል ሁለት የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ መርሆዎችና የመልካም አስተዳደር አስፈላጊነትን የሚያሳዩ ትምህርቶች የቀረቡ ሲሆን፣ በክፍል ሶስት ደግሞ የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶች፣ መልካም አስተዳደርን መገንባት እና በመልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ተዋናዮችና ሚናቸውን የሚመለከቱ ትምህርቶች ቀርበዋል፡፡

ምእራፍ ሁለት የሥነ-ምግባርና የመልካም አስተዳደር ትስስርን የሚያስገነዝቡ አምስት የትምህርት ርእሰ ጉዳዮች አካተዋል፡፡ በክፍል አንድ የስነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦችና የ መልካም አስተዳደር ትስስር፣ በክፍል ሁለት የሥነ-ምግባር መርሆዎች አቀራረጽ እና መልካም አስተዳደር፣ በክፍል ሶስት የሥነ-ምግባር ደንቦች እና መልካም አስተዳደር፣ እዲሁም በክፍል አራት ሥነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎች እና መልካም አስተዳደር የሚሉ የትምህርት ርእሰ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ ትምህርቱ አሳታፊ እንዲሆን የመወያያ ጥያቄዎች፣ ኬዞች እና ተግባራዊ መልመጃዎች በየትምህርት ክፍሉ ቀርበዋል፡፡ በየትምህርት ክፍሉ ሥር የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችን በተሻለ መንገድ ለማቅረብ አመቻቾችን የሚያግዙዋቸው አማራጭ የአቀራረብ መንገዶች የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች እና ታሳቢ ጊዜ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡ ሞጅሉ ለማሰልጠን የተመደበለት አጠቃላይ ጊዜ አምስት (5) ቀን ነው፡፡

# የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ

የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ በመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብና ግንባታ እንደዚሁም መልካም ሥነ-ምግባር ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ያለውን ፋይዳና አስፈላጊነት በሚመለከት መሰረታዊ እውቀትና ክህሎቶችን በማስጨበጥ በመንግሥት ተቋማት ሥነ-ምግባራዊ አገልግሎት እና መልካም አስተዳደርን ለማጎልበት ነው፡፡

**ዝርዝር ዓላማዎች**

ተሳታፊዎች ይህን የስነ-ምግባርና የመልካም አስተዳደር ስልጠና ሲያጠናቅቁ፤

- ስለ አስተዳደርና መልካም አስተዳደር ፅንሰ-ሀሳብ ያብራራሉ፣
- በሀገር ደረጃ እየተካሄደ ያለውን የስነ-ምግባርና የመልካም አስተዳደር ስነ-ምህዳሮችን ይገመግማሉ፣
- የሚሰሩበትን ተቋም መልካም አስተዳደር ሁኔታ ይገመግማሉ፣
- ሥነ-ምግባር ለሀገር አስተዳደር ያለውን ፋይዳ ያስረዳሉ፣

# ምዕራፍ አንድ

# 1. መልካም አስተዳደር

## የምዕራፍ አንድ ዋና ዋና ይዘቶች

በዚህ ምዕራፍ አስተዳደር እና መልካም አስተዳደርን የሚመለከቱ አራት ዋና ዋና የትምህርት ክፍሎች ቀርበዋል፡፡ በክፍል አንድ የአስተዳደር ሥርዓት እና የመልካም አስተዳደር ጽንሰ-ሃሳብ ሲቀርብ ፣ በክፍል ሁለት የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ መርሆዎች እና የመልካም አስተዳደር አስፈላጊነትን የሚያሳዩ ትምህርቶች ቀርበዋል፣ በክፍል ሶስት ደግሞ የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶች፣ መልካም አስተዳደርን ለመገንባት ሊደረጉ የሚገቡ ጉዳዮች እና በመልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ተዋናዮችና ሚናቸውን የሚመለከቱ ትምህርቶች ቀርበዋል፡፡ ትምህርቱን ለማጠናከርና ተጨባጭ ለማድረግ ከተሳታፊዎች ልምድ ጋር የተያያዙ መልመጃዎችና ኬዞች ተካተው ቀርበዋል፡፡

## የትምህርቱ ዓላማዎች

የሥልጠናው ተሳታፊዎች ከምእራፍ አንድ ትምህርት በኋላ፡

- የመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብን ያስረዳሉ፣
- የመልካም አስተዳደርና መንግስታዊ አስተዳደር ልዩነት ያብራራሉ፣
- የመልካም አስተዳደር ባህሪያትን፣ መርሆዎች እና ለመልካም አስተዳደር መስፈን ያላቸውን አስፈላጊነት ያብራራሉ፣
- የመልካም አስተዳደር አስፈላጊነትን ያስረዳሉ፣
- የአገሪቱን እና የሚሰሩበትን ተቋም የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን አተገባበር ይመዝናሉ፣
- መልካም አስተዳደርን በማስፈን ሂደት የሚገጥሙ ተግዳሮቶችን ይለያሉ፣
- የመልካም አስተዳደር መገንቢያ መንገዶችና መወሰድ ስለሚገቡ እርምጃዎች ያብራራሉ፣
- በመልካም አስተዳደር ግንባታ ወሳኝ ሚና ያላቸውን ቁልፍ አካላት ይዘረዝራሉ፣
- የአገሪቱንና የየተቋማቸውን የመልካም አስተዳደር ሁኔታ ይገመግማ

# ክፍል አንድ

## 1.1 የአስተዳደር ሥርዓትና መልካም አስተዳደር

### የክፍለ ትምህርቱ አጭር መግለጫ

የበርካታ አገራት የልማት እና የዲሞክራሲ ችግሮች ዋነኛው መንስኤ የአስተዳደር ወይም መጥፎ አስተዳደር እንደሆነ በመታመኑ ዛሬ መልካም አስተዳደር ማስፈን የልማትና የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን መመለሻ የአስተዳደር መሳሪያ ተደርጎ ይወሳዳል፡፡ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በቅድሚያ የጽንሰ-ሃሳቡን ምንነት መረዳትና መገንዘብን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል የአስተዳደር ሥርዓት ጽንሰ-ሃሳብን የሚያስጨብጡ ትምህርቶች በሶስት ክፍለ ትምህርቶች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ በትምህርት አንድ የአስተዳደር ሥርዓት ጽንሰ-ሃሳብ የቀርበ ሲሆን፤ ትምህርት ሁለት መንግስታዊ አስተዳደር ምንነት እዲሁም ትምህርት ሶስት የመልካም አስተዳደር ጽንሰ-ሃሳብ ዙሪያ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችሉ ይዘቶች ቀርበዋል፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

የስልጠናው ተሳታፊዎች ክፍል አንድን በሚገባ ተከታትለው ሲያጠናቅቁ:

- የአስተዳደር ሥርዓትና የመንግሥታዊ አስተዳደር ምንነትን ያብራራሉ፤
- የመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብን ያስረዳሉ፤
- የመልካም አስተዳደር ለልማትና ለእድገት ያለውን አስፈላጊነት ይዘረዝራሉ፤
- መልካም አስተዳደር ለምን የትኩረት መስክ እንደሆነ ያብራራሉ፤

**መነሻ ተግባር 1.1**

**መመሪያ:** ሰልጣኞች ያላችሁን እውቀት በመጠቀም ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሰቻችሁን ለአሳታፊዉ ግለጹ፡፡

1. በእርስዎ ግንዛቤ የአስተዳደር ሥርዓትን እንዴት ይረዱታል?
2. መልካም አስተዳደርንስ እንዴት ይረዱታል?
3. ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መልካም አስተዳደር የልማትና የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን የመመለሻ የአስተዳደር መሳሪያ ተደርጎ በተደጋጋሚ ይነሳል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምን ይመስላችኃል?

## ትምህርት አንድ

## 1.1.1 የአስተዳደር ሥርዓትና መንግሥታዊ አስተዳደር ጽንሰ-ሃሳብ

### ሀ. የአስተዳደር ሥርዓትና ጽንሰ-ሃሳብ

የአስተዳደር ስርዓት አዲስ ጽንሰ ሃሳብ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ መንግሥት በኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያለው የቁጥጥርና የመወሰን አቅምና ሚና ከመጨመር ጋር በተያያዘ ለአስተዳደር ሥርዓት ትኩረት እንዲሰጥ አስገድዷል፡፡ በመሆኑም ከ1980ዎቹ ወዲህ የአስተዳደር ሥርዓት እና መልካም አስተዳደር ከልማትና ከዲሞክራሲ እድገት ጋር በተያያዘ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኝ ጽንሰ ሃሳብ ነዉ፡፡ በመሆኑም እንደሌሎች የማኅበራዊ ሳይንስ ጽንሰ ሀሳቦች ሁሉ ለአስተዳደር አንድና ወጥ የሆነ ትርጓሜና መገለጫ ማግኘት ቢያስቸግርም፤ አስተዳደራዊ ሥርዓት በዋናነት የሥልጣን አጠቃቀምን፣ ግንኙነትና ተጠያቂነትን የሚመለከት ሲሆን፤ ተጽእኖ መፍጠር የሚችለው ማነው? ወሳኔ የሚወስነው ማነው? አወሳሰኑስ እንዴት ነው? የሚሉ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው:: የአስተዳደር ስርዓት ጥቅል ትርጓሜዉም “በዋናነት የአንድን ሃገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሃብቶች መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ ተቋማት የሚያስተዳድርበት፣ የዜጎች ወይም የቡድኖች ፍላጎትና ህጋዊ መብቶቻቸው የሚገልፅበትና ግዴታቸውን የሚወጡበት እንዲሁም የተለያዩ ሃሳቦቻቸውንና ፍላጎታቸውን በማቻቻልና በማስታረቅ ለጋራ ጥቅም የሚሠሩበት የአሰራርና የአመራር ሥርዓት ሂደት እና ተቋማትን የሚይዝ ነው”፡፡

በተጨማሪም የተለያዩ ሙሁራንና አለማአቀፍ ተቋማት ለአስተዳደር ተቀራራቢ ጽንሰ ሃሳባዊ ትርጓሜ ይሰጣሉ፡፡ ከነዚህም ዉስጥ የሚከተሉት የአስተዳደር ስርዓት ትርጓሜዎችና መገለጫዎች በወናነት የሚጠቀሱት ናቸዉ፡፡

- “የአስተዳዳር ሥርዓት በአንድ መንግሥታዊ ሥርዓት ውስጥ ባሉ የተለያዩ መዋቅሮች፣ ተቋማት፣ አሰራሮች ያላቸውን ትስስርና ከዜጎች ጋር ያላቸውን ግንኑነት የሚመለከት ሲሆን፣ የስልጣን አጠቃቀምና አተገባበርን፣ የውሳኔ አሰጣጥና የዜጎች

የተሳትፎ ደረጃን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚያጠቃልል ጽንሰ ሃሳብ ነው"፡፡ (የተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራም-UNDP፣ 1997)፡፡

- የዓለም ባንክ (2003)፣ የአስተዳደር ሥርዓትን "የአገርን ኢኮኖሚና ማህበራዊ ሃብት ለልማት ለማዋል ሀብት የማስተዳደር የስልጣን አጠቃቀም የሚተገበርበት አካሄድ ወይም ሥርኣት ነው" በማለት ይገልፃል፡፡
- "የአስተዳደር ስርዓት ፖለቲካዊ እና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች የሚመሩበት መዋቅርና ስልት ሲሆን የህዝብ ጉዳይን የማስተዳደርና የመምራት ተግባራት ወይም ሂደት ነው:: ይህም ከመንግሥት አስተዳደር የተለየ የአሰተዳደር ጥራትና የተገቢነት ደረጃን የሚመለከት ነው" (Wehmber፣ 2000)፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው ትርጓሚዎች እንደሚያሳዩት የአስተዳደር ስርዓት የስልጣን አጠቃቀም፣ግንኙነትና የውሳኔዎች ተግባራዊነት የሚረጋገጥበት ሂደት በመሆኑ በተለያዩ ደረጃዎች ማለትም በሀገር ደረጃ እስከ አካባቢያዊ፣ ማህበረሰብ ወይም በቤተሰብ ደረጃ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ለምሳሌ የኮርፖሬት አስተዳደር ስርዓት፣ ዓለም አቀፍ የአስተዳደር ስርዓት፣ (መንግሥታት በሚመሰርቷቸው ግንኙነት፣ ተቋማት)፣ ብሄራዊ የአስተዳደር ስርዓት፣ የአካባቢ አስተዳደር ስርዓት፣ ክልላዊ፣ የቀበሌ አስተዳደር ስርዓት፣የሲቪክ ማህበራት ወዘተ ይገለጻል ወይም ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይ የአስተዳደር ስርዓት በብሄራዊ፣ በክልላዊና በአከባቢያዊ ደረጃ ውሳኔ የመስጠት ሂደት ሲሆን ባለድርሻ አካላት የውሳኔዎችን መተግበር ወይም አለመተግበር የሚከታተሉበት ሂደትም ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል (የአፍሪካ ህብረት፣ 2008)፡፡

አስተዳደር ከመንግሥት በተለየና ራሱን የቻለ ጽንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ መንግሥት ራሱን እንደቻለ ተቋም አንድ የአስተዳደር ሥርዓት ተዋናይ የሚታይ ነው፡፡ የአስተዳድር ሥርዓት መንግሥታትና ሌሎች ማህበራዊ ድርጅቶች ከዜጎች ጋር እንዴት እንደሚገናኙና ውሳኔዎች እንዴት እንደሚወሰኑ የሚገልጽ ጽንሰ ሃሳብ ሲሆን የመንግስት ቢሮክራሲ እያደገ የመጣውን የዜጎች ፍላጎት በብቃት መመለስ ባለመቻሉ የህዝብ አገልግሎቶች ቅልጥፍና እንዲጨምር ከመንግሥት አስተዳደር በተለየ እያደገ የመጣ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡

የአስተዳደር ሥርዓትን ለመረዳት የህዝባዊ ጉዳዮች ፍላጎትና አገልግሎት በመንግስት ብቻ የተገደበ፣የሚመለስና የሚስተናገድ አለመሆኑን መገንዘብ ይጠይቃል። ሌሎች ተዋናዮች ማለትም መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣መገናኛ ብዙሃን፣የሲቪክ ማህበራት፣ የሃማኖትና ባህላዊ ተቋማት የህዝብ ጉዳዮችን እና ፍላጎቶች መመለስ ላይ ወሳኝ ሚና አላቸው። በመሆኑም አስተዳደር ሥርዓት የውሳኔ አሰጣጡ ሂደትና ውሳኔዎች የሚተገበሩበት ሂደት ሰለሆነ፣የአስተዳደር ትንተና የሚያተኩረው በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ በተሳተፉ መደበኛና ኢ-መደበኛ በሆኑ ባለ ድርሻ አካላት ላይ ነው። በዚህም መሰረት መንግስት በአስተዳደር ውስጥ ካሉ ተዋናዮች አንዱ ነው።

## ለ. *መንግሥታዊ አስተዳደር*

*ከላይ በቀርበዉ የአስተዳደር ሥርዓት ጽንሰ ሃሳብን መሰርት በማድርግ መንግሥታዊ አስተዳደር ማለት መንግስት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞች በውጤታማነት ተግባራዊ በማድረግ ህዝቡን የሚያገለግልበት፤ እንዲሁም መንግስታዊ አደረጃጀቶችና አሰራሮች፣ ህጐች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች የሚተላለፉበትና ተግባራዊ የሚደረግበት ሥርዓት ነው። መንግሥታዊ አስተዳደር በዋናነት የአንድ ሀገር መንግሥት የአገሪቱን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሃብቶችን የሚያስተዳድርበት፣ የዜጎችን አጠቃላይ ሠላም፣ ደህንነትና ብልጽግና የሚያረጋግጥበት አሰራር ነው።*

*በዚሁ መሰረት መንግስታዊ አስተዳደር በህግ አውጪው፣ በህግ ተርጓሚው፣ በህግ አስፈጻሚው ወይም በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና በመንግሥት ሠራተኖች የሚፈፀም ይሆናል። መንግሥታዊ አስተዳደር መልካም ወይም መልካም ያልሆነ አስተዳደር ሊሆን ይችላል። የመንግሥት አስተዳደር መልካም የሚሆነው የህዝብ ፍላጎት፣ ጥቅምና ደህንነት ማስቀደምና መጠበቅ ሲችል ሲሆን አስተዳደሩ ውጤታማነትን፣አሳታፊነት፣ተጠያቂነት፣የህግ የበላይነት በማክበር እና ሙስናን በመቆጣጠር ራሱን መግለጽ ሲችል ነው። በሌላ በኩል የመንግስታዊ አስተዳደር ከዚህ በታች ከቀርበዉ የመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብ ጋር ቀጥተኛ ተያኙነት ያለዉ ሲሆን እደሚከተለው ቀርቧል።*

**መልመጃ 1.1**

**መመሪያ:** አሳታፊው በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በአነስተኛ ቡድን በመሆን በሚከቱሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለተሳታፊዎች ግለጹ።

1. የአስተዳደራዊ ሥርዓት ጽንሰ ሃሳብን እንዴት ተገነዘባችሁት?
2. መንግሥታዊ አስተዳደርስ ምንድን ነው?
3. አስተዳደራዊ ሥርዓት ከመንግሥታዊ አስተዳደር ይለያል እንዴት?

## ትምህርት ሁለት

### 1.1.2 የመልካም አስተዳደር ጽንሰ-ሃሳብ

**መነሻ ተግባር 1.2**

**መመሪያ:** ሰልጣኞች ያላችሁን እውቀት በመጠቀም ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶቻችሁን ለአሳታፊዉ ግለጹ።

1. መልካም አስተዳደር በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የፖለቲካ አጀንዳ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ የሚዉል ቃል ነው። ለመሆኑ መልካም አስተዳደር ምንድንነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. መልካም ካልሆነ ወይም ከብልሹ አስተዳደርስ በምን ይለያል?

የ"መልካም" አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ የታወቀዉ እ.ኤ.አ. በ1989 ሲሆን የዓለም ባንክ “Sub-Saharan Africa-from Crisis to Sustainable Growth” በሚል ርዕስ ባካሄደው ጥናት ላይ ነዉ። የዚህ ጥናት ሪፖርት የአፍሪካ የልማት ችግሮች ዋነኛው መንስኤ የአፍሪካ መንግሥታት መጥፎ አስተዳደር በመሆኑ መልካም አስተዳደርን ማስፈን እንደሚያስፈልግ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል። ከዚህ ሪፖርት በኋላ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ውስጥ መልካም አስተዳደርን፣ ዲሞክራሲንና ልማትን ማስረፅና መገንባት በተለያዩ መንግስታዊና ክልላዊ በሆኑ ተቋማት ትኩረት አግኝቷል።

በሌላ በኩል መልካም አስተዳደር ልማትንና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ እንደ አንድ አማራጭ የህዝብ አመራር መሳሪያ ተደረጎም ይወሰዳል። መልካም አስተዳደር ከ1990ዎቹ ቀደም ሲል የነበሩ የህዝብ አመራር ዘይቤዎች (Traditional bureacratic public management) በዋናነት የመንግስት አፈጻጸም ውጤታማና ቀልጣፋ ከማድረግና ሙስናና ቢሮክራሲያዊ የአሰራር ችግሮችን ከመፍታት አንጻር ክፍተት የሚታይባቸው በመሆኑ ይህን ክፍተት ለመድፈን

የመንግስት ተቋማትና የህዝብ አገልግሎቶቹን ቅልጥፍና እንዲጨምር፣ የመንግስት አመራር የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን የመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሀሳብ እንደ አንድ የፐብሊክ አመራር አማራጭ ብቅ ማለቱንና በአሁኑ ወቅት በሁሉም የአለም አገራት ዘንድ ልማትን ለማረጋገጥ ትኩረት ያገኘ የአመራር ሥርዓት እንደሆነ ብዙዎች ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ለመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብ ጎልቶ መውጣትና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለኢኮኖሚያዊ ልማትና እድገት ትኩረት ማግኘት በአገራት መንግሥታዊ አስተዳደር ውስጥ ለዲሞክራሲ፣ ለልማትና እድገት እንቅፋት የሆኑ ተግባራት የሙስና መስፋፋት፣ ተጠያቂነት የጎደላቸው መንግስታት መበራከት እና የዲሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ጥሰት እየተስፋፋ እና አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱ ምክንያት መሆኑን የተለያዩ ጽሑፎች ይገልጻሉ፡፡

ስለ መልካም አስተዳደር ምንነት አንድና ወጥ ትርጉም ማግኘት ያስቸግራል፡፡ መልካም የሚለው ቃል የተወሰነ መለኪያ የሌለው በመሆኑ መልካም አስተዳደርን ከመተርጎም መገለጫ ባህሪያቱን ማሳየት የተሻለ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ በዚህ መሰረት የተለያዩ ጸሐፊዎችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ለመልካም አስተዳዳር ተመሳሳይና ተቀራራቢ መገለጫዎችና ትርጉም ሰጥተዋል፡፡

- የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም UNDP (1997 እ.ኤ.አ) መልካም አስተዳደር የአንድን አገር ጉዳዮች አሳታፊ፣ ግልጽ፣ ተጠያቂነት ያለበት፣ ውጤታማ እና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለማስተዳደር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ስልጣንን መጠቀም እንደሆነ ይገልጻል፡፡
- እንደ የአለም ባንክ (2008) አገላለፅ ደግሞ የመልካም አስተዳደር ትርጉም ግልፅነትና ተጠያቂነትን፣ ቅልጥፍናንና ውጤታማነትን፤ የህግ የበላይነትንና መንግስታት ከህዝባቸው ጋር የሚኖራቸው መልካም የፖለቲካ ግንኙነትን እንደ ዋነኛ የመልካም አስተዳደር መገለጫ አድርጎ ይወስዳል፡፡
- እንደ USAID (2005) ገለፃ መልካም አስተዳደር መንግስት ወጭ ቆጣቢ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት ያለው የህዝብ አስተዳደርን የመፍጠር አቅም እና ተግባርን የሚመለከት ሲሆን መገለጫዉም ግልፀኝነት፣ ብዝሃነት፣ የዜጎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ መሳተፍ፣ ዉክልናና ተጠያቂነት እንደሆኑ ያስረዳል፡፡

- የአውሮፓ ህብረትና ኤሲፒ ቡድን (EU & ACP Group) መልካም አስተዳደር ሰብአዊ መብትን፣ ዴሞክራሲያዊ መርሆዎችና የህግ የበላይነት የሚያከብር ፖለቲካዊና ተቋማዊ ሁኔታዎች ባለበት ሁኔታ ለአስተማማኝና ዘላቂ ልማት የሰዉ ሀበት፣ የተፈጥሮ እና የገንዘብ ሀብቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ ማስተዳደር ነው በማለት ሲያብራሩ። በተለይም ግልጽ የሆኑ የውሳኔ አሰጣጥ አካሄዶችን፤ ተጠያቂነት ያላቸውን ተቋማት ሀብትን በማስተዳደርና በማሰራጨት ዙሪያ ያለ የህግ የበላይነትና ሙስናን ለመከላከል የሚወሰድ እርምጃዎችንና የአቅም ግንባታን የሚያካትት እንደሆነ ይገለጻሉ።
- እንዲሁም የአፍሪካ ልማት ባንክ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣ የመንግስት ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ለህዝብ ግልጽ ማድረግ፣ ሙስናን በጽናት መዋጋት ፣ በየደረጃው የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥና ግልጽና በሁሉም አካባቢ ዜጎች ላይ በወጥነት የሚተገበሩ ህጋዊና ፍትሃዊ አሰራሮችን መዘርጋት መልካም አስተዳደር የሚገለጽባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መሆናቸውን አስቀምጧል።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች ለመረዳት እንደሚቻለው መልካም አስተዳደር የአገር ሀብት በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚመራበት፣ የህዝብ ጥቅምና ፍላጎት የሚከበርበት የህዝቦች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚረጋገጠበት፣ ለህዝብ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ የሚሰጥበት፣ የህግ የበላነትና ተጠያቂነት የሚሰፍንበት፣ አሳታፊና ሙስናን መቆጣጠር የሚያስችል አስተዳደራዊ ሥርዓት ማለት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

## የክፍል አንድ ማጠቃለያ

በክፍል አንድ በትምህርት አንድ እንደተመለከትነው መልካም አስተዳደርን ለመገንባት በቅድሚያ የአስተዳደርና አስተዳደር ሥርዓት እና ስለ መልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብ በቂ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል ። በመሆኑም በክፍል አንድ የአስተዳደር ስርዓት የስልጣን አጠቃቀም፣ ግንኙነትና ተግባራዊነት የሚረጋገጥበት ሂደት ሲሆን በተለያዩ ደረጃዎች ማለትም በሀገር፣ በአካባቢያዊ፣ በተቋም፣ ማህበረሰብ ወይም በቤተሰብ ደረጃ ሊገለጽ ይችላል። አስተዳደር ሥርዓት የውሳኔ አሰጣጡ ሂደትና ውሳኔዎች የሚተገበሩበት ሂደት ስለሆነ፣ መንግሥት በአስተዳደር ውስጥ ካሉ ተዋኒያን አንዱ ነው። በመሆኑም አስተዳደር ሥርዓት ከመንግስታዊ አስተዳደር የተለየ እንደሆነ ተመልክትናል።

መንግሥታዊ አስተዳደር መንግስት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች እና ኘሮግራሞች በውጤታማነት ተግባራዊ በማድረግ ህዝቡን የሚያገለግልበት፤ እንዲሁም መንግስታዊ አደረጃጀቶችና አሰራሮች፣ ህጐች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች የሚተላለፉበትና ተግባራዊ የሚደረጉበት ሥርዓት ነው፡፡ መንግሥታዊ አስተዳደር የአንድ ሀገር መንግሥት የአገሪቱን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሃብቶችን የሚያስተዳድርበት፣ የዜጎችን አጠቃላይ ሠላም፣ ደህንነትና ብልጽግና የሚያረጋግጥበት አሰራር ነው፡፡ የመንግሥታዊ አስተዳደር መልካም ወይም መልካም ያልሆነ አስተዳደር ሊሆን ይችላል፡፡

መልካም አስተዳደደር የህዝብ ጥቅምና ፍላጎት የሚገለጽበት፣ የህዝቦች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተረጋገጠበት፣ ለህዝብ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ የሚሰጥበት፣ የህግ የበላይነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን እና አሳታፊ አስተዳደራዊ ሥርዓት ማለት እንደሆነ በክፍል አንድ ተመልክተናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## 1.2 የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ መርሆዎችና አስፈላጊነት

**የክፍለ ትምህርቱ አጭር መግለጫ**

በክፍል አንድ የአስተዳደር ሥርዓትና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ጽንሰ ሃሳብን ተመልክተናል:: በዚህ ክፍል ደግሞ በትምህርት አንድ የመልካም አስተዳደር መሰረታዊ ባህሪያትን እንዲሁም በትምህርት ሁለት የመልካም አስተዳደር አስፈላጊነትን የሚመለከቱ ትምህርቶች ቀርበዋል፡፡

**የትምህርቱ ዓለማዎች**

ተሳታፊዎች ይህን ክፍለ ትምህርት ሲያጠናቅቁ፡

- የመልካም አስተዳደር ባህሪያትንና መርሆዎች ይዘረዝራሉ፣
- የመልካም አስተዳደር መርሆዎች ለመልካም አስተዳደር መስፈን ያላቸውን አስፈላጊነት ያብራራሉ፣
- የአገሪቷን እና የሚሰሩበትን ተቋም የመልካም አስተዳደር መርሆዎች አተገባበር ይመዝናሉ፣

## መነሻ ተግባር 2.1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አሳታፊው በሚሰጣችሁ መመሪያ መሰረት ያላችሁን ልምድና እውቀት በመጠቀም መልሱ።

1. በልምድ ከምታዉቁት በመነሳት የመልካም አስተዳደር መገለጫ ባህሪያት ምንድን ናቸው? በምሳሌ አስረዱ።
2. መልካም አስተዳደር ለምን ያስፈልጋል ትላላችሁ?

## ትምህርት አንድ

### 1.2.1 የመልካም አስተዳደር መሰረታዊ መርሆዎች

*የተለያዩ የልማትና የፋይናንስ ዓለም አቀፍ ተቋማት ከራሳቸው እይታ አንጻር የመልካም አስተዳደር መገለጫ ባህሪያትን ወይም መርሆዎችን ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ ስምንት መሠረታዊ የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች ወይም መርሆዎች ይጠቀሳሉ። ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር እንደ መልካም አስተዳደር መርሆዎች ተወስደው ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉት የሚከተሉት ናቸዉ። የህግ የበላይነት፣ ተሳትፎ ፣ የጋራ መግባባት፣ ፈጣን ምላሽ መስጠት፣ ግልፀኝነት፣ ተጠያቂነት ፣ ፍትሃዊነት እንዲሁም ቀልጣፋነትና ውጤታማነት ናቸው። መርሆዎቹም እርስ በርሳቸው የተቆራኙና አንዱ ያለአንዱ ትርጉም የማይኖራቸው መሰረተ ሀሳቦች ናቸው።*

### 1. *አሳታፊነት* (Participatory)

*መልካም አስተዳደር ከሚገለጽባቸው ባህሪያት መካከል አንዱ የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ ነው። መልካም አስተዳደር የሲቪል ማህበረሰቡ ፣ የተለያዩ ቡድኖች እና መላው ህብረተሰብ በአገር ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ የሚችሉበት ልምድና አሰራር እንዲኖር ይጠይቃል:: ህዝብ መንግሥት በሚቀርባቸው ፖሊሲዎች ፣ የልማትና ማህበራዊ ፕሮግራሞች ፣ በአካባቢያቸው ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል። የህዝብ ተሳትፎ የሌለበት የልማት ሥራ ውጤታማ አይሆንም። ተሳትፎው በቀጥታ ወይም ፍላጎታቸውን በሚወክሉ አካላት ሊሆን ይችላል። ህዝብ መንግሥታዊ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ተቋማት አሰራር ላይ አስተያየት የሚሰጥበት ፣ ዕቅድና አፈፃፀምን የሚገመግምበት እና በሁሉም የአመራር ሂደቶች በባለቤትነት ተሳትፎ የሚያደርግበት አሰራር የመልካም አስተዳደር መገለጫ ባህሪይ ነው። ይህ*

የመልካም አስተዳድር ገጽታ ለመንግሥት የልማትና ማህበራዊ እቅዶች ተግባራዊነት እና የአፈፃፀም ጥራት ለማሻሻል ወሳኝ ሚና ይጫወታል::

## 2. የህግ የበላይነት (The Rule of Law)

የህግ የበላይነት ዜጎች ያለ ምንም አድሎና ልዩነት በህግ ፊት እኩል የሚዳኙበት ፣ መብቶችና ጥቅሞቻቸው በእኩል የሚጠበቅበት ሥርዓት መሠረት የሆነ መርህ ነው፡፡ መልካም አስተዳደር ሁሉም ዜጎች በህግ ፊት እኩል የሚዳኙበት እና የህግ የበላይነት መከበር የሚያረጋግጥበት የአስተዳደር ሥርዓት ነው፡፡ የመልካም አስተዳደር የሕግ ማዕቀፎች ፍትሃዊ መሆን ብቻ ሣይሆን የሰብአዊ መብት ህጎችና ሌሎች ህጎች ያለ አድሎና በተገቢው መንገድ መከበርን እንዲሁም ህጋዊ ግዴታቸውን የማይወጡ አካላት የሚጠየቁበት ህጋዊ አሰራር እውን መሆንን የሚጠይቅ ሥርዓት ነው፡፡ በመሆኑም የህግ የበላይነት የመልካም አስተዳደር መርህና ዋነኛ መገለጫ ባህሪው ነው፡፡

የህግ የበላይነት መከበር ሁሉም ዜጋ በህግ ፊት እኩል መሰተናገድን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የመንግሥት አገልግሎት በቅድሚያ ተለይተው በሚታወቁ የህግ ማእቀፎች በህግ አግባብ መሰጠትንም የሚመለክት ነው፡፡ በመሆኑም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ በቅድሚያ ተለይተው በሚታወቁ ህግና ደንብ ወጥና ፍህታዊ በሆነ መንገድ ለዜጎች ሁሉ መሰጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም አድሏዊ አሰራርና ሙስና እንዳይፈጸም ያግዛል፡፡

## 3. ግልጽነት (Transparency)

ግልፅነት የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ መገለጫ መርህ ነው፡፡ ግልጽነት የመንግሥት አሰራርና ውሳኔዎች ለህብረተሰቡ ግልጽ የሚሆንበት ፣ ህዝብም ስለመንግሥት አሰራር የሚያውቅበት እና ቁጥጥር የሚያደርግበት አሰራርን የሚመለከት መርህ ነው፡፡ በመንግስት አሰራር ውስጥ ግልጽነት የመንግሥት አገልግሎት የሚመራበትን ህግና ደንብ ፣ እንዲሁም መንግሥት ለልማትና ለህዝብ አገልግሎት የሚመድበውን በጀትና የበጀት አጠቃቀም የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎች ለህዝብ ግልጽ ማድረግን ያካትታል፡፡ መልካም አስተዳደር ደግሞ ዜጎች የመንግሥት አሰራርና ውሳኔዎች ግልጽ የሚሆንበትና ህዝብም ስለመንግሥት አሰራር የማወቅና መረጃ የማግኘት መብት የሚከበርበት አሰራር መኖርን ይጠይቃል፡፡

ሕዝቡ በመንግስት አሰራርና ውሣኔዎች ላይ በብቃት መሳተፍ እና መቆጣጠር እንዲችል መንግሥት ለልማትና ለህዝብ አገልግሎት ስለሚመደቡ በጀትና አጠቃቀም ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ በግልጽነት የአሰራር ስርአት ህብረተሰቡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻለ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ የአስተዳደር በደል ፣ ብልሹ አሰራር፣ ሙስናና የሀብት ብክነትን ለመቀነስ ያስችላል::

## 4. ተጠያቂነት (Accountability)

ሌላው የመልካም አስተዳደር ሥርዓት መለያ ባህሪይ የተጠያቂነት ሥርዓት መኖር ነው፡፡ ተጠያቂነት በተሰጠ ህዝባዊና መንግስታዊ ሃላፊነት ላከናወኑት ተግባር፣ለወሰኑት ውሳኔና ለተገኘ ውጤት በጋራና በግል ሃላፊነት መወሰድና ተጠያቂ መሆንን የሚመለከት ነው፡፡

የተጠያቂነት መርህ መንግሥት፣ የመንግሥት ባለሥልጣናት እና ሠራተኞች የተሰጣቸውን ተግባርና ሃላፊነት በአግባቡ ባልተወጡ ጊዜ ተጠያቂ የሚሆኑበት፣ ላከናወኑት ተግባር ፣ ለሚወስዷቸው እርምጃዎች እና ውሳኔዎች ሃላፊነት የሚወስዱበት እና ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት ነው፡፡ ተጠያቂነቱ ከፖለቲካ፣ ከሕግ፣ ከገንዘብ፣ ከአስተዳደር ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጠያቂነት ሥርዓት መንግሥትና የመንግሥት አካላት ብቻ ሳይሆኑ የሲቪክ ማህበራትና የግሉ ሴክተርም የሚያከናውኑዋቸው ተግባራት፤ የሚወስዱት እርምጃዎች የሚያገኙት ውጤት ተጠያቂነትን ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

**መልመጃ 2.1**

**መመሪያ፡** አጠገባችሁ ከተቀመጡ ተሳታፊዎች ጋር በመነጋገር የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. የህዝብ ተሳትፎ ምንድን ነው? እንዴት ይገለጻል ? በምሳሌ አስረዱ
2. በመንግሥት አስተዳደር ዉስጥ ተሳትፎ ምን ያህል ዋጋ አለው? በምሳሌ አሳዩ
3. የህግ የበላይነት ምንድን ነው? የህግ የበላይነት እንዴት ሊከበር ይችላል?
4. በመንግስት አስተዳደር ውስጥ የህግ የበላይነት ካልተጠበቀ ምን ይሆናል?
5. “ግልጽነትና ተጠያቂነት” ማለት ምን ማለት ነው? መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር ምን ፋይዳ አላቸው?
6. ግልጽነትና ተጠያቂነት ሙስናን ለመከላከል ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?

## 5. ምላሽ ሰጪነት (Responsiveness)

ምላሽ ሰጪነት ተገቢ፣ ወቅታዊና ፈጣን አገልግሎት መስጠትን ፣ ዜጎች ለሚያነሷቸው የልማት ጥያቄዎች እንዲሁም በመንግሥት ተቋማት አሰራርና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ፣ ነቀፌታዎችና አስተያየቶችን መቀበልና ተገቢውን መልስ መስጠትን የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም መልካም አስተዳደር ከሚገለጽባቸው መካከል ዜጎች ከመንግሥት ተቋማት ለሚፈልጓቸው አገልግሎቶች እና ለሚያቀርቧቸው ቅሬታዎች ፈጣንና ተገቢ ምላሽ መስጠት መቻል አንዱ ነው፡፡

በመንግስት አሰራርና አገልግሎቶች ዙሪያ ከህዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚገባ ነው፡፡ ለዚህም ህዝብ ቅሬታዎቹንና ጥያቄዎቹን የሚያቀርብበትና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያግዙ አስፈላጊ የሆኑ አሰራሮችን መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ በኩል መልካም አስተዳደር ለህዝብ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ የመንግሥት ተቋማት ፈጣን አገልግሎት የሚሰጡበት፣ በአሰራራቸው ላይ ተገልጋዮች ቅሬታና አስተያየት የሚሰጡበት ሥርዓት በመዘርጋት ፈጣን ምላሽ የሚሰጥበት ሥርዓት ነው፡፡

## 6. ስምምነት ተኮር (Consensus Oriented)

መልካም አስተዳደር የተለያዩ ፍላጎቶችና አመለካከቶች የሚሰተናገዱበት፣ የተለያዩ ፍላጎቶችን በማጣጣም አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ በዜጎች መካከል የጋራ ስምምነት መፍጠር የሚያስችል አሰራር ላይ የሚመሰረት ሥርዓት ነው፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚከናወኑ ማንኛውም ተግባራት የጋራ ስምምነትና መግባባት ያገኘ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህም ለአንድ ዓላማና ግብ በጋራ መንቀሳቀስና ውጤት ለማምጣት ያስችላል፡፡ መልካም አስተዳደር የተለያዩ ፍላጎቶችና አመለካከቶች በሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ በማስተናገድ የጋራና መሰረታዊ በሆኑ በልማት፣ በሀገር ደህንነትና መሰል ጉዳዮች በህዝቦች መካከል የጋራ መግባባት መፍጠር መርህን መሰረት ያደረገ ሥርዓት ነው፡፡

## 7. ፍትሃዊነትና አካታችነት (Equity and Inclusiveness)

ፍትሃዊነትና ሁሉን አቀፍ መርህ የመልካም አስተዳደር ዋነኛ መገለጫ ነው፡፡ ፍትሃዊነት ዜጎችን በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በዘርና በጎሳ፣ በፖለቲካ አመለካከት እና ባላቸው ማህበራዊ ቦታ ልዩነት ሳይደረግ የሀገርን ሀብትና ንብረት በእኩል ተጠቃሚ የማድረግ መርህ ነው፡፡ ፍትሃዊነት ዜጎች በመንግሥታዊ አገልግሎቶች ያለአድልዎና ልዩነት እንዲገለገሉ፣ እንዲስተናገዱና ጥያቄና ቅሬታቸው በህግ አግባብ ምላሽ የሚያገኙበት አሰራር ነው፡፡ መልካም አስተዳደር ለድሃ፣ ለወጣት ወይም በእድሜ ለገፉ አረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞች ጥቂት ቁጥር ላላቸዉ ጎሳዎች እና የህብረተሰብ ክፍሎች እኩልና የተመጣጠነ የትምህርት፣ የጤና፣ የሥራ፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ ምቹ የመኖሪያ አካባቢና ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶች እኩል ተጠቃሚ በማድረግ የሚታወቅ ሥርዓት ነው፡፡

የፍትሃዊነት መጓድል በዜጎች መካከል አድሎና ልዩነት ስለሚፈጥር ለሙስናና ብልሹ አሰራር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ይህም በዜጐች ዘንድ ቅሬታን በመፍጠር፣ የመንግሥትን አመኔታ ያሳጣል፣ ህዝባዊ አመጽን ያስከትላል ፤ ሠላምን ያሳጣል፡፡ ስለዚህ መንግሥታዊ አሰራር ያለ አድልዎ በፍትሃዊነት ሊፈፀም ይገባዋል፡፡ ለዚህም መልካም አስተዳደርን መገንባት የግድ ያስፈልጋል፡፡

## 8. ውጤታማነት እና ቅልጥፍና (Effectiveness and Efficiency)

ቀልጣፋና ውጤታማ ህዝባዊ አገልግሎት ለህብረተሰቡ መስጠት የመልካም አስተዳደር አንዱ መርሆ ነው፡፡ ቅልጥፍናና ውጤታማነት የአገር ሀብትና ገንዘብን ከብክነት በጸዳ መልኩ በመጠቀም በአጭር ጊዜ የሀገርና የህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ለሟሟላት የሚበጁ ተግባራትን በብቃት መፈጸምን እና የህዝብን ተጠቃሚነት ማረጋገጥን የሚመለከት መርህ ነው፡፡

መንግሥት ለዜጎች ህግና ደንቦችን ከማውጣት ባሻገር ጥራት ያለው ፈጣን አገልጎቶችን የማቅረብ ሃላፊነት አለበት፡፡ ህዝብም ፈጣን ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡ ይህን የህዝብ መብት ለማስጠበቅ ፈጣን ፣ ቀልጠፋና ውጤታማ አገልግሎት ለህዝብ መስጠት መቻል ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም መልካም አስተዳዳርን ማጎልበት ግድ ይላል፡፡ መልካም አስተዳደር ውስን የሆነዉን የሰዉና የፋይናንስ ሀብት በተገቢ መልኩ ጥቅም ላይ በማዋል ፣ ከሀብት ብክነት እና ከሙስና የፀዳ ፈጣን ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ አገልግሎት

መስጠት መለያ ባህሪው ነዉ። በመሆኑም መልካም አስተዳደር የአገርን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም የህብረተሰቡን ፍላጎት ለሟሟላት የሚያስችል ውጤታማ ተቋማዊ አሰራር መኖር ማለት ነው።

# የመርሆዎች ቁርኝት ስዕላዊ መግለጫ




**መልመጃ 2.2**

**መመሪያ፡ በሚከተሉት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩና መልሳችሁን አቅርቡ።**

1. ፍትሃዊነትና ሁሉን አቀፍ መርህ የመልካም አስተዳደር ዋነኛ መገለጫ ነው የሚባለው ለምንድን ነው?
2. የውጤታማነት እና ቅልጥፍና መርህ መልካም አሰተዳደርን በመገንባት ለዘላቂ ልማትና ለድህነት ቅነሳ ያለዉ አሰተዋፅኦ ምንድን ነው ትላላችሁ?
3. እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መገኛ በሆኑ ሀገራት የፍትሀዊነት

እና ሁሉን አቀፍ መርህ አስፈላጊነትን እንዴት ትገነዘባላችሁ?

4. በተቋማችሁ ለህዝብ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር አለ? እንዴት ይገለጻል?
5. በአገራችን ወይም በምትሰሩበት ተቋም የመልካም አስተዳደር መርሆዎች ተግባራዊነት ደረጃ ምን ያህል ነው? ለህዝብ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር አለ? እንዴት ይገለጻል?
6. በእናንተ አመለካከት በአገራችን መልካም አስተዳደርን እውን ለማድረግ ካላቸው አስፈላጊነት ደረጃ አንጻር ከላይ የተዘረዘሩትን የመልካም አስተዳደር መርሆዎች በቅደም ተከተል አስቀምጡና ምክንያታችሁን ግለጹ?

## ትምህርት ሁለት

## 1.2.2 የመልካም አስተዳደር አስፈላጊነት

***መልካም አስተዳደር ለምን ያስፈልጋል?***

*የመልካም አስተዳደር ስርዓት መስፈን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ ጥናታዊ ፅሑፎች ይገልጻሉ። መልካም አስተዳደር መልካም አመራርን፣ መልካም አፈጻጸምን፣ መልካም ኢንቨስትመንትን፣ መልካም የሥራ ባህርይን እና መልካም ውጤትን ያመጣል። የመልካም አስተዳደር መስፈን የስልጣን ምንጭና ባለቤት የሆነው ህዝብ በመንግሥትና በተወካዮቹ ላይ እምነት እንዲኖረው ያደርጋል፤ በመንግስት በሚተላለፉ ውሳኔዎች ላይ እምነት እንዲጥልና ለተግባራዊነቱም እንዲረባረብ በማድረግ ውጤታማ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ስኬቶችን ማረጋገጥ ያስችላል። ስለ መልካም አስተዳደር አስፈላጊነት የሚከተሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።*

**1. ህዝብ/ዜጎች በመንግስት ላይ ያላቸውን እምነት ይጨምራል**

*መልካም አስተዳደር በሰፈነበት ሥርዓት ውሳኔዎች ግልጽ በሆነና ተጠያቂነት ባለበት መንገድ የሚካሄዱ በመሆናቸው ህዝቡ እያንዳንዱ የመንግሥት ውሳኔዎች በማህበረሰቡ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እንዲሰማቸዉ ያደርጋል። ይህም ዜጎች በአካባቢያቸዉ አስተዳደር ላይ የሚኖራቸውን እምነት ከፍ ያደርጋል። መልካም አስተዳደር ለዜጎች/ተገልጋዮች ስለ አሰራራቸው፣ ስለበጀት አጠቃቀማቸው ግልጽ መረጃ የሚሰጡ፣ ለውሳኔያቸውና ለሥራቸው ውጤት በህዝብ ተጠያቂ የሚሆኑ፣ ህጎችና ደንቦች በሁሉም ዜጎች ላይ እኩል የሚተገብሩ*

ተቋማት፣ መሪዎችና የመንግሥት ሠራተኞች እንዲኖር የሚያደርግ በመሆኑ ህዝብ/ዜጎች በመንግሥትና በተቋማት ላይ ያላቸው እምነት ይጨምራል።

**2. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠንና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ያግዛል**

መልካም አስተዳደር ህዝብ በመንግሥት የልማትና ማህበራዊ ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም በአካባቢያቸው ጉዳዮች ተሳታፊ የሚሆኑበት፣የልማት ሥራዎችን በጀትና የበጀት አጠቃቀም በተመለከተ ግልጽና ወቅታዊ መረጃ የሚያገኙበት በመሆኑ ህዝብ የልማት ሥራዎችን እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር እድል ይሰጣል። ይህም የአገር ሀብትን ከብክነት በጸዳ መልኩ በመጠቀም በአጭር ጊዜ የሀገርና የህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ለማሟላት የሚበጅ የልማት ተግባራት ለማከናወን እና የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያስችላል።መልካም አስተዳደር የሀገርን የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና ካባቢያዊ ሁኔታዎችን በዘላቂነት በመጠበቅ የህዝብን የልማት ጥያቄ ለመመለስና ድህነትን ለመቀነስ ያስችላል።

**3. ሙስናን ፣ ብልሹ አመራርን ፣ የሀብት ብክነትንና ስጋትን ይቀንሳል**

መልካም አስተዳደር የመንግሥት አሰራርና ውሳኔዎች ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት፣ ፍትሃዊነትና የህግ የበላይነት የሚረጋገጥበት በመሆኑ ህዝብ ስለመንግሥት አሰራር የማወቅና መረጃ የማግኘት መብት የሚከበርበት፣ የመንግሥት በጀት አጠቃቀምና አሰራሮች ሁሉ ግልጽ የሚሆኑበትና ሃላፊነታቸውን የማይወጡ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት በመሆኑ የአስተዳደር በደል፣ ብልሹ አሰራር፣ ሙስናና የሀብት ብክነትን ለመቀነስና ለመከላከል ያስችላል።

**4. ፍትሀዊና ዲሞክራሲያዊ አሰራርን ያሰፍናል ፣ ግጭቶችን ይቀንሳል**

መልካም አስተዳደር በመንግሥት አገልግሎቶች፣ በአገር ሀብትና ልማት ሁሉን አቀፍ የዜጎችን ተጠቃሚነትና ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ በመሆኑ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ፣ የተገለሉና የተረሱ የህበረተሰብ ክፍሎች በማንኛውም አገራዊ ጉዳይ የባለቤትነት ድርሻና ተጠቃሚነት እንዲኖራቸው ያስችላል። ዜጎችና አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በውሳኔ ተሳታፊ ስለሚሆኑ ፍትሃዊነትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ያጠናክራል። ይህም በዜጎች መካከል አድሎና ልዩነትን ስለሚያስቀር መተማመንና ዘላቂ ሠላም እንዲኖር ያደርጋል። ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር የመልካም አስተዳደር መስፈን የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታን

ያፋጥናል ፤ አስተማማኝ ሰላም እንዲኖር ያደርጋል ፤ የሁሉንም ብሄር/ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ጥቅም ያስከብራል እንዲሁም እኩል ተጠቃሚነታቸውን ያረጋግጣል፡፡

**5. የተሻለ የውሳኔ አሰጣጥ እንዲኖር ያደርጋል**

መልካም አሰተዳደር በሰፈነበት ሥርዓት የህዝብ መሪዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የአስተዳደር አካላት ለውሳኔያቸውና ለተግባራቸው ተጠያቂነት ያለባቸው በመሆኑ ግልጽና ታማኝ በሆኑ ውይይቶች ህብረተሰቡንና ባለድርሻዎችን በማሳተፍ መልካምና በአጠቃላይ የማህበረሰቡን ጥቅሞች የሚያስከብሩ ውሳኔዎች ለመወሰን እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ውሳኔዎችም በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ በጣም የተሻለና ተቀባይነት ያለው ወሳኔ ለመወሰንና ተግባራዊ ለማድረግ መልካም አስተዳደር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**መልመጃ 2.3**

**መመሪያ፡ የስልጠናው አሳታፊ በሚሰጣችሁ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሱ፡፡**

1. ከመልካም አስተዳደር ጠቀሜታና አስፈላጊነት መካከል ሙስናና የሀብት ብክነትን መከላከል ወይም መቀነስ አንዱ ነው፡፡ እንዴት?
2. መልካም አስተዳደር በዜጎች መካከል ግጭት እንዳይፈጠርና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን እንዴት እንደሚያስችል አብራሩ?
3. መልካም አስተዳደር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶችን ለማፋጠንና ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡ እንዴት?

**መልመጃ 2.4**

**መመሪያ፡ አመቻቹ በሚሰጣችሁ መመሪያ መሠረት ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ መሰረት አድርገው በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን አቅርቡ፡፡**

**ኬዝ አንድ**

አቶ ሠለሞን የአንድ ዘን አመራር ናቸው፡፡ በመሆኑም የዞኑን የአስተዳደር የማናጅመንት አባላት ሰብሰበው የዞኑን የልማት እቅድ ያቅዳሉ፤ ከእቅዳቸው መካከል በዞኑ/ወረዳ ለሚገኘው የለምለም ቀበሌ አርሶ አደሮች ጤና ጣቢያ መስራት አንዱ ነው፡፡ እቅዳቸውን ለማስፈጸም ወደ ለምለም ቀበሌው በመሄድ የቀበሌው ሊቀመንበር ህዝቡን እንዲሰበስብላቸው ያደርጋሉ፡፡ ለህዝቡም እዚህ የተገኘሁት ለዚህ ህዝብ ያስፈልጋል ያልኩትን የጤና ጣቢያ ግንባታ

ለማስጀመር ነው በማለት ከገለጹ በኃላ ለግንባታው እያንዳንዱ አባወራ አምስት አምስት መቶ ብር እንዲዋጣ ፣ ለግንባታው ምቹ የሆነ ቦታ ከነዋሪው ይዞታ አንዱ ተመርጦ እንዲሰጥ እንዲሁም ይህንን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያስፈጽሙ የአምስት ሰዎችን ሰም ጠርተው እንድታስፈጽሙ ብለው ወደ መጡበት ይመለሳሉ፡፡ በወሩ ሥራው ምን ላይ እንደደረሰ ለመመልከት ሲመጡ የተመረጡት ሰዎች ህዝቡ እምቢተኛ መሆኑንና እንደውም አመጽና ተቃውሞ ለማስነሳት እየተዘጋጀ እንደሆነ ይገልጹላቸዋል፡፡

1. ይህን ኬዝ ከመልካም አስተዳደር መርሆዎች አንጻር መዝኑ?
2. የለምለም ቀበሌ ነዋሪዎች አንድ የልማት ሥራ የሆነውን የጤና ጣቢያ ግንባታ ያልተቀበሉት ለምንድ ነው?
3. የተጣሱ የመልካም አስተዳደር መርሆዎች የትኞቹ ናቸው?

**መልመጃ 2.5**

**መመሪያ፡ አመቻቹ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ቀጥሎ የቀረበዉን ኬዝ መሰረት አድርገው በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን አቅርቡ፡፡**

**ኬዝ ሁለት**

ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል በሚፈልጉ ሥረዎች ላይ የተሰማሩ 500 የሚሆኑ የአንድ ትንሽ የገጠር ከተማ ነዋሪዎች ለከተማቸው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከፍተኛ ሃይል የሚሸከሙ ቆጣሪ እንዲያቀርብላቸው ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሃላፊ ጥያቄውን ለዋናው መሥሪያ ቤት በማቅረብ 100 ቆጣሪዎች ይላክለታል፡፡ ቆጣሪዎችን ለሚፈልጋቸው 100 ሰዎች ይሰጣል፡፡ በዚህ ምክንያት ሌሎች ቅሬታና ተቃውሞ ሲያቀርቡ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሃላፊ ቆጣሪውን ለማግኘት መስፈርቶቹን ስለማታሟሉ ነው የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡

1. ይህን ኬዝ ከመልካም አስተዳደር መርሆዎች አንጻር መዝኑ?
2. የተጣሱ የመልካም አስተዳደር መርሆዎች የትኞቹ ናቸው?

## የክፍለ ትምህርቱ ማጠቃለያ

***በዚህ ክፍል ስለ መልካም አስተዳደር መሰረታዊ መርሆዎች ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በክፈለ ትምህርቱ እንደተብራራው መልካም አስተዳደር ስምንት መሰረታዊ መርሆዎች አሉት፡፡ መልካም አስተዳደር በህዝቦች ተሳትፎ፣ በግልጽነት፣ በተጠያቂነት ፣በህግ የበላይነት፣በፍትሃዊነት መርሆዎች ላይ በመመስረት ለህዝቦች ፍላጎት***

**ፍትሃዊ፣ህጋዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ ምላሽ**

መስጠት መገለጫ ባህሪዎቹ ናቸው። ለበርካታ አገራት የድህነትና ኃላቀርነት፤ የዲሞክራሲ ፣ የህዝቦች ሠላምና የልማት የለውጥ ጥረቶች ስኬታማ አለመሆን ምክንያት የመልካም አስተዳደር እጦት ችግር እንደሆነ በበርካታ ጥናቶች ተረጋግጧል። መልካም አስተዳደርን ማስፈን ቀጣይነት ያለው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትና እድገት ለማምጣትና ህዝቦችን ተጠቃሚ ለማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ በዓለም አገራት ዘንድ የታመነበትና ትኩረት ያገኘ ጉዳይ ነው። መልካም አስተዳደር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል፣ በህዝቦች መካከል ፍትሃዊነትና እኩልነት ለማስፈን፣ መተማመንና ሰላምን ለመፍጠር፣ ዘላቂነት ያለው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ለማረጋገጥና ለድህነት ቅነሳ አስፋለጊ ሥርዓት ነው።

## ክፍል ሦስት

## 1.3 የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶች እና መልካም አስተዳደርን መገንባት

### አጭር መግለጫ

በዚህ ክፍል መልካም አስተዳደርን በአግባቡ ለመተግበርና ለማስፈን እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮች እና መልካም አስተዳደርን ለመገንባት የሚያግዙ አሰራሮችና መርሆዎች ይብራራሉ። ትምህርቱ በሦስት ንኡሳን ክፍለ ትምህርቶች ቀርቧል። በመጀመሪያው ትምህርት መልካም አስተዳደርን በማስፈን ሂደት የሚገጥሙ ዋነኛ ተግዳሮቶች፤ በሁለተኛው ትምህርት መልካም አስተዳደርን መገንቢያ መንገዶች ሲቀርቡ። በትምህርት ሦስት ደግሞ በመልካም አስተዳደር ግንባታ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ቁልፍ ተዋናዮችና ሚናቸውን የሚመለከቱ ሃሳቦች ይብራራሉ።

### የትምህርቱ ዓላማዎች

ከዚህ ትምህርት በኃላ የሥልጠናው ተሳታፊዎች፡

- መልካም አስተዳደርን በማስፈን ሂደት የሚገጥሙ ተግዳሮቶችን ይለያሉ፤
- የመልካም አስተዳደር መገንቢያ መንገዶችና መወሰድ ስለሚገቡ እርምጃዎች ያብራራሉ፤
- በመልካም አስተዳደር ግንባታ ወሳኝ ሚና ያላቸውን ቁልፍ አካላት ይዘረዝራሉ፤
- በአገራችንና የተቋማቸውን የመልካም አስተዳደር ሁኔታ ይገመግማሉ ፣ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ያስቀምጣሉ።

## መነሻ ተግባር 3.1

**መመሪያ:** ያላችሁን እውቀትና ልምድ በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. መልካም አስተዳደር በማስፈን ሂደት እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ምንድን ናቸው ትላላችሁ?
2. መልካም አስተዳደርን እንዴት መገንባትና ማጠናከር ይቻላል ትላላችሁ?
3. መልካም አስተዳደርን እውን ለማድረግ ወሳኝ ሚና ያላቸው አካላት እነማን ናቸው? ሚናቸውን አብራሩ?

## ትምህርትአንድ

## 1.3.1 የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶች

**በመልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት ተግዳሮት የሚሆኑ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?**

የመልካም አስተዳደር ትግበራ ስኬታማ ነው የሚባለው የህዝብ ተሳትፎን ፣ የህግ የበላይነት ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍኑ ፣ የአገርና የህዝብ ሃብቶች ውጤታማ ፣ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በመጠቀም ለህዝብ ወሳኝ ፍላጐቶች ፈጣንና ቀልጣፋ ምላሽ መስጠት የሚያስችሉ ፣ እንዲሁም የዜጎችን ሠላም ፣ ደህንነት እና ነጻ እንቅስቃሴ የሚያረጋግጡ፣ሀብትና ሥራ ፈጥረው ድህነትን ማቃለል የሚያስችሉ አሰራሮች፣ተቋማትና የህብረተሰብ ክፍሎች መገንባትና እውን ማድረግ ሲቻል ነው።

### መልመጃ 3.1

**መመሪያ: ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ዙሪያ የኢትዮጵያንና የየመስሪያ ቤታችሁን ተጨባጭ**

**ሁኔታ በመዉሰድ ተወያዩ።**

1. በኢትዮጵያ የመልካም አስተዳደርን አተገባበር እንዴት ይመዝኑታል?
2. በኢትዮጵያ የመልካም አስተዳደር አተገባበር ስራ ጠንካራና ደካማ ጎኖቹ ምንድን ናቸዉ?
3. በአገሪቱ ውስጥ የመልካም አስተዳደር ትግበራን በተመለከተ ምን ተግዳሮቶች አሉ? ፈተናዎቹስ ምን ምን ናቸዉ?

4. በምትሰሩበት ተቋም (ወይም ሰፊ ህዝባዊ አገልግሎት ያለው ተቋም) የመልካም አስተዳደር አፈፃፀምና ዉጤታማነት ምን ይመስላል?
5. በአገራችን ወይም በምትሰሩበት አካባቢ በመልካም አስተዳደር በምሳሌነት የምትጠቅሷቸው ተቋማት አሉ? ምሳሌ የሆኑባቸውን ጉዳዮች አብራሩ?
6. ከግል ተሞክሮዎችዎ በመነሳት የመልካም አስተዳደር መርሆዎች በአገራችን በተለያዩ የፖሊሲና የህግ ማእቀፎች ውስጥ እንዴት እንደተካተቱና ስለተግባራዊነታቸው አስረዱ?

ከላይ የተጠቀሱን ጉዳዮች እውን እንዳይሆኑ በመልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት የሚገጥሙ በርካታ ተግዳሮቶች ወይም እንቅፋቶች አሉ፡፡ መልካም አስተዳደርን በማስፈን ተጠቃሚ ለመሆን በግንባታው ሂደት የሚገጥሙ ተግዳሮቶችና መንስኤያቸውን መለየትና እንቅፋቶቹን መፍታት ያስፈልጋል፡፡ በመልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት እንቅፋት ከሚሆኑ ተግዳሮቶች መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

## 1. የቁርጠኝነት ማነስ

መልካም አስተዳደር ትግበራ ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች ለበርካታ አገራት መልካም አስተዳደር ግንባታ ዋነኛ ችግር የፖለቲካ ሹመኞች እና የመንግስት ሰራተኞች የመልካም አሰተዳደር መርሆዎችን በተሟላ መልኩ ለመተግበር ቁርጠኛ አለመሆን እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ መንግሥታት የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታትና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን ለማሻሻል አሰራሮችን ማሻሻል፣ አስተዳደራዊ የቁጥጥርና የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት እና ማጠናከር፣ ህግና ደንቦችን የማሻሻልና የማውጣት ሥራዎችን ሲሰሩ ይታያሉ፡፡ ይሁን እንጅ መሻሻያዎችን ተግባራዊ በማድረግ በኩል ቁርጠኝነት ስለሚጎድላቸውና በዚህም ተጠያቂነት ስለማይኖር የተሻሻሉ የአሰራር ሂደቶችና ደንቦች በአግባቡና በተከታታይ ተፈፃሚነት ያጣሉ፡፡ ይህም በመልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት ላይ እንቅፋት ይፈጥራሉ፡፡

## 2. የአቅምና ብቃት ማነስ

የህዝብ የልማት ፍላጎትና የአገልግሎት ጥያቄን ለመመለስ የህዝብ ተመራጮችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ የመሪዎችና የሰራተኞች አቅምና ብቃት ማነስ ለመልካም አስተዳደር ግንባታ እንቅፋት ከሚሆኑ ጉዳዮች መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እያደገ የመጣውን የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ለመመልስ የልማት ሥራዎችን የማቀድ ፣ የመተግበር ፣ የመከታተልና የመመዘን አቅም ያላቸው፣

እንዲሁም የህግ የበላይነት፣ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የሚችሉ የተቋማት መሪዎች፤ አዳዲስ አሰራሮችን እና ዉጤታማ የማሻሻያ ስትራተጂዎች የሚያዘጋጅና የሚተገብር የሰው ኃይል እንዲሁም ይህንን ለመተግበር የሚችል የቴክኖሎጂና በቂ የሀብት አቅርቦት ያለመኖር ለመልካም አስተዳደር አውን መሆን ተግዳሮት ይሆናሉ፡፡

## 3. የቢሮክራሲ ችግሮች

የቢሮክራሲ መሥራች ከሆኑት ሰዎች አንዱ የሆነዉ ጀርመናዊዉ ሶሾሎጂስት ማክስቬበር (Max Weber- 1864-1920) እንዳለዉ "ቢሮክራሲ አጠቅላይ የሆኑ ደንቦችን በዝርዝር ጉዳዮቹ መተግበር የሚያስችል ተቋማዊ አሠራር ሆኖ የመንግስት ተግባር ፍትሃዊና ተገማች እንዲሆን ያደረጋል"፡፡ ይሁን እንጂ በቢሮክራሲያዊ መንግሰት አስተዳደር ሂደት ውስጥ ሁለት ችግሮች አሉ እነሱም ብቃት ማነስና በዘፈቀደ መስራት ናቸዉ፡፡ እነዚህ ደግሞ በበርካታ ሀገራት ዉስጥ የተካሄዱ አስተዳደራዊ ለዉጦች በሚከተሉት ብሮክራሲያዊ ምክኒያቶች ሙሉ በሙሉ እንዳልተሳኩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም እና የአለምባንክ ያካሄዷቸዉ ጥናቶች ውጤታማ ያልሆነ ቢሮክራሲ ለመልካም አስተዳደር መስፈን ዋነኛው ችግር መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት አስተዳደሮች ቅልጥፍናን ለማሻሻልና ሙስናን ለመቀነስ ቢሮክራሲውን መልሶ የማደራጀትና መልሶ የማቋቋም መርሃ ግብሮችን አከናውነዋል፡፡ ይሁን እንጅ በታዳጊ አገሮች የሚሰጡ የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶች የሚከተሉትን ጨምሮ በርካታ ድክመቶችን እንዳለ ያመለክታሉ፡፡ እነኝህ ድክመቶች መልካም አስተዳደር እውን እንዳይሆን እንቅፋት ሆነው ቆይተዋል፡፡

- ደካማ የእቅድ፣ የአጀንዳ አቀራረብና የፖሊሲ አወቃቀሮች፤
- አግባብ ያለው የስራ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት አለመተግበርና አለማስቀጠል፤
- ተደራራቢና የተዛቡ የመንግሥታዊ ተግባራትና ክንዋኔዎች፤
- ለተቀመጡ ውጤቶችና ዕቅዶች መሳካት ከሀብት ቁጥጥር ይልቅ ለህጎች እና ሂደቶች ከፍተኛ አፅንዖት መስጠት፤
- በከፍተኛ ሁኔታ በፖለቲካዉ የሚዘወር ቢሮክራሲ መኖር፤

- አስፈላጊው የአስተዳደርና የቴክኒክ አቅም ማነስ፤ እነዚህ ክፍተቶች መልካም አስተዳደር እውን እንዳይሆን እንቅፋት ሆነው ቆይተዋል፡፡

## 4. ሙስናና ብልሹ አሠራር

የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ፅንሰ-ሀሳቦች እርስ በርስ የሁለትዮሽ የምክንያት ግንኙነት ያላቸው እና እርስ በርስ በመጥፎ አዙሪት ውስጥ ይመጋገባሉ፡፡ የመልካም አስተዳደር መርሆዎችና አወቃቀሮች ካልተዘረጋ ለሙስና ትልቅ እድል ይፈጥራል፡፡ ሙስና በበኩሉ የመልካም አስተዳደር መርሆችና አወቃቀሮችን እንዳይዘረጉ ወይም እንዳይተገበሩ ያደርጋል፡፡

በታዳጊ አገራት የልማትና ፋይናንስ ላይ የተደረገ ጥናቶች ከታዳጊ ሀገራት ጠቅላላ በጀት ውስጥ ከ13 በመቶ በላይ የሚሆኑት በሙስና እንደሚመዘበር ይገልጻሉ፤በዚህም መንግስታት ለህዝብ የልማት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ የመስጠት አቅም ያጣሉ፡፡

ሙስና የመልካም አስተዳደር እሴቶች የሆኑ ግልጽነት፣ተጠያቂነት እና የህግ የበላይነትን እውን እንዳይሆኑ በመጣስ እንቅፋትና ችግር ይፈጥራል፡፡ በህግ እኩል የመዳኘትን፣ግልጽነትና ተጠያቂነትን ስለሚቀንስ የሕግ የበላይነት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ሙስና የህዝብ አገልግሎቶችና የልማት ሥራዎች በጥቅምና በዝምድና ግንኙነት ከሕግ ውጪ እንዲከናወኑ በማድረግ፣ ዜጐች በሀገራቸው ብሔራዊ ሃብት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መብታቸው እንዲነካና አድሎ እንዲፈጸምባቸው ስለሚጋብዝ መልካም አስተዳዳር እንዳይሰፍን እንቅፋት ይሆናል፡፡

የመልካም አስተዳደር እጦት ለግለሰቦችና ቡድኖች ፈላጭ ቆራጭነት፣ ለአድሎአዊ አሰራር፣ ለመብት ጥሰቶች፣ስለሚዳርግ ለግጭት መከሰትና ለሠላም መደፍረስ መንስኤ ይሆናል፡፡ ዞሮ ዞሮ ሙስናና የመልካም አስተዳደር እጦት ዴሞክራሲን፣ የህግ የበላይነትን እና የኢኮኖሚ ልማትን የሚያናጉ የጸጥታ ችግሮች ስለሆኑ ለመልካም አስተዳደር እውን መሆን ተግዳሮት ይሆናሉ፡፡

## 5. ህብረተሰቡንና ባለድርሻ አካላትን በስፋት አለማሳተፍ

ከመልካም አሰተዳደር መገለጫዎች መካከል የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ አንዱ ነው፡፡ ህዝብ በሚመለከተው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አለማሳተፍ ለመልካም አስተዳደር እውን መሆን እንቅፋት ይሆናል፡፡ ህዝብ ስለመንግስት አሰራር፣የልማት አጀንዳዎች የበጀት ምንጭና አጠቃቀም ማወቅና ስምምነቱን የጠበቁ ሊሆኑም ይገባል፡፡ በመሆኑም የመንግሥት ተቋማት ህብረተሰብና ባለድርሻ አካላት ምክክር የሚያደርጉበት፣ የህብረተሰቡን አስተያየትና እርካታ ምላሽ የሚያገኙበት አሰራር ካለዘረጉ፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን ለህብረተሰቡ ፍላጎት ምላሽ መስጠት አይችሉም፡፡

## 6. ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት

በየደረጃው በሚገኙ የህዝብ መስተዳደር አካላትና የመንግሥት ተቋማት አሰተዳደራዊ ሥራዎችና ውሳኔዎች ላይ ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነት መኖር ሌላው የመልካም አስተዳደር ተግዳሮት ነው፡፡ በአካባቢ ደረጃ የሚገኙ የአስተዳደር አካላትና ተቋማት እንዲሁም በመልካም አስተዳደር ግንባታ ሚና ያላቸው (ሚዲያ፣ ሲቪክ ማህበራት) አካላት ባላቸው ህጋዊ ስልጣን በነጻነት የማቀድ ፣ የመተግበርና የመወሰን አቅም ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በአካባቢ መስተዳደርና በመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አስተዳደራዊ ሥራዎችና ውሳኔዎች ላይ የፖለቲካ አመራሩ ጣልቃ ገብነትና ውሳኔዎችን የመቀልበስ ሁኔታ መልካም ስራዎችንና መልካም አስተዳደር የሚያደናቅፉ ናቸው፡፡

**መልመጃ 3.2**

**መመሪያ፡ ቀጥለው በቀረቡ ትጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን አቅርቡ፡፡**

1. የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለመኖር ለመልካም አስተዳደር እንዴት እንቅፋት ይሆናል?
2. መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ተግዳሮት ከሚሆኑ ችግሮች መካከል ሙስና ተጠቃሽ ነው እንዴት ሙስና ተግዳሮት እንደሚሆን ከተቋማችሁ ወይም ከልምዳችሁ በምሳሌ በማሳየት አብራሩ?
3. የአቅም ማነስ እንዴት ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ተግዳሮት ይሆናል?
4. ከላይ የቀረቡትን የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶች ይበልጥ እንቅፋት ናቸው የምትሏቸውን በደረጃ አስቀምጡ? ምክንያታችሁን አቅርቡ?
5. ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ለመልካም አስተዳደር እንቅፋት ናቸው የምትሏቸውን ጉዳዮች አቅርቡና አብራሩ?

## ትምህርትሁለት

### 1.3.2 መልካም አስተዳደርን መገንባት

‹መነሻ ተግባር 3.2

***መመሪያ: ያላችሁን እውቀትና ልምድ በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. *መልካም አስተዳደር ለመገንባት ምን መደረግ አለበት?*
2. *በኢትዮጲያ መልካም አስተዳደር ለመገንባት ምን ተግባራት ተከናውነዋል?*

---

*መልካም አስተዳደርን ለመገንባት የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን እና የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ መልካም አስተዳደርን ለመገንባት የሚከተሉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መተግበር እንዳለባቸው በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች የውጤታማ አገራትን ተመክሮዎች መሰረት በማድረግ ያስረዳሉ፡፡*

### 1. *ጠንካራ ተቋማትን መገንባትና ማጠናከር*

*መልካም አስተዳደርን ማስፋፋት የተመሰረተዉ ጠንካራ ተቋማትን በማቋቋም ላይ ነው:: የመልካም አስተዳደር ግንባታ እያደገ የመጣውን ሰፊ ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የህዝብን የልማት ፍላጎትና ተጠቃሚነት ጥያቄ መመለስ የሚችሉ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሆኑ፣ በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፁ የመንግሥት ተቋማት ፣ ባለሥልጣንና ሠራተኞችን ይፈልጋል፡፡ መልካም አስተዳደር የሚገነባው በመንግሥት ተሳትፎ ብቻ ባለመሆኑ ጠንካራ የግል ዘርፍና የሲቪክ ማህበራት ሊገነቡ ይገባል ፡፡ መልካም አስተዳደር የህዝብ የልማት ሥራዎች የሚያቅድ ፣ የሚተገብር ፣ የመልካም አስተዳደር የለውጥ መሳሪያዎችን በአግባቡ መተግበርና ውጤታማ መሆን የሚችል እውቀትና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል እና የህግ የበላይነት ማረጋገጥ የሚችሉ ነፃና ጠንካራ ቋማትን መገንባት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን መሰረታዊ*

ጉዳይ ነው። ነጻና ጠንካራ ተቋማት መገንባት ካልተቻለ መልካም አስተዳደርን እውን ማድረግ አይቻልም። ተቋማትን አቅም ከመገንባት አንጻር፦

- የዲሞክራሲ ተቋማትን መገንባት፣ የህዝብ ምርጫ ቦርድ፣ ሰብአዊ መብት፤ ፀረ-ሙስናን ፣ የእንባ ጠባቂ ተቋማትን መገንባትና በነጻነት እንዲሰሩ ማድረግ፤
- የኦዲት፣የፋይናንስ አስተዳደርና የፕላን ኮሚሽን ተቋማት አቅም ማሳደግ፤
- የመንግሥት ሚኒስተሮችና ሰራተኞች በተለይ በእቅድ፣ በፕሮጀክት አስተዳደርና በፋይናንስ ማናጅመንት አቅም በስልጠና መገንባት፤
- ያለተማከለ አስተዳደር ማጠናከር ፤ የአካባቢ መስተዳደር አካላትን ማጠናከር፤
- የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማጎልበት፤
- የውስጥና የውጪ የፋይናንስ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎች ናቸው።

## 2. የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ

መልካም አስተዳደር በመገንባት ሂደት ውስጥ አንዱና ዋነኛው ጉዳይ የዜጎችን የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን በብቃት ለመመለስ የሚያስችሉ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይህም የህግ የበላይነትን፣የመንግሥት አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት መሆኑን የሚያረጋግጡ፣የህዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲዊ መብቶች፣ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚነት እና ቀልጣፋና ጥራት ያለው የመንግሥት አገልግሎቶች የማግኘት መብቶችን የሚያስከብሩ ህጎችና ፖሊሲዎች መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 3. የህዝብ ተሳትፎን ማሳደግ

መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በአጠቃላይ ህዝብ በመንግሥት ፖሊሲዎች፣የልማትና ማህበራዊ ፕሮግራሞች፣በአካባቢያቸው ጉዳዮች እቅድና ትግበራዎች ላይ ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል አሰራሮችና ሥርኣት መዘርጋትን ይጠይቃል። የህዝብ ተሳትፎን ለማረጋገጥ ቡድኖችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሁሉም የአመራር ደረጃ የሚሳተፉበትና በቀጥታ ወይም ፍላጎታቸውን በሚወክሉ ተቋማትና አካላት ውክልናቸው የሚረጋገጥበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል።

ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በመገንባት የህዝብ ተሳትፎ ለማረጋገጥ፡

- ነጻና ፍትሃዊ የህዝብ ምርጫ ተቋምና አሰራር መዘርጋት እና ማጠናከር፣ጠንካራ የህግ ማእቀፍና የአሰራር ነጻነት መስጠትና በሰው ኃይልና በማቴሪያል በቴክኖሎጅ ማጠናከር፤
- የሴቶች እና የአናስተኛ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ብሄረሰቦች፣አካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ማጠናከርና መደገፍ፤
- የህዝብ ተወካዮች ምክርቤቶችን፣የአካባቢ አስተዳደር ምክር ቤቶችን እና የመንግስት ተቋማትን ነጻነትና አቅም ማጠናከር መጠበቅ፤
- የሲቪክ ማህበራት ተሳተፎ ማስፋትና ማጠናከርና፤

## 4. ሙስናን መከላከልና መቆጣጠር

ሙስና የመንግስት ተቋማትና ሰራተኞች ለህዝብ ፈጣን ፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታቸዉን እንዳይወጡ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ሙስና በህግ እኩል የመዳኘትን ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዳይኖር ዜጐች በሀገራቸው ሃብት እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ፣ መብታቸው እንዲነካና አድሎ እንዲፈጸምባቸው ስለሚያደርግ መልካም አስተዳዳር እንዳይሰፍን እንቅፋት ይሆናል። መልካም አስተዳደር ለማስፈን ሙስናን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችሉ ሥራዎች መስራት ያስፈልጋል። ሙስናን ለመከላከል፡-

- ነጻና ጠንካራ የጸረሙስና ተቋማት ማቋቋም እነዚህን በሰው ኃይል ፣ በማቴሪያልና በቴክኖሎጂ ማጠናከር፤
- ጠንካራ የህግ ማቅፎች ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ፤
- የህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ሰራተኞች፣ተመራጮች፣የፍትህ አካላትና የመንግሥት ባለስልጣናት የሚመሩበት የሥነምግባር ደንብ ማዘጋጀትና መጠቀም ያስፈልጋል።

## 5. ጠንካራ የግል ሴክተርና የሲቪክ ማህበራት መገንባት

የግሉ ሴክተር እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሲቪክ ማህበራት መልካም አስተዳደር በመገንባት ከፍተኛ ሚና ያላቸው ክፍሎች ናቸው። የህዝብ የልማት ፍላጎትና ተጠቃሚነት ጥያቄ በመንግሥት ጥረት ብቻ የሚመለስ አይደለም በመሆኑም የግል ሴክተሩ የልማትና የኢኮኖሚ እድገት ዋነኛው ኃይል በመሆን የስራ ፈጣሪነቱን እና በመንግሥት የማይሸፈኑ የልማት ሥራዎችን የመሙላት ሃላፊነቱን እንዲወጣ ነጻ የገበያ ሥርዓት በመዘርጋት ማጠናከር ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ወሳኝ ጉዳይ ነው። በተመሳሳይ የሲቪክ ማህበራት የቡድኖች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ በማስተማርና በማስተባበር የመንግስትንና የግል ተቋማትን አሠራር በመከታተል ለማስተካከል ይሰራሉ። በመንግስት ወጪ

ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ባለሙያዎችንና ሰራተኞችን በማቅረብ ፣ በመከታተልና ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት እንዲስተካከል የማድረግ ሚና ያላቸው በመሆናቸው መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሲቪክ ማህበራት መገንባትና ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም

- ሲቪል ማህበራትን አቅም መገንባት፤
- የመንግሥትን አሰራር ለመከታተል የሚያስችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- የተሳትፎ ምህደሩን ማስፋት ፣ የተረሱ አካላትን ድምጽ የሚያሰሙትን መደገፍ፤

## 6. የህግ የበላይነትን ማጠናከር

መልካም አስተደደር ለማሰፈን የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ደግሞ ነጻና ጠንካራ የፍትህ ሥርዓትና ተቋማት እንዲሁም የፖለቲካ ቁርጠኝነት መኖር የግድ ያስፈልጋል፡፡ የህግ የበላይነት ባልተረጋገጠበት መልካም አስተዳደርን መገንባት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፡

- ነጻ ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የፍትህ ሥርዓት መገንባት፤
- የህግ ሥርዓት ማሻሻያ ማድረግ፤
- የፍትህ አካላትን አቅም መገንባት፤
- የፍትህ አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግና የህግ ንቃተ ህሊናን በህብረተሰቡ ዘንድ ማዳበር ያስፈልጋል፡፡

## 7. ጠንካራ የሚዲያ ተቋማት መገንባት

መልካም አስተዳደር ህዝብ ስለመንግስት አሰራር መረጃ የማግኘት ፣ ሃሳቡን የመግለጽና የመሳተፍ መብትና ነጻነቱን እውን የሚያደርግ ሥርዓት ነው፡፡ ይህን እውን ለማድረግ ነጻና ገለልተኛ የሆነ መገናኛ ብዙሃን በመልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የህዝቡ አንደበት ሆኖ በማገልገል ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ መገናኛ ብዙሃን የህዝብን ፍላጎትና ሃሳብ በመግለጽ የህዝቡን ንቃተ ህሊና እንዲዳብር አስተዋፅዎው ከፍተኛ ነው፡፡ የህዝብ ተመራጮች ህጋዊና ፍትሃዊ አሰራሮችን ተከትለው እንደሚሰሩ፣ የህዝብ ሃብትን በተገቢው መንገድ ከሙስና በጸዳ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንደሚያውሉ ግልጽ፣ ወቅታዊና ፈጣን መረጃ ለህዝብ በመስጠት ተጠያቂነትና ግልጽነት እንዲሰፍን ትልቅ መሳሪያ በመሆኑ መልካም አስተዳደር ለመገንባት ነጻና ገለልተኛ ሚዳያ መገንባት የግድ ያስፈልጋል፡፡

- ሚዲያዎች ነጻ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ የፕሬስ ነጻነትን ማረጋገጥ፤
- የሚዲያ ተቋማትና ሙያተኞችን አቅም መገንባት፤

- መረጃዎችን እንደልብ እንዲያገኙና ሚናቸውን እንዲወጡ የተሳትፎ ምህዳሩን ማስፋት ይገባል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ጋር በተያያዘ የአፍሪካ ልማት ባንክ

- ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣
- የመንግስት ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ለህዝብ ግልጽ ማድረግ፣
- ሙስናን መዋጋት የሚያስችል አሰራርና ተቋማት መገንባትና፤ሙስናን በጽናት መታገል
- በየደረጃው የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥና፣
- ግልጽና በሁሉም አካባቢ ዜጎች ላይ በወጥነት የሚተገበሩ ህጋዊና ፍትሃዊ አሰራሮችን መዘርጋት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን አስፈላጊ ጉዳዮች መሆናቸውን አስቀምጧል፡፡

በተጨማሪ መልካም አስተዳደር በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ብዝሃነት ባላባቸዉ ሀገሮች እንዲተገበር የሚከተሉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መተግበር እንዳለባቸዉ የመስኩ ሙህራን ይመክራሉ፤

☞ **የህዝቦች ደህንነትን መጠበቅ**፡ ህዝቦች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው በሠላም የመኖር፣ የመስራትና ሀብት የማፍራት የህግ ከለላና ጥበቃ የማግኘት መብቶቻቸውን ማክበርና ማስጠበቅ፤

☞ **ለብዝሃነት እዉቅና መስጠት**፡ ብዝሃነትን መቀበልና ማስተናገድ፣ ሀብቶችን ለመጠቀም ያለ እድል፤ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ለመሳተፍ፤በአከባቢ የህዝብ ተቋማት ውስጥ ዉክልና ለማግኘትና የአናሳዎችን ፍላጎቶች ለሚሟላት ለብዝሃነት እውቅና መስጠት የመጀመሪያው እርምጃ ነው፡፡

☞ **የአካባቢ አስተዳደረን አቅም ማሻሻል**፡ በአካባቢ ደረጃ ህጎችን ለመተግበርና አንገብጋቢ ጉዳዮችን ለመፍታት ወሳኝ ሚናን የሚጫወቱ የአካባቢውን ህዝብ አስተዳደር የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ የአካባቢ አስተዳደሮች ፖሊሲዎችን ፣ የለውጥና የልማት መርሃ ግብሮችን ለመተግበር እንዲችሉ አቅማቸውን የመገንባት እና አሰራራቸውን የማሻሻል ሂደቱ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

☞ **ያልተማከለ አስተዳደር**: ማዕከላዊ ወይም በቂ ያልሆነ ያልተማከለ አሰተዳደር በአካባቢ ደረጃ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ የማያስችል ሌላ እንቅፋት ነው፡፡ የውሳኔ ሰጪነት አቅም ማነስ፤ በቂ ያልሆነ የሰውና የገንዘብ ሀብት፤ በአካባቢውና በማዕከላዊ

ደረጃዎች መካከል ያለው ተደራራቢ ብቃቶች፣ ወይም በአካባቢ ውሳኔዎች ላይ ማዕከላዊ አካል ያለዉ ውሳኔዎችን የመቀልበስ ስልጣን መኖር በአካባቢ ደረጃ መልካም ስራዎችንና መልካም አስተዳደር የሚያደናቅፉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ውሳኔ ሰጪነት ተግባራት ከማዕከላዊ ወደ ክልላዊና ከዚያም ወደ አከባቢ ደረጃዎች ማዉረድ ሌላው የመልካም አስተዳደር ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

በአጠቃላይ የመልካም አስተዳደር ግንባታ የሚሳካዉ መንግስት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በዘላቂ ልማትና የዜጎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት መረጋገጥ ላይ ከፍተኛ ቁርጠኝነት ያለው ሲሆን ነው፡፡ መልካም አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ ተጠያቂነትን፣ ያልተማከለ አስተዳደርንና የህዝብ ተሳትፎ ማጠናከር፣ ውጤታማነትን፣ የህግ የበላይነትን ማስፈን እና ሙስናን መቆጣጠር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**መልመጃ 3.3**

1. በተቋማችሁ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ይታያሉ መልካም አስተዳደር እንዳይሰፍን ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
2. ችግሮቹን እንዴት መፍታት ይቻላል?
3. ጠንካራ የሚዲያ ተቋም መኖር ለመልካም አስተዳደር ግንባት እንዴት ይጠቅማል?
4. ጠንካራ ሲቪክ ማህበራት መገንባት ለመልካም አስተዳደር ግንባት ለምን ያስፈልጋል?
5. መልካም አስተዳደርን ለመገንባት ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት መካከል ይበልጥ አስፈላጊ ናቸው የምትሏቸውን በደረጃ አስቀምጡና ምክንያታችሁን ግለጹ?
6. የአገራችን ወይም የአካባቢያችሁ መስተዳደር የመልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት ምን ይመስላል?

## ትምህርት ሦስት

### 1.3.3 በመልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ተዋንያን እና ሚናቸው

**መነሻ ተግባር 3.3**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. በመልካም አስተዳደር ግንባታ ዋነኛ ተዋናዮች እነማን ናቸው?
2. መልካም አስተዳደርን ለመገንባት ከፍተኛ ሚና ያላቸው አካላት እነ ማን ናቸው?


### 1.3.3.1 በመልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ተዋንያን

በመልካም አስተዳደር ሦስት ዋነኛ ተዋናዮች አሉ፡፡ እነርሱም መንግሥት፣ የግሉ ሴክተርና ሲቪክ ማህበረሰብ ናቸው፡፡ በእነዚህ አካላት ማለትም በመንግስት፣ በግሉ ሴክተር (ገበያ) እና በሲቪል ማህበረሰቦች መካከል ያላቸው የእርስ በርስ መስተጋብር የሚመለከት የአስተዳደር ስነ- ምህዳር ጉዳይ ነዉ፡፡

- **በአስተዳደር ስነ-ምህዳር መንግስት እንደ ተዋናይ፡** መንግስት እንደ አንድ ተዋናይ የህግ አውጪ፣አስፈፃሚና የፍትህ አካላትን ያካትታል፡፡ ከሌሎች ተዋናዮች ጋር በሚኖረዉ መስተጋብር ሂደት ውስጥ መንግስት አሰቻይ የሆነ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና የህግ አካባቢን የመፍጠር ሚና ይጫወታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡
- **በአስተዳደር ሰነ-ምህዳር ውስጥ ገበያ እንደ ተዋናይ፡** ሌላው ተዋናይ ደግሞ ገበያ ነው (በተለምዶ የግሉ ሴክተር ተብሎ ይጠራል)፡፡ ይህ ዘርፍ እንደ አነስተኛ/መካከለኛ/ትልልቅ ኩባንያዎች፤ ዓለምአቀፍ ኮርፖሬሽኖችና የገንዘብ ተቋማት የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ የስራ ዕድል መፍጠር፤ የስራ ፈጠራ ክህሎትን ማዳበር፤ የገቢ ማስገኛ ዕድሎችን ማጎልበት፤ እና ለህብረተሰቡ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን ማቅረብ የዚህ ዘርፍ ኃላፊነቶች ናቸዉ፡፡
- **በአስተዳደር ሰነ ምህዳር ውስጥ የሲቪል ማህበረሰቡ እንደ ተዋናይ፡** ብዙውን ጊዜ ሶስተኛ ዘርፍ ተብሎ የሚታወቀው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ሙያዊ ማህበራት፤ ማህበረሰብ መሰረት ያደረጉ ድርጅቶች፤ የጾታ/ሴቶች/ቡድኖች፤ እምነትን መሠረት ያደረጉ ድርጅቶች፤ መገናኛ ብዙሃንና የፖለቲካ ፓርቲዎች ይይዛል፡፡ የእነዚህ አካላት ፍላጎት አብዛኛውን ጊዜ ህዝቡን በማንቀሳቀስ በራሳቸው በተለያዩ መንገድ እንዲሳተፉ ማነሳሳት ነዉ፡፡ ሰዎች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ዴሞክራቲክና ሰብአዊ መብቶቻቸው ንእንዲያውቁና እንዲጠቀሙበት

ለማድረግም የቀስቃሽነት ተግባርና ሚናም አላቸው፡፡ የአስተዳደር ስነ-ምህዳር አጽንዖት የሚሰጠዉ የእነዚህ ሶስት ተዋናዮች መስተጋብር ነዉ፡፡ ተጨባጭ ማህበራዊ ለውጥን ለማምጣት ደግሞ ተጠያቂነት በሰፈነበት፣ ግልጽ፣ አሳታፊ፣ ፍትሃዊ፣ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መመራት አለበት፡፡ ከዚህ በታች የቀርበዉ የአስተዳደር ስነ-ምህዳር ምስል የእነዚህ ሶስት ተዋናዮች እንዴት መስተጋብር እንደሚፈጥሩ የሚያሳይ ነው::

**ምስል 1፡ የመልካም አስተዳደር ስነ-ምህዳር**




## መልመጃ 3.4

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ላይ አጠገባችሁ ካሉ ተሳታፊዎች ጋር በመወያየት መልሳችሁን ለአሳታፊው ግለጹ፡፡

1. ከላይ ከቀረበው ምስል ምን ትረዳላችሁ?

2. የመልካም አስተዳደር ስርአት ከሚለው ሃሳብ ምን ተረዳችሁ?
3. ተዋናዮቹ እንዴት እርስ በርሳቸው ግንኙነት እንደሚያደርጉ ከስእሉ በመነሳት አብራሩ?

## 1.3.3.2 በመልካም አስተዳደር ግንባታ ከፍተኛ ሚና ያላቸው አካላት

**መነሻ ተግባር 3.4**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. መልካም አስተዳደርን በማስፈን ሂደት የግሉ ዘርፍ ምን ሚና አለው?
2. በመልካም አስተዳደር ግንባታ የመንግሥትን ሚና አብራሩ?
3. ነፃ፣ሐቀኛና ገለልተኛ መገናኛ ብዙሃን ምን ማለት ነው?
4. በመልካም አስተዳደር ውስጥ ነፃና ገለልተኛ ሚዲያዎች ምን ሚና አላቸው?

### 1. በታችኛው እርከን ላይ ያለው የመንግስት አካል

በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ መንግሥታት (የፌደራልም ሆነ የክልል) እና የመንግሥት ተቋማት ዋነኛ ተልዕኮ የህዝብን ሠላምና ደህንነት መጠበቅ፣ የህዝብ ፍላጎቶችን በጥራትና በቅልጥፍና ማሟላት፣ ከሙስና የጸዳ ፈጣን፣ ጥራትና ብቃት ያለው ሁሉን አቀፍ ፍትሃዊ የህዝብ አገልግሎቶች መስጠት ነው፡፡ ይህን ተልኮውን በአግባቡ ለመወጣት የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን ተግባራዊ በማድረግ መልካም አስተዳደርን መገንባት ያስፈልጋል፡፡ በከተማችን መልካም አስተዳደርን በመገንባት ሂደት ህብረተሰቡን በቀጥታ የሚያስተናግዱ የመንግስት አካላት እና ተቋማት ከፍተኛ ሚና እና ሃላፊነት አለባቸው፡፡ መንግሥት በሥስቱ የመንግሥት አካላት መልካም አስተዳደርን በመገንባት የሚከተሉት ዋና ዋና ሚናዎች ይኖሩታል፡፡

**ህግ አውጪ (የህዝብ ተወካዮች ምክርቤቶች)፡** የተወካዮች ምክር ቤቶች የህዝብ ውክልና የሚገለጽባቸው በመሆናቸው በመንግስትና በህዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ይፈጥራሉ፡፡ የተለያዩ ህዝቦች ፍላጎታቸውን የሚያንጸባርቁባቸውና መንግሥት ለህዝባዊ ፍላጎቶች ምላሽ

እንዲሰጥ በመንግሥት አስተዳደር ተሳትፋቸውን የሚያረጋግጡባቸው ናቸው። ምክር ቤቶች የሕዝቡ ተወካይ እንደ መሆናቸዉ መጠን ሕግ የማውጣት፣ ፖሊሲዎችን የመቅረጽ አሠራሮችን የመዘርጋት ስልጣን አላቸው። በዚህ ሥልጣናቸው

- የህግ የበላይነት የሚከበርበት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሚያረጋግጡ መንግሥታዊ አሰራሮችን በመዝርጋት፣ጠንካራ የህግ ማቅፎች በማውጣትና ተግባራዊ በማድረግ፤
- ምክር ቤቶች በተሰጠው ሥልጣንና ሃላፊነት የተለያዩ አስፈጻሚ ተቋማት የልማት ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች አፈጻጸም ቁጥጥራዊ ክትትል በማደግ፤
- ሙስናን ለመካላከልና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ነጻ፣ ጠንካራና ቀልጣፋ የፍትህ ሥርዓትና ተቋማት በመገንባት፤
- የህዝብ መረጃዎችን የማግኘት መብትና ተሳተፎ ለማረጋገጥ ጠናካራና ነጻ የሚዲያ ተቋማት መገንባት፣ የፕረስ ነጻነትን የሚያረጋግጡ ህግና ፖሊሲዎች ማውጣት፤
- የተለያዩ የህብተሰብ ክፍሎች፣የሲቪክ ማህበራት እና የሚዲያ ተቋማትን ተሳትፎ ለማሳደግ የተሳትፎ ምህዳሩን ማስፋት፤
- የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ደህንነት፣ የልማት ተሳትፎና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ አሰራሮችን ህጎችንና ፐሊሲዎችን በማውጣት፣ተግባራዊነታቸውን በመከታተልና በመቆጣጠር መልካም አስተዳደርርን በመገንባት ከፍተኛ ሚና አላቸው።

**ህግ አስፈፃሚው**፡ የህግ አስፈፃሚው የህግ አውጪውን ህጎችና ፖሊሲዎች በሥራ ላይ ለማዋል ኃላፊነት ያለው የመንግስት አንድ አካል ነው። የሥራ አስፈፃሚው አካል የመንግስት ፖሊሲ የማስተባበርና የማቀናጀት አጠቃላይ ሀላፊነት የሚወስዱትን የመንግሥት ተቋማት፣የፖለቲካ አመራሮችንና ሰራተኞችን ያጠቃልላል። እነዚህ አካላት የህዝብ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ የልማት እቅዶችን ህዝብን በማሳተፍ በማቀድና በመተግበር፣አሰራራቸውን ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው በማድረግ፣ ሁሉን ያካተተ ፍትሃዊ ቀልጣፋና ጥራት ያለው ህዝባዊ አገልግሎቶች በመስጠት መልካም አስተዳደርን የመገንባት ሚና አላቸው።

**ህግ ተርጓሚው**፡ ሦስተኛው የመንግስት አካል የህግ ነክ ውሣኔዎችን ለመወሰን ስልጣን ያለው የዳኝነት አካሉ ነው። የዳኞች አብይ ተግባር ሕግና ህግን ብቻ መሠረት በማድረግ በመወሰን የህግ የበላይነትና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ ነው። በመሆኑም

የዳኝነት አካሉ ህገመንግሥቱንና ሌሎች ህጎችን ብቻ መሰረት በማድረግ የዜጎችን በህግ ፊት እኩል የመዳኘት መብት በማስከበር፤ከሙስናና ከአድሎ የጸዳ ፈጣንና ቀልጣፋ ዳኝነት በመስጠት የዜጎችን ህጋዊ

መብትና ደህንነቶች በማስጠበቅ መልካም አስተዳደርን በማስፈን ጉልህ ስፍራ አላቸው፡፡ ዳኞች ከሌሎች ጣልቃ ገብነት ተጽእኖ ፍጹም ነፃና ከፖለቲካ ወገንተኝነት የጸዱ መሆናቸው የመልካም አስተዳደር መገለጫ ነው፡፡

***የአካባቢ መንግሥታት፡*** የአካባቢ መንግስታት የአካባቢ ተኮር መልካም አሰተዳደር መሰረቶች ናቸው፡፡ መልካም አስተዳደር በአካባቢ መንግስታት ደረጃ የአስተዳደሩን ውጤታማነትና ወጪ ቆጣቢነት፣ህዝባዊ አገልግሎት አሰጣጥ፤የመንግስት ፖሊሲ አተገባበርና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ጥራት፣የአካቶነትና የተጠያቂነት ሁኔታ እንዲሁም በአካባቢ ደረጃ የስልጣን አጠቃቀም ሁኔታን የሚመለከት ነዉ፡፡

የአካባቢ መንግስታት ዜጎች ፍላጎቶቻቸውን ለመግለጽ፣ ጥቅማቸውንና መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ እና በአካባቢያቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ለመምከርና ለመወሰን የሚጠቀሙባቸዉ ተቋማት ሲሆኑ ለዜጎች ማህበራዊና ህዝባዊ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ናቸዉ፡፡ ባልተማከለ አስተዳደር የአካባቢ መንግሰት የአካባቢ ነዋሪ ማህበረሰብና የተለያዩ ቡድኖች በአስተዳደር ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ እንደ መሰረት ሆኖ ያገለግላል፡፡ መሰረተ ልማት በተለይም ተጠቃሚ ላልሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ያቀርባል፡፡ የአከባቢው መንግስት ህዝብ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በማድረግና የልማት ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በማሳካት በመልካም አስተዳደር ግንባታ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

## 2. የግሉ ዘርፍ

በአሰተዳደር ጉዳይ ዉስጥ የግሉ ዘርፍ (የግል ንግድ ተቋማት) የህብረተሰቡ የኢኮኖሚና የልማት ሞተር ሆኖ ያገለግላል፡፡ መንግስት የግሉ ዘርፎች በገበያ ህግ ሊወዳደሩ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታዎች እና በልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳተፎውን ለማሳደግ የገበያ ሥርዓቱን ያመቻቻል፡፡ በዚህ ምቹ ሁኔታ ውስጥ የግሉ ዘርፍ ለማህበረሰቡ የሥራና የገቢ ምንጭ ይፈጥራል፡፡ እንዲሁም ከአካባቢዉ መንግስት የገንዘብ አቅም ውጭ የሆኑትን ሰፋፊና ታላላቅ ፕሮጀክቶችን ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ሀብቶችን ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የግሉ ዘርፍ በመንግስት ሊከናወኑ የማይቻሉ የልማት ሥራዎች ላይ ኢንቨስት በማድረግ ፍትሃዊ የኢኮኖሚ እድገትና ልማት እንዲዳርስ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲስፋፋ በማገዝ ለመልካም አስተዳደር መስፈን ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡

### 3. የሲቪል ማህበራት  መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

የሲቪል ማህበራት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመልካም አስተዳደር ግንባታ ውስጥ  ሚና የሚጫወቱ ሌሎች ክፍሎች ናቸው፡፡ የሲቪል ማህበረሰብ ፅንስ ሀሳብ ዜጎች የመደራጀት መብታቸውን በመጠቀም ለጋራ ፍላጎትና ዓላማ የሚደራጁና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርጉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሠራተኛ ማህበራት፣ የሙያ ማህበራት፣ የተማሪዎች ማህበር፣ የሴቶችና የወጣት ማህበር፣ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ተቋማትን ጨምሮ የተለያዩ ማህበራዊ አደረጃጀቶችን ያጠቃልላል፡፡

ሲቪል ማህበራት ቡድኖችና ግለሰቦች ፍላጎታቸውንና አላማዎቻቸዉን ለማሳካት የመደራጀት መብታቸው እንዲከበር መንገድ ይጠርጋሉ፡፡ የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማትና መንግስታዊ ያልሆኑ  ድርጅቶች በአብዛኛው ህዝባዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ፣ ህዝብን በማስተማርና በማስተባበር የመንግስትንና የግል ተቋማትን አሠራር በመከታተል የመደገፍ ወይንም በማጋለጥና ተጽእኖ በመፍጠር የማስተካከል ሥራ በመሥራት ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ ሲቪል ማህበራት ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለአብነት ያክል እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃና የመሳሰሉትን በማስፋፋትና በማሻሻል ለህዝቦች የጋራ ጥቅም ይሰራሉ፡፡

በአጠቃላይ የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት መልካም አስተዳደርን ለማስፋፋትና ለማጠናከር በተለያየ መንገድ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፤

- በአገሪቱ ውስጥ በየአካባቢው ያሉ መሰረታዊ የማህበረሰብ ክፍሎችን የማንቃት፣ የማንቀሳቀስና አሳታፊ በሆኑ ስልቶች ውጤታማ ዜጎችን በማብቃት፤
- የፖለቲካ መሪዎችን፣ የመንግስት ባለስልጣናትንና ተቋማትን በመከታተልና በመቆጣጠር የመንግስት ስልጣን አጠቃቀምን መቆጣጠር እና ተጠያቂነት እንዲኖር ተጽእኖ በመፍጠር፤
- የብልሹ አስተዳደርንና ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀምን በተመለከተ የህዝብ ግንዛቤ ማሳደግ፣መረጃዎችን ተደራሽ በማድረግ፣ ሙስናን በማጋለጥ ላይ በመሳተፍ፤
- የዴሞክራሲያዊ እሴቶችን በማስፋፋትና ለተግባራዊነታቸዉ እድልን በመፍጠር፣ የዲሞክራሲ ባህልን ማስረፅ ላይ በመስራት፤

- ለህዝቦች የትብብር መድረክ የሚረዳ ገንቢ የውይይት መድረክ በመፍጠር እንዲሁም በጐሳ፣በሃይማኖት ወይም በሌሎች ክፍፍል ውስጥ አዲስ የተዋሃደ ህብረት የመፍጠር ተግባር ላይ በመሳተፍ፤
- በፖለቲካ ተዋንያንና በመንግስት ተቋማት መካከል የዉይይትና የክርክር እድል በመፍጠር፤
- ግጭቶችን ለመፍታት ማማከርና እገዛ በማድረግ፤
- ህጋዊና ፍትሃዊ የህዝብ ምርጫ እንዲካሄድ የምርጫ ሂደቶችን ክትትል በማድረግ፤
- መረጃዎችን በማሰራጨት የመገናኛ ብዙሃን ሚና በመደገፍ፡፡

4. **መገናኛ ብዙሃን**

ነጻና ገለልተኛ የሆነ መገናኛ ብዙሃን በዴሞክራሲ ሥርዓትና በመልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የመገናኛ ብዙኃን ተግባራት የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- **መረጃ እና ትምህርት፡** መገናኛ ብዙሃን ዜጎችን በማስተማርና በማሳወቅ እንዲሁም ለህዝብ ትክክለኛ መረጃ በማቅረብ ረገድ ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ የመገናኛ ብዙሃን በተለያዩ ህዝባዊ ጉዳዮች ላይ የመንግሥት የልማትና ማህበራዊ እቅዶችና አፈጻጸም መረጃዎች ፈልፍሎ በማውጣት፣ በመንግስት ከሚቀርቡ መረጃዎች በስተጀርባ ያለውን እውነታ በመተንተን ትክክለኛ መረጃ ህዝብ እንዲኖረው በማድረግ ያግዛሉ፡፡ መገናኛ ብዙሃን ህዝብ ስለ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹና ግዴታዎቹ እንዲያውቅ፣ የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን እና አስፈላጊነት ህዝብን በማስተማር ህዝብን የማንቃት ሚና ይጫወታሉ፡፡ የመንግሥት የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች እቅዶችና አፈጻጸሞችን በተመለከተ ህዝባዊ ውይይቶችንና ክርክሮችን በማስተናገድ ህዝብ የመንግሥት የልማት ፖሊሲዎችና እቅዶች ላይ በቂ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲኖረው እና ምክንያታዊ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ መረጃ በመስጠት ከማገዙም በላይ ትክክለኛና ተገቢ አሰራሮችን በመጠቆም ያግዛል፡፡ ይህ ሚና በተለይም በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች ወቅት በጣም አሰፈላጊ ነዉ፡፡
- **የተለያዩ አመለከካከቶች፣ አስተሳሰቦችንና ፍላጎቶችን በማስተናገድ፡** መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተሳሰቦች ፣ አመለካከቶችና በተለይ የተረሱና ትኩረት የተነፈጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በአገር ማህበራዊ ፖለተካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የልማት ጉዳዮች

*ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የውይይት ፣ የክርክርና የሃሳብ መስጫ መድረኮች በማመቻቸት ተሳትፎና አካታችነት እንዲኖር ተጽእኖ የመፍጠር ሚና አላቸው፡፡*

- ***በመንግሥትና በሌሎች የማህበረሰቡ ተቋማት ውስጥ እንደ ጠባቂ ያገለግላል፡*** *ህዝብ መረጃ የማግኘት መብቱን እንዲከበር መረጃ የማግኘት ነፃነታቸውን በመጠቀም መንግስታት ከሚቀርቡት እውነቶች በስተጀርባ ያለውን እውነታ ሊያጋልጡ ይችላሉ ፣ እንዲሁም የመንግሥት ተቋማት፣ ባለሥልጣናት እና ሠራተኞችን ፍትሀዊ ያልሆነ አገልግሎት አሰጣጥ ፤ ህገ ወጥ ተግባራትና ብልሹ አሰራሮችን በመከታተል ለህዝብ በማጋለጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የማድረግ ሚና አላቸው፡፡*

*በአጠቃላይ መገናኛ ብዙሃን መረጃ በመስጠት፣ በማስተማርና ግንዛቤ በመፍጠር እንዲሆም ብልሹ አሰራሮችን በማጋለጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የመገናኛ ብዙሃን ይህን ሚናቸውን ለመጫወትና ሃላፊነታቸዉን ለመወጣት ነጻና ከመንግስት ቁጥጥር እና ተጽእኖ ነጻ ሊሆኑ ይገባል፡፡*

**መልመጃ 3.5 የቡድን ሥራ**

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለተሳታፊዎች አቅርቡ

1. በአገራችን ወይም በአካባቢዎ የሲቪል ማህበራት መልካም አስተዳደር በመገንባት ያላቸውን ሚና እየተወጡ ነው ትላላችሁ? ካልሆነ ምን ፈታኝ ሁኔታዎች አሉባቸው? ችግሮቹን እንዴት መፍታት ይቻላል?
2. በአገራችን የፌደራል መንግሥት ሆነ የምትኖሩበት የክልል መንግሥት እና የአካባቢዎ አስተዳደር መልካም አሰተዳደር በመገንባት ያላቸውን ሚና እና ውጤታማነት ምን ያህል ነው ትላላችሁ?
3. የሀገራችን የግልም ሆነ የመንግሰት መገናኛ ብዙሃን መልካም አሰተዳደር በማሰፈን ዙሪያ ያለባቸውን ሃላፊነትና ሚና እየተወጡ ነው ትላላችሁ? ካልሆነ ምን ፈታኝ ሁኔታዎች አሉባቸው? ችግሮቹን እንዴት መፍታት ይቻላል?

**መልመጃ 3.6 ማጠቃለያ የቡድን ሥራ**

***መመሪያ፡*** *አሳታፊው በሚሰጣችሁ መመሪያ መሰረት በቡድን በመሆን ከዚህ በታች በቀረበው የመልካም አስተዳደር መርሆዎች ትግበራ ለመገምገም የቀረበውን ሠንጠረዥ መሰረት በማድረግ*

የአካባቢያችሁን፣ የምትሰረቡትን ተቋም እና የአገራችንን የመልካም አስተዳደር ሁኔታ ገምገማና ምዘና በማድረግ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

**የተቋም/የአካባቢ አስተዳደር/ቀበሌ፣ ከተማ፣ የመልካም አስተዳደር ሁኔታ (መርሆዎች) ትግበራ ዳሰሳ**

| ተ.ቁ | መርሆዎች | የጥንካሬ ደረጃ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ጠንካራ | ጠንካራ | መካከለኛ | ደካማ | በጣም ደካማ |
| 1 | **አሳታፊነት** (participatory)<br>የከተማ (ቀበሌ) አስተዳደሩ በከተማ የልማትና ማህበራዊ ፕሮግራሞች፣በአካባቢያቸው ጉዳዮች እቅድና ትግበራዎች ላይ የማሳተፍ ሁኔታ እዲሁም ሰራተኛውንና ባለድርሻ አካላት በእቅድ ዝግጅት፣ትግበራና ምዘና የማሳተፍ ሁኔታ | | | | | |
| 2 | **የህግ የበላይነት** (follows the rule of law)<br>ለሁሉም አካል በህግና ደንብ ብቻ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ መሥራትና በህግ ፊት አኩል የማስተናገድ ሁኔታ | | | | | |
| 3 | **ግልጽነት** (Transparency)<br>ውሳኔዎች፣የአገልግሎት አሰጣጥ፣ አሰራሮች ህግና ደንብ፣በጀትና የበጀት አጠቃቀም የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎች ለህዝብ ግልጽ ማድረግ | | | | | |
| 4 | **ተጠያቂነት** (Accountability)<br>ከህግና ደንብ ውጪ ለተሰሩ ሥራዎች ፈጻሚዎችን ተጠያቂ ማድረግ ለወሰኑት ውሳኔና ለተገኘው ውጤት በጋራና በግል ተጠያቂ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 5 | **ምላሽሰጪነት**<br>ተገልጋዮች አገልግሎቶች እና የልማት ጥያቄዎች፣ ቅሬታዎችና አስተያየቶች ተገቢ፣ወቅታዊና ፈጣን ምላሽ የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| 6 | **ስምምነት ተኮር** (Consensus Oriented)<br>የተለያዩ ፍላጎቶችና አመለካከቶች በማስተናገድና ለጋራ ግብና ዓላማ ማሰለፍ | | | | | |
| 7 | **ፍትሃዊነት እና ሁሉን አቀፍ** (Equity and inclusiveness)<br>ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሀገርን ሀብትና ንብረትን፣ | | | | | |

| ተ.ቁ | መርሆዎች | የጥንካሬ ደረጃ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ጠንካራ | ጠንካራ | መካከለኛ | ደካማ | በጣም ደካማ |
| | የልማትና የመሰረተ ልማት እኩል ተጠቃሚ ማድረግ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | **ውጤታማነት እና ቅልጥፍና** (Effectiveness and Efficiency)<br>ከሀብት ብክነት እና ከሙስና የፀዳ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| **አማካይ የጥንካሬ ደረጃ ዉጤት (አጠቃላይ የጥንካሬ ደረጃ ዉጤት)** | | | | | | |

**ማስታወሻ**: እያንዳንዱ ተሳታፊ እና ቡድን በጥንቃቄ እና በትክክል ከገመገመ ዉጤቱ እንደሚከተለዉ ይተረጎማል፡፡

- **አማካይ ዉጤት 5.0 እና 4.0 መካከል ከሆነ** =በጣም ጠንካራ የመልካም አስተዳዳር ተቋማዊ ሁኔታዎች ወይም በጣም ከፍተኛ መርሆዎች ትግበራ ላይ ነው ያሉት፡፡
- **አማካይ ዉጤት 3.9 እና 3.0 መካከል ከሆነ** = ጠንካራ የመልካም አስተዳዳር ተቋማዊ ሁኔታዎች ወይም ከፍተኛ መርሆዎች ትግበራ ላይ ናቸው ያሉት፡፡
- **አማካይ ዉጤት 2.9 እና 2.0 መካከል ከሆነ**= የመልካም አስተዳደር ተቋማዊ ሁኔታዎች ደካማ ወይም ወደ መጥፎ ለመቀየር እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡
- **አማካይ ዉጤት 1.9 እና 1.0 መከከል ከሆነ** = የመልካም አስተዳደር ተቋማዊ ሁኔታዎች በጣም ደካማ ደረጃ ላይ ነው፡፡

## የክፍል ሦስት ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል መልካም አስተዳደር በማስፈን ሂደት የሚገጥሙ ዋነኛ ተግዳሮቶች ፣ መልካም አስተዳደርን ለመገንባት መከናወን ስለሚገቡ ጉዳዮች እና በመልካም አስተዳደር ግንባታ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው እና ቁልፍ ተዋናዮችን የሚመለከቱ ትምህርቶች በስፋት ተብራርተዋል፡፡ መልካም አስተዳደር በመገንባት ሂደት እንቅፋት ከሚሆኑ ተግዳሮቶች መካከል ዋነኛው የመንግሥትና የፖለቲካ መሪዎች የመልካም አሰተዳደር መርሆዎችን በተሟላ መልኩ ለመተግበር ቁርጠኛነት ማነስ ወይም አለመኖር ነው፡፡ የበርካታ ታዳጊ አገሮች መልካም አስተዳደር ግንባታ እንቀፋት አስተዳደራዊ ለዉጦችን አሰራሮችን ለመተግበር የፖለቲካ ባለሥልጣናትና ሌሎች አካላት ቁርጠኝነት አለመኖር ነው፡፡ በተመሳሳይ የህዝብ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ለመመለስ የቴክኖሎጂና በቂ የሀብት አቅርቦት ያለመኖር እና የሰው ኃይልና የተቋማት አቅምና ብቃት ማነስ ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ሌላው እንቅፋት ነው፡፡ ከዚህ

በተጨማሪ ቀልጣፋና ውጤታማ ቢሮክራሲ አለመኖር፣ የሙስናና ብልሹ

አሰራር መስፋፋት፣ ህብረተሰብንና ባለድርሻ አካላት በልማትና በማህበራዊ ጉዳዮች በስፋት አለማሳተፍ እና በአካባቢ መስተዳደርና በመንግስት ተቋማት አስተዳደራዊ ሥራዎችና ውሳኔዎች ላይ ጣልቃገብነት መኖር በመልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት እንቃፋት የሚሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡

እነዚህን ተግዳሮቶች አልፎ መልካም አስተዳደርንለመገንባት ግልጽነትና ተጠያቂነት፣ ፍታሃዊነትና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ነፃና ጠንካራ ተቋማትን መገንባት፣ የዜጎችን የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን በብቃት ለመመለስ የሚያስችሉ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን ማውጣት፣ ማሻሻልና ተግባራዊ ማድረግ፣ ህዝብ በመንግሥት ፖሊሲዎች፣ የልማትና ማህበራዊ ፕሮግራሞች እንዲሳተፍ ማስቻል፣ ሙስናን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችሉ ሥራዎች መስራት፣ ጠንካራ የሲቪክ ማህበራት እና የሚዲያ ተቋማት መገንባትና ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም መልካም አስተዳደር እውን ለማድረግ የህብረተሰቡን ደህንነትን መጠበቅ፣ ለብዝሃነት እዉቅና መስጠት፣ የአካባቢ አስተዳደረን አቅም ማሻሻል፣ ያልተማከለ አስተዳደር መዘርጋት የግድ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ የመልካም አስተዳደር ግንባታ የሚሳካዉ መንግስት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በዘላቂ ልማትና የዜጎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት መረጋገጥ ላይ ከፍተኛ ቁርጠኝነት ያለው ሲሆን ነው፡፡ መልካም አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ ተጠያቂነትን፣ ያልተማከለ አስተዳደርንና የህዝብ ተሳትፎ ማጠናከር፣ውጤታማነትን፣ የህግ የበላይነትን ማስፈን እና ሙስናን መቆጣጠር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በመልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት ሦስት ዋነኛ ተዋናዮች አሉ፡፡ እነርሱም መንግሥት፣ የግሉ ሴክተርና ሲቪክ ማህበረሰብ ናቸው፡፡ የእነዚህ ሦስት አካላት የእርስ በርስ ግንኙነትና መስተጋብር የአስተዳደር ስነ-ምህዳር ሁኔታን የሚመለከት ነው፡፡

- መንግስት በመልካም አስተዳደር ግንባታ በሦስቱ የመንግስታ አካላት ምቹ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና የህግ አካባቢን የመፍጠር ሚና ይጫወታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መንግሥት ግልጽነትና ተጠያቂነት የሚያረጋግጡ መንግሥታዊ አሰራሮችን በመዘርጋት፣ የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ደህንነት፣ የልማት ተሳትፎና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ህጎችንና ፐሊሲዎችን በማውጣት መልካም አስተዳደርርን በመገንባት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡

- የግሉ ዘርፍ የልማቱ አንቀሳቃሽ በመሆን የስራ ዕድል ለመፍጠር፤የስራ ፈጠራ ክህሎትን ማዳበር፤የገቢ ማስገኛ ዕድሎችን ማጎልበት፤እና ለህብረተሰቡ የፍጆታ እቃዎችን በማቅረብ ሚና ይጫወታል።የግሉ ዘርፍ በመንግስት ሊከናወኑ የማይቻሉ የልማት ሥራዎች ላይ ኢንቨስት በማድረግ ፍትሃዊ የኢኮኖሚ እድገትና ልማት እንዲዳርስ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲስፋፋ በማገዝ ለመልካም አስተዳደር መስፈን ጉልህ ሚና ይጫወታል።
- የሲቪል ማህበረሰቡ ህዝብን በማስተማር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ዴሞክራቲክና ሰብአዊ መብቶቻቸውን እንዲያውቁና እንዲያስከብሩ በማድረግ እንዲሁም የመንግስትንና የግል ተቋማትን አሠራር በመከታተል በማጋለጥና ተጽእኖ በመፍጠር የማስተካከል ሥራ በማሥራት ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ድጋፍ ያደርጋሉ።
- መገናኛ ብዙሃን መረጃ በመስጠት፣ በማስተማርና ግንዛቤ በመፍጠር እንዲሆም ብልሹ አሰራሮችን በማጋለጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ሚዲያ ሚናውን ለመጫወትና ሃላፊነቱን ለመወጣት ነጻና ከመንግስት ቁጥጥር እና ተጽእኖ ነጻ ሊሆን ይገባል።

# ምእራፍ ሁለት

## 2. ሥነ ምግባርና መልካም አስተዳደር

### የምእራፍ ሁለት ዋና ዋና ይዘቶች

*መልካም አስተዳደር ስንል ህዝባዊ ተቋማት የዜጎችን ፍላጎት መሰረት አድርገው ህዝባዊ ጉዳዮችን የሚያስተናግዱበት እና ተልእኮዋቸውን እንዲወጡበት በአደራ የተሰጣቸው ሃብት ወይም የሚያስተዳድሩበት ዘይቤ ነው፡፡ ተቋማት የቱንም ያህል ገንዘብ ቢመደብላቸው፣ ግብአት ቢሟላላቸው፣ በሰለጠነ የሰው ሃይልም የተደራጁ ቢሆኑ ያለ ሥነ-ምግባር መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ አይችሉም፡፡ ሥነ-ምግባር ጥሩውንና መጥፎውን ተግባር የምንለይበትና መጥፎውን ትተን ጥሩውን የምንከተልበት መለኪያ ነው፡፡ ወጤቱም የሰው ልጅን ኑሮ ደህንነት ማረጋገጥ ነው፡፡ ሰዎች በህብረተሰብ ውስጥ አብረው ሲኖሩ ገና ከቤታቸው ሲወጡ ጀምሮ በተለያዩ ጉዳዮች ከተለያዩ ሰዎች ጋር ይገናኛሉ፡፡ ግንኙነታቸው የሰመረ እንዲሆን ስነ-ምግባር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም በአንድ ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ሰዎችም ከአለቆቻቸው፣ ከስራ ባልደረቦቻቸው፣ ከባለጉዳዮቻቸው ጋር ይገናኛሉ፡፡ ከነዚህ አካላት ጋር በምን አይነት ባህርይ እና ሁኔታ መገናኘት እንደሚገባቸው ውጤታማ ተግባር እንዲያከናውኑ የሚመራቸው ሥነ-ምግባር ነው፡፡ ግንኙነታቸው የሰመረ እንዲሆን የሚያደርገው የሚከተሉት ሥነ-ምግባር ነው፡፡ ሥነ-ምግባር አንድን ተግባር ጥሩ ወይም መጥፎ ለማለት ምክንያታዊ የሆኑ ማስረጃዎችን ያቀርባል፡፡ ከዚህ ባሻገርም በህዝባዊ ተቋማት ያሉ ሰራተኞች ሥራቸውን ሲሰሩ በሀቀኝነት እንዲሰሩና ከአድሎ የጸዳ ፍትሃዊ፣ቀልጣፋ፣ ብቁና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ፣ አገልግሎት የማግኘት መብታቸው ተከብሮ፣ በአክብሮትና በትህትና ተስተናግደው ለጠየቁት አገልግሎት ፈጣንና ተገቢ ምላሽ እንዲሰጣቸው ለማድረግ ስነ-ምግባር ከፍተኛ ድረሻ እና አስዋፅዖ ነው፡፡*

*አንዳንድ ሰዎች ሥነ-ምግባር ህግ ውስጥ ያሉትን ነገሮች መፈጸም ነው ይላሉ፡፡ ይሁንና በለት ተለት ኑሮ ውስጥ የሰው ልጅ የሚያጋጥመው ነገር ሁሉ በህግ ውስጥ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፣ ተዘርዝሮ ቢያልቅ እንኳ መልካም ስነ-ምግባር በሌለበት ህግ ብቻውን ፋይዳው ብዙም አይደለም፡፡ በመሆኑም አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ህዝባቸውን ለማገልገል የተረከቡትን ግብአቶች በአግባቡ ለታለመለት አላማ እንዲያውሉት እንዲሁም የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ እንዲገለገሉበት የሥነ-ምግባር ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡*

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ስለ ስነ-ምግባር ምንነት፤ ስነ-ምግባርና መልካም አስተዳደር ያላቸው ትስስር፤ ሥነ-ምግባር ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያለው ፋይዳ በተለያዩ ንኡሳን ክፍሎች ይቀርባል፡፡

## የምእራፉ ዓላማ

የዚህ ምእራፍ ዓላማ ሠልጣኞች በሥነ-ምግባር እና በመልካም አስተዳደር መካከል ያለውን ትስስር እንዲሁም ሥነ-ምግባር ለመልካም አስተዳደር የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ አስመልክቶ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግና ክህሎታቸውን በማዳበር፣በሚሰሩበት የሥራ መስክ የሚጠበቅባቸውን የሥነ-ምግባር ደረጃ በመጠበቅ ሥነ-ምግባር የተላበሰ አገልግሎት ለዜጎች እንዲሰጡና መልካም አስተዳደርን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሰርት የምዕራፉ ዝርዝር ዓላማዎችም፤

- የሥነ-ምግባር ምንነትን ያስረዳሉ፤
- የሥነ-ምግባር እና የመልካም አስተዳደርን ትስስር ያብራራሉ፤
- የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦችና ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸውን እንድምታ ይመረምራሉ፤
- የሥነ-ምግባር ደንቦች እና መልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸውን ፋይዳ ያስረዳሉ፤
- ሥነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው መልካም አስተዳደርን የማያበላሹ ሥነ- ምግባራዊ ውሳኔዎችን ይወስናሉ፤

# ክፍል አንድ

## 2.1 የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦችና መልካም አስተዳደር ትስስር

### የክፍል አንድ አጭር መግለጫ

*ሥነ-ምግባር በምክንያት የተደገፈ መልካም ውሳኔ መወሰን ወይም መምረጥ ነዉ፡፡ የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ደግሞ ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ በማየት አሳማኝና ጠንካራ ምክንያትን ለመስጠት የሚያስችሉ የሥነ-ምግባር ማእቀፎች በመሆናቸዉ፣ በመንግስት ተቋማት ሚወሰኑ ውሳኔዎች የህዝብን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ አስተዋጽዋቸው ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦችን እና የመልካም አስተዳደር ትስስር በተመለከተ በዚህ ትምህርት ክፍል ቀርቧል፡፡*

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

*የሥልጠናው ተሳታፊዎች ከክፍል ሁለት ትምህርት በኋላ:*

- ☞ *ዋና ዋና የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ምንነት ያብራራሉ፤*
- ☞ *የሥነ-ምግባር እና የመልካም አስተዳደር ትስስርን ያብራራሉ፤*
- ☞ *የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች መልካም ሥነ-ምግባር ለመገንባት ያላቸውን እንድምታ ይገመግማሉ፤*
- ☞ *ሥነ-ምግባር ለመልካም አስተዳደር ያለውን ፋይዳ ይዘረዝራሉ፤*
- ☞ *የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ይለያሉ፤*

### የመነሻ ተግባር 2. 1

1. ሥነ-ምግባር ሲባል ወደ አእምሮአችሁ ቀድሞ የሚመጣው ነገር ምንድን ነው?
2. ሥነ-ምግባር ማለት የማምነው እምነት ወይም ሃማኖቴ መልካም ናቸው ብሎ ያዘዘኝን በተግባር መፈጸም ነው በሚለው ሃሳብ ላይ ምን አስተያየት አላችሁ? በእናንተ አስተያየትስ ስነ-ምግባር ምን ማለት ነው?
3. አንድ ሰው 12ቱን የሥነ-ምግባር መርሆዎች በደንብ ስለተነተነ ስነ-ምግባር አለው ማለት ይቻላል?

4. ያለ ሥነ-ምግባር መልካም አስተዳደር ማረጋገጥ ይቻላል?
5. ሥነ-ምግባር መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

ሥነ-ምግባርና ምግባር በዕለት ተዕለት ህይወታችን አዘወትረን የምንሰማቸው በጣም የተለመዱ ቃላት ናቸዉ፡፡ ከዚህ የተነሳ አንዳንድ ጊዜ እነዚህን በጣም የተለመዱ ቃላት የያዙትን ጽንሰ ሃሳቦች በተሳሳተ መንገድ ልንረዳ እንችላለን፡፡ ሥነ-ምግባር አንድን ተግባር ወይም ድርጊት መልካም እና መጥፎ ብለን ምክንያታዊ (Rational) በሆነ ዘዴ ለመለየት የምንገለገልበት መለኪያ ነው፡፡ እንደ ውሸት ወይም ስረቆት ያሉ ድርጊቶች ትክክል ወይም ስህተት የሚያደርጋቸዉ ነገር ምንድን ነው? እና ማንኛዉንም ድርጊት ጥሩ ወይም መጥፎ የሚያደርገዉ ምንድን ነዉ? የሚሉት ጥያቄዎች ሥነ-ምግባራዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በምንሰጠው መልስ የሚገኘው ውጤት ደግሞ በሰዎች የኑሮ ህይወት ውስጥ በመልካምም ሆነ በመጥፎ ይገለጣል፡፡ ሥነ-ምግባር በግላችን ምን ዓይነት ባህርይ ማሳየት እንዳለብን፣ በአንድ ተቋም ውስጥ እንዴት ባለ ሁኔታ ስራችንን መስራት እንዳለብን፣ ከውስጥ ሰራተኞችና ከውጭ ደንበኞች ጋር እንዴት ባለ ሁኔታ መገናኘት እንዳለብን፣ በህብረተሰብ ውስጥ ስንኖር እንዴት መመላለስ እንዳለብን ይጠቁመናል፡፡ ሥነ-ምግባር አንዱ ሌላውን ሳይጎዳ ሊኖር የሚችልበትን መንገድ ይጠቁማል፣ አንድን ተግባር ለማከናውን ትክክለኛው መንገድ የቱ ነው? ወይም” what is the right thing to do?” የሚለውን ጥያቄ መመለሻ መንገድ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች የስነ- ምግባር ምንነትን ሲያስረዱ መልካምና ጥሩውን የምንለይበት መንገድ መሆኑን ብቻ ይጠቁማሉ፣ ወይም ደግሞ የተዘረዘሩ የሥነ-ምግባር ደንቦችን በደንብ ተንትኖ ማስረዳት መቻል ይመስላቸዋል፣ ይሁንና ስነ-ምግባር የመለየት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን መልካም ሆኖ የመገኘትም ጉዳይ ነው፡፡ (“The purpose of ethics is to become good, not merly to know” Aristotle).

በመሆኑም በአንድ ተቋም ያለ አንድ ሰራተኛ በተቋሙ ያሉ የሥነ-ምግባር ደንቦችን ማወቁ ወይም ደግሞ ተቋሙ በየቦታው የሥነ-ምግባር ደንቦችን መለጠፉ ስነ-ምግባር ያለው አገልግሎት እየተሰጠ ነው ማለት አያሰኝም፡፡ መልካም አስተዳደር ለህዝብ ጥያቄ እና ፍላጎት ተገቢ ምላሽ መስጠት እንዲሁም የተረከቡትን ግብአቶች በአግባቡ ለህዝብ ጥቅም ማዋል እንደ መሆኑ ሥነ-ምግባር በአንድ ተቋም መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

መልካም አስተዳደር ሲረጋገጥ ታክስ ከፋይ ዜጎች በመልካም ስነ-ምግባር የመስተናገድ መብታቸው ይረጋገጣል፡፡ በተቋሙ ያለው የስራ አካባቢም ምቹ ከመሆኑ የተነሳ የተቋሙ ተገልጋዮች በሰራተኞች ላይ እምነት እንዲጨምሩ ያደርጋል፡፡ በመልካም ስነ-ምግባር የተገነቡ የመንግስት ሰራተኞች የሚያስተዳድሩት ወይም የሚጠቀሙበት ሪሶርስ ባላደራዎች በመሆናቸው ባግባቡ እንዲጠበቁ ያደርጋሉ፡፡ ከታክስ የሚገኘው ገንዘብ ትክክለኛ እና የህዝብን ፍላጎት በሚመልሱ አገልግሎቶችና የልማት ስራዎች ላይ እንዲውሉ ይሆናል፡፡ በመልካም ስነ-ምግባር የተገነቡ ሰራተኞች እጃቸው ከሙስና የጸዳ ስለሚሆን እና የሚያደርጉት ተግባር ሁሉ የህብረተሰብን ፍላጎት ለሟሟላት ስለሆነ የሚሰሩትን ስራ ለህዝብ ይፋ ወይም ግልጽ ለማድረግ ይፈቅዳሉ፡፡ ለሚጠየቁትም ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ይሆናሉ፤ በዚህም ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡

**መልመጃ 2.1**

**አመቻቹ በሚነግሯችሁ መሰረት ቡድን መስርቱ፤ ከዚያም ቀጥሎ የቀረበላችሁን ኬዝ በመመርመር ከግርጌው ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

**ኬዝ 1**

በአንድ ተቋም ውስጥ በውጭ ተገልጋዮች ዘንድ በመልካም ሥነ-ምግባራቸው የተመሰከረላቸው አቶ ክንዴ የተባሉ አገልግሎት ሰጪ በየአውድ አመቱ ከአንዳንድ ተገልጋዮቻቸው ለሚያሳዩት መልካም ሥነ-ምግባር እውቅና ለመስጠት ሲባል ሙክቶች ይመጡላቸዋል፣ ይህም ከእለት ወደ እለት ለአገልግሎት ፈላጊዎች የሚሰጡት አገልግሎት በመልካም ስነ-ምግባር መሆኑን እንዲጨምር አድርጎታል፡፡

1. አቶ ክንዴ ስጦታውን መቀበላቸው መልካም ነው ወይስ መጥፎ? ለምን?
2. ይህ አይነቱ ተግባር በተቋሙ መልካም አስተዳደር ላይ በአውንታም ይሁን በአሉታ የሚያሳርፈው ተጽእኖ ይኖራል?
3. እንዲህ አይነት ተሞክሮ ካለ ለሌሎች ተሳታፊዎች አቅርቡ?

**መልመጃ 2.2 የማጠቃለያ ጥያቄ**

1. ሥነ-ምግባር ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያለውን አስተዋጽኦ ምሳሌ እያቀረባችሁ አስረዱ?
2. የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች  መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ እንዴት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ?

የመንግስት ሃላፊዎች የሚወስኑት ውሳኔ የሚመሩበት መርህ ሆኖ እንዲያገለግላቸው ሥነ- ምግባር ያስፈልጋቸዋል፡፡ የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ደግሞ የስራ ሃላፊዎች የሚወስኑትን ውሳኔ ከተለያየ አቅጣጫ አይተው እንዲወስኑ ያግዟቸዋል፡፡ የህዝብ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ አገልግሎት ለመስጠት፣ ከህዝቡ የተሰበሰበውን የታክስ ገንዘብ፣ በእርዳታና በብድር የተገኘውን ገንዘብ ህዝብን በሚጠቅም ልማት ላይ ለማዋል፣ የሚታቀዱ እቅዶችና የሚወሰኑ ውሳኔዎች የህዝብን ፍላጎት መሰረት ያደረጉና ፍትሃዊ እንዲሆኑ ማመዛዘንን ይጠይቃል፡፡ የስነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ደግሞ ጠቃሚ የሚባሉ ጉዳዮችንና ውሳኔዎችን ለመወሰን ሁኔታዎችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማየት እንደ ማእቀፍ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ንድፈ ሃሳቦቹን አውቀው ውሳኔውን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በማየት መወሰን ደግሞ መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች እንደ መርህ ሆነው በበርካታ ጉዳዮች ላይ ማንኛውንም ድርጊት ለመገምገም ይጠቅማሉ፡፡ የህዝባዊ ተቋማትም በህብረተሰቡ የእለት ተለት ህይወት ላይ የራሳቸው እንድምታ የሚኖራቸውን የተቋም እሴት ለመቅረጽ የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ሶስቱን የሥነ ምግባር ንድፈ ሃሳቦች (ዩትሊታሪያን፣ ዲኦንቶሎጂን እና ቨርቹ ኤቲክስን) ምንነት እና በተቋማት ውስጥ ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸውን ጠቀሜታ እናያለን፡፡

- **ዩትሊታሪያን:** የዩትሊታሪያን መርህ አራማጆች የማንኛውም ተግባር መልካምነት የሚመዘነው በውጤቱ ነው፡፡ ይኸውም የአንድ ተግባር መልካምነት የሚዳኘው ውጤቱ ለብዙሃኑ ትልቅ የደስታ ምንጭ በመሆኑ ነው ይላሉ፡፡ ዩትሊታሪያን የበለጠ መልካም ነገር የቁጥር ብልጫ ላለው የሚለው መርህ ለአንድ የመንግስት ተቋም የሥራ ሃላፊ እጅግ ጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ አንድ የመንግስት ተቋም ሃላፊ የሚወስነው ውሳኔ ሰፊው ማህበረሰብ ላይ የራሱ እንድምታ ስለሚኖረው ውሳኔዎች ህብረተሰብን የሚጠቅሙ ስለመሆናቸው ንድፈ ሃሳቡ እገዛ ያደርጋል፡፡ በዚህም ከህዝብ የተሰጣቸውን አደራ እና ሪሶርስ ሰፊውን ህብረተሰብ እንዲጠቅሙ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ እንደ አንድ ስነ-ምግባራዊ ውሳኔ መስጫ ማእቀፍ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ዩትሊታሪያን ንድፈ ሃሳብ የመንግስት አስተዳደር የህብረተሰብን ፍላጎት ለማሟላት ሃላፊነት እንዳለበት ምክንያታዊ ትንታኔ እንዲቀርብ ይጋብዛል፣ በተጨማሪም የዩትሊታሪያን ንድፈ ሃሳብ የህዝብን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ስራዎች በዘፈቀደ ሳይሆን እንደ አስፈላጊነታቸው

**በቅደም ተከተል**

በመተግበር ውጤታማ ስራን ለመስራት እንደ መርህ ሆኖ ያገለግላል፤ በዚህም መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

በህዝብ ተቋማት ስራዎች ውስጥ የዩትሊታሪያን ንድፈ ሃሳብ ተግባራዊ ከሆኑባቸው አሰራሮች መካከል ወጪና የሚገኝ ጥቅምን ማነጻጸር (cost-benefit analysis) የሚባለው አሰራር ነው፡፡ በዚህም የሚወሰኑ ውሳኔዎች በሙሉ በሰፊው ህዝብ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ የሚገመገምበት መርህ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ የዩትሊተሪያን መርህን ብቸኛ አማራጭ አድርጎ ማለትም ውሳኔዎቹ የሚያስከትሉትን ወይም የሚያመጡትን ውጤት ብቻ መሰረት አድርጎ መወሰን የሚያስከትላቸው የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖም ሊኖራቸው እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጉዳይ በተለይ ስነ-ምግባራዊ ውሳኔዎች በውሳኔው ምን ያህሉን ሰው እንደጠቀመ ወይም እንዳስደሰተ በትክክል በቁጥር ማስቀመጥ ስለማይቻል ነው፡፡ ሌላው በተለይ በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት የጥቂቱን መብት ስለሚደፈጥጥ መርሁ ብቻውን ተግባራዊ ቢደረግ ፍትሃዊነትን ሊያዛባ ይችላል፡፡

☞ **ዲኦንቶሎጂ:** የዚህ መርህ ሀሳብ የአንድ ተግባር መልካምነት የሚወሰነው ውጤቱ ምንም ይሁን ምንም ድርጊቱ አንድ የሞራል ስታንደርድን ተከትሎ በመሰራቱና ባለመሰራቱ ነው፡፡ እንደ ዲኦንቶሎጂ መርህ አራማጆችን መርህን መሰረት ያደረገ ስነ-ምግባር ወይም rule based ethics ይሏቸዋል፡፡ አንድ ተግባር ትክክለኛነቱ የሚረጋገጠው የሚሰራው ስራ ለመሰራቱ ተገቢ ነው ተብሎ ሲታመንበት ብቻ ነው፡፡ (an act should be chosen simply because it is the right thing to do)፡፡

ዲኦንቶሎጂ የሞራል ደረጃዎችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ የተመሰረተ መርህ ነው፡፡ አንድ የተቋም ሃላፊ የሚያደርገው ድርጊት ወይም ሃሳብ የሚያስገኘው ውጤት ምንም ይሁን ምን እተገብረዋለው ብለው ቃል ለገቡላቸው የሥነ-ምግባር መርሆች ታማኝ ሆነው መተግበር እንዳለባቸው ትኩረት የሚሰጥ መርህ ነው፡፡ ስለዚህ የተቋማት ሃላፊዎች ትኩረታቸው በተቋማቸው እሴት ላይ ነው፡፡ ዲኦንቶሎጂ በህዝባዊ ተቋማት ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች የሚወሰኑ ውሳኔዎች የተቀረጹ የሞራል ደረጃን መሰረት ያደረጉና ለሁሉም ወጥ የሆነ አገልግሎት በመስጠት በየደረጃው ያሉ የሥራ ሃላፊዎችም

ስልጣናቸውን እንደ ፈለጉ እንዳይገለገሉበት የስነ-ምግባር ደረጃን በማውጣት መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

የዲኦንቶሎጂ መርህ የስነ-ምግባር ደንብና መመሪያን የማዘጋጀት እና የመተግበር እንድምታ አለው፡፡ ይሁንና በሮዎች ውስጥ በሚታዩ ለአሰራር ምቹ ሁኔታ አለመኖር ምክንያት ዲኦንቶሎጂ መርህን በተቋማት ተግባራዊ ማድረግ ሊያስቸግር ችላል፣ በመሆኑም የስነ-ምግባር ደንቦችን ማውጣት ተገቢ መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ሰራተኛውን በባህሪ ለመቅረጽ ስልጠናም ተገቢ ስለሆነ ሁሉንም የስነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች እንደየሁኔታው በማቀናጀት ተግባራዊ ማድረግና ለመልካም እስተዳደር መረጋገጥ የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ ይገባል፡፡

አንዳንድ ባለሞያዎች የዲኦንቶሎጂ ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ የሚወጡ የሥነ ምግባር ደረጃዎች እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ወይም የሚቃረኑ እሴቶች ሊከሰት እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ግጭቶች ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንቅፋት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ የውጤታማነት እሴት ከተጠያቂነት እሴት ጋር ሊጋጭ የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ እንደነዚህ አይነት ሁኔታዎች ለስነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታ (dilemma) ያጋልጣሉ፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ ውስብስብ መሆንም እና የተገልጋይ ፍላጎት ማደግ በተመረጡት የስነ-ምግባር ደረጃዎች መካከል ግጭቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናሉ፡፡

☞ **ቨርቹ፡** ቨርቹ የሚባለው የስነ-ምግባር ንድፈ ሃሳብ ደግሞ ትኩረቱ በአንድ ተግባር የመጨረሻ ውጤቱ ወይም በስነ-ምግባር ስታንደርድ ላይ ሳይሆን በሰዎች ባህሪ ላይ ነው፡፡ ቨርቹ ኤቲክስ ትኩረቱ መልካም ስነ-ምግባር ያላቸው ሰዎች መልካም ነገርን መስራት ይችላሉ ብለው ያምናሉ፤ በመሆኑም ትኩረታቸው ሰውየው ላይ ነው፡፡ የሰውየው ተግባር በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ የሚሰራው ስራ ውጤቱ ብዙዎችን የሚያስደስት ይሁን ወይም ደግሞ በመርህ ላይ ተመስርቶ የተፈጸመ መልካም የሞራል እሴቶችን የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ የቨርቹ ኤቲክስ ንድፈ ሃሳብ (መርህ) በመንግስት ተቋማት ተግባራዊ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ ቨርቹ ኤቲክስ ትኩረት የሚያደርገው በፈጻሚው የባህርይ (ሥነ-ምግባር) ላይ ነው፡፡ በህዝባዊ አገልግሎት ውስጥ ስነ-ምግባራዊ የሆኑ ውሳኔዎች የሚወሰኑት የሚከናወኑ ተግባራት በሚያስከትሉት ውጤት ወይም በተነደፉ የስነ-ምግባር ደረጃዎች ሳይሆን

በፈጻሚው ባህርይ እና ስነ-ምግባር ላይ ነው፡፡ ስለዚህ የተቋሙ ትኩረት በስነ-ምግባር ስልጠና ላይ ሆናል ማለት ነው፡፡

**መልመጃ የመውያያ 2.3**

**አመቻቹ በሚነግሯችሁ መሰረት ቡድን መስርታችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡**

1. የዩትሊታሪያን መርህን መሰረት በማድረግ በሚዲያ የሚነገሩ የሲጋራ ማስታወቂያዎችን (ለመንግስት ከሚያስገኙት የኢኮኖሚ ጥቅም እና ህብረተሰቡ ላይ ከሚያደርሰው የጤና ጉዳት አኳያ) ገምግሙ፡፡
2. የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያዎችን የሚገድበው አዋጅን ለማውጣት የዩትሊታሪያን መርህ ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋጽኦ አስረዱ፡፡
3. በሙስኞች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ከዩትሊታሪያን መርህ አንጻር ተገቢነታቸው ላይ ተወያዩ፡፡
4. በአንድ ተቋም ያለ አንድ ሃላፊ የዩትሊተሪያን አራማጅ ቢሆንና የሚወስናቸው ውሳኔዎች በሙሉ በዚህ መርህ ላይ የተመሰረተ ቢሆን በተቋሙ ላለው መልካም አስተዳደር አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽእኖ ተወያዩ፡፡
5. የቨርቹ እና የዲኦንቶሎጂ ሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳብ ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ምሳሌ በማቅረብ አስረዱ፡፡

## የክፍል አንድ ማጠቃለያ

*ሥነ-ምግባር በምክንያት የተደገፈ መልካም ውሳኔ መመወሰን ወይም መምረጥ ነው፡፡ የስነ- ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ደግሞ ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ በማየት ውሃ የሚቋጥር ምክንያትን ለመስጠት የሚያስችሉ የስነ-ምግባር ማእቀፎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በመንግስት ተቋማት የሚወሰኑ ውሳኔዎች የህዝብን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ የሥነ-ምግባር ንድፈ ሃሳቦች አስተዋጽኦዋቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ሥነ- ምግባር ምልካም እና መጥፎ ድርጊት ወይም ባህርይ የምንለይበት መስፈርት ወይም መለኪያ ነው፡፡ ይሁንና ሥነ-ምግባር መልካም እና መጥፎ የሆነውን ባህርይ የመለየት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፤ መልካሙን የመምረጥና የመተግበር ጉዳይም እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ መልካም አስተዳደር ህዝባዊ ጉዳዮችን እንዴት ባለ ሁኔታ የምንመልስበት እንዲሁም የህዝብን ሪሶርስ*

በምን አይነት ሁኔታ የምናስተዳደርበት ዘይቤ በመሆኑ ያለ መልካም ስነ-ምግባር መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በመልካም ሥነ-ምግባር የተገነባ አገልግሎት ሰጪ ለህብረተሰቡ መብቱ የሆነውን አገልግሎት ያለ አድልዎ በከፍተኛ የስነ-ምግባር ደረጃ ያቀርብለታል፤ ለሚጠይቀው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ይሰጠዋል፤ ለልማትና ለህዝባዊ አገልግሎት የተመደበለትንም ገንዘብ ከሙስናና ከምዝበራ በጸዳ መንገድ በአግባቡ ጥቅም ላይ ያውላል፡፡ እነዚህ እና እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮች የሥነ-ምግባር እና የመልካም አስተዳደርን ትስስር አጉልተው ያሳዩናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2.2 የሥነ- ምግባር መርሆዎችና መልካም አስተዳደር

### የክፍል ሁለት አጭር መግለጫ

የሥነ-ምግባር መርሆዎች ለድርጊት መመሪያ እንደመሆናቸዉ መጠን እሴቶችን ለመተግበርና የአገልጋዩ ባህሪ ለአገልግሎት አሰጣጡ የሚመጥን እንዲሆን ያደረጋሉ፡፡ በአንድ ህዝባዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር መርሆዎች ማዋቀሪያ አምዶች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል የሥነ-ምግባር መርሆዎችና መልካም አስተዳዳር፣የመርሆዎች ማዋቀሪያ አምዶች፣ የሥነ-ምግባር ደንብን እንዲሁም የሥነ-ምግባር ደንቦች ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸው ጠቀሜታ በተመለከተ በአራት የትምህርት ይዘቶች ቀርቧል፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

የሥልጠናው ተሳታፊዎች ከክፍል ሁለት ትምህርት በኋላ:

- የሥነ-ምግባር መርሆዎች ምንነትን ያስረዳሉ፤
- ሥነ-ምግባር መርሆዎችን ለመቅረጽ መነሻ የሆኑ ቁልፍ ጉዳዮችን ያብራራሉ፤
- የሥነ-ምግባር መርሆዎች እና መልካም አስተዳዳር ያላቸውን ትስስር ያረጋግጣሉ፤
- የሥነ-ምግባር መርሆዎች ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያለውን ፋይዳ ያብራራሉ፤
- የሥነ-ምግባር ደንቦች ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸውን አስተዋጽኦ ያስረዳሉ፤
- ለሥነ-ምግባር ደንብ መተግበር ቁርጠኝነታቸውን ያሳያሉ፤

**የመነሻ ተግባር 2.3**

1. የሥነ-ምግባር መርሆዎች ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?

## ትምህርት አንድ

## 2.2.1 የሥነ ምግባር መርሆዎች

የሥነ-ምግባር መርሆዎች በአንድ ድርጅት ወይም ተቋም ውስጥ ያሉ ሰዎች ለጋራ ደህንነትና ጥቅም ሲሉ ተስማምተው የሚቀርጹዋቸው የሥነ-ምግባር መመሪያዎች ናቸው፡፡ በሥነ-ምግባር ደንብ ውስጥ የሚገለጹት እነዚህ መርሆዎች ዲሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ ምርታማነትን ለመጨመርና ለመሳሰሉት ጉዳዮች ይጠቅማሉ፡፡ የሥነ- ምግባር መርሆዎቹ ተቀርጸው በየግድግዳው መለጠፋቸው ብቻ ትርጉም የለውም፤ በመሆኑም ደንቦቹን በተለያየ መንገድ ከስራና ከሙያ ጋር በማስተሳሰር ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል፡፡

የሥነ-ምግባር መርሆዎች ለድርጊት መመሪያ ናቸው፡፡ ስለሆነም እሴቶችን ለመተግበርና የአገልጋዩ ባህሪ ለአገልግሎት አሰጣጡ የሚመጥን እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ ለጋራ ጥቅም ሲባል ለሚሰጥ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ጥረቶች እና ጽናትን ለመደገፍ የሚችል የመነሳሳት ምንጭም ናቸው፡፡

ህዝባዊ አገልግሎት ሰጭዎች በብልሹ አሰራሮች ዉስጥ ሊያገኙት ከሚችሉት ቁሳዊ ጥቅም ይልቅ ለሥነ-ምግባር መርሆዎች ተገዥ የሚሆኑበትን ጉልበት ይሰጣቸዋል፡፡ የሥነ-ምግባር መርሆዎች የዉሳኔ አሰጣጥ መመሪያዎች ይሆኑ ዘንድ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት አለባቸዉ፡፡

- **የሥነ-ምግባር መርሆዎች ጠቅለል ያሉ መሆን አለባቸው፡** የሥነ-ምግባር መርሆዎች ጠቅለል ባለ ሁኔታ መገለጽ አለባቸው፡፡ ጠቅለል ብለው በመቀመጣቸው በቀላሉ የሚታወሱ አተገባባራቸዉም ዘለቄታ ያለው ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ ጠቅለል ብለው በሚቀመጡበት ጊዜ በተወሰኑ ግለሰቦች ወይም ማህበሮች ሁኔታ ብቻ የተወሰኑ መሆን እንደ ሌለባቸው ማረጋገጥ ይገባል፡፡ በመሆኑም እነዚህን መሰረታዊ መርሆች ለመረዳት ከተወሰኑ ግለሰቦች ጋር ትዉዉቅ ማድረግን ወይም የግለሰብ ወይም ማህበራትን እንደማጣቀሻ መውሰድ አያስፈልግም፡፡ የመርሆዎቹ አቀራረጽም በአንድ ወቅት ያለ የማህበረሰብን ክፍል ብቻ ያማከለ ሳይሆን መጪውንም ትውልድ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህም መርሆዎቹ ዘመን ተሻጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ መርሆች ማህበረሰብን ዘላቂነት ባለዉ ሁኔታ ማገልገል መቻል አለባቸው፡፡

- **የሥነ-ምግባር መርሆዎች በሰዎች ስብእና ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡** የሥነ-ምግባር መርሆዎች ለሁሉም የሞራል ስብዕና ያለው ሰዉ የሚሰሩ መሆን አለባቸዉ፡፡ እነሱን ለመተግበር ከሰው ልጅ ሥነ-ምግባራዊ ባህርይ ወጣ ያለ ባህርይን የሚጠይቁ መሆን የለባቸውም፡፡ የሚመረጡት እሴቶች ወይም መርሆዎች በማንኛውም ጠንካራ ስብዕና ያለው ሰዉ ለመተግበር የተዘጋጁ መሆን አለባቸው፡፡
- **የሥነ-ምግባር መርሆዎች በይፋ የሚታወቁ እና ተቀባይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡** የስነ-ምግባር መርሆዎች በህዝብ የሚታወቁና በተደጋጋሚ የህዝብ ምርመራ እና ክርክር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡
- **የሥነ-ምግባር መርሆዎች እርስ በእርሳቸው በሚጋጩ ጉዳዮች ላይ ቅደም ተከተል መስጠት አለባቸው፡** ይህ ቅድመ-ሁኔታ በቀጥታ የሚነሳዉ የሥነ-ምግባር መርሆዎቹ ተወዳዳሪ ፍላጎቶችን ለማቻቻል ካላቸዉ ሚና ነዉ፡፡ ተወዳዳሪ ፍላጎቶችን ማቻቻል ፍትሃዊነት በተሞላበት ሁኔታ ለተመረጡ እሴቶች ቅድሚያ መስጠትንና መርሆዎችን ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል፡፡
- **የሥነ-ምግባር መርሆዎች በመስሪያ ቤቱ ለሚከሰቱ ዋና ዋና ሥነ-ምግባራዊ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጠ መሆን አለባቸው፡** በዚህ መርህ መሰረት የስነ-ምግባር መርሆዎች ሲነደፉ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ችግሮችን እንዲሁም ከመስሪያ ቤቱ ባህርይ አንጻር ወደፊትም ሊከሰቱ ይችላሉ የሚባሉ የስነ-ምግባር ችግሮችን ታሳቢ ማድረግ እንዳለባቸው የሚጠቁም ነው፡፡

እነዚህ አምስት ሁኔታዎች የሥነ-ምግባር መርሆችን ተፈጥሮ ግንዛቤ ከማገዝ አልፎ በመንግስት ዘርፍ አስተዳደር ውስጥ የሥነ-ምግባር መርሆችን፣ ትክክለኛነትና አግባብነት ለመገምገም እንደ መስፈርት ሆነው ያገለግላሉ፡፡

## ትምህርት ሁለት
## 2.2.2 የሥነ-ምግባር መርሆዎች ማዋቀሪያ አምዶች

### 1. ፍትህ እና ፍትሃዊነት

**ፍትህ/ፍትሃዊነት ስነ-ምግባራዊ** ችግሮችን በመመርመር ከአድልዎ ነፃ የሆነ ዳኝነትንከመስጠት ጋር ይዛመዳል፡፡ ፍትህ የተመሰረተው በሁለት ሽልማት እና ቅጣትበተባሉ ምሶሶዎች ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ፍትህ ማለት ለእያንዳንዱ የሚገባውን ወይም ሚዛናዊ የሆነ ሽልማቱን እና/ወይም ቅጣቱን መስጠት ነው፡፡ የህብረተሰቡ ተቋማት በፍትህ መርሆዎች መመራት አለባቸው፡፡ በተቋማዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያለው ምክክር በተቋሙ ጉዳዮች ውስጥ የፍትህ ሂደት መገለጫ ነው፡፡ ምክንያቱም የምክክር ሂደቱ ውሣኔዎች የተለያዩ አመለካከቶች ማካተታቸዉን እና ፍትሃዊ ዉሳኔዎች የሚያስፈለጉ መረጃዎች ላይ መመስረታቸዉን ለማረጋገጥ ይችላል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በብዝሃነት አንድነት መኖሩን ማረጋገጥ በአብዛኛው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የህዝቡ የተሳትፎ ደረጃ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ስለሆነም የምክክር ሂደቱ ለፍትሃዊ አስተዳደር አስፈላጊ መስፈርት ሆኖ ተለይቷል፡፡

ፍትሃዊነት በግለሰብ ደረጃ ፍትህ በተግባር የሚገለጥበት ሂደት ነው፡፡ የኅብረተሰብ ተቋማት ፍትህን በጋራ በሚባል ደረጃ የሚያስተዳድሩ ሲሆን፣ ግለሰቦች በግለሰባዊ ተፅዕኖዋቸው ውስጥ በዳኝነታቸዉና በባህሪያቸው ፍትሃዊነትን ለማሳካት ይሞክራሉ፡፡ በትክክል ፍትሃዊ መሆን ማለት ነገሮችን በሌሎች አይን ሳይሆን በራሳችን አይን ማየት፤ ከሌሎች ሰዎች እዉቀት አንፃር ሳይሆን ጉዳዮችን በራሳችን እዉቀት መጠን መገንዘብ መቻል ነው፡፡ ይህ የፍትህ ፅንሰ ሀሳብ ጭፍን ጥላቻን ለማስወገድ እና በሁሉም ነገሮች እውነትን ለመፈለግ የሞራል ግዴታነትን የሚያመለክት ነው፡፡ የፍትህ መርሆዎችም የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- የህግ የበላይነት፣
- ስልጣንን በአግባቡ መጠቀምና የህዝብ ሀብቶችን በሃላፊነት መጠቀም፣
- ሚዛናዊ (እኩል የሆነ) የሽልማቶችና የቅጣቶች አስተዳደርን፣
- የመብቶች እና እድሎች፣
- አሳታፊ የተቋማዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት፣
- ብቃትን መሰረት ያደረገ የሰራተኛ አስተዳደር ይመለከታል፡፡

**መልመጃ 2.4**

1.ፍትሃዊነት ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ የሚኖረውን አስተዋጽ ምሳሌ እያነሳችሁ ተወያዩ::

**2. እውነት**

ለእውነት ታማኝ መሆን በግለሰብም ሆነ በህብረተሰብ ደረጃ ለታማኝነት፣ለቅንነትና ለክብር መሰረት ነው። የእውነት ፍለጋ ቢያንስ በሁለት መሠረታዊ ምድቦች መከናወን አለበት። የመጀመሪያው የተገለጠዉን ወይም የተረጋገጠዉን እውነት መረጃዎች ፍለጋ ነው። በማስረጃ ላይ የተመሠረተ የውሳኔ አሰጣጥ የተረጋገጡ እውነታዎችን መሰረት የሆነዉን ጥሬ ሀቅ ፍለጋ ላይ የተመሠረተ ነው። ሁለተኛው ምድብ ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያያዥነት ላላቸው የስነ- ምግባር መርሆዎች እና የምግባር እሴቶች ዉስጥ እዉነትን ፍለጋ ማድረግን ያካትታል። እንደ አለመታደል ሆኖ ይህ ምድብ ብዙውን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ችላ ይባላል። ለዚህም ነዉ ወደ ኢሥነ-ምግባረዊና ኢሞራላዊ የዉሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚወስደው።

በምክክር ሂደት ዉስጥ የሞራል ጥያቄ በሚነሳበት ጊዜ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ፍለጋና ተግባራዊነት ሲከተሉ፣ የውሳኔዎችን የጥራትና የጥበብ ደረጃን ከፍ ለማድረግ እና ቀጣይ ድርጊቶች የበለጠ ለማሳደግ የሚያስችል አዲስ እንቅስቃሴ ይጀምራል። ከህዝብ ሀብቶች አስተዳደር ጋር በተያያዙ ውሣኔዎች ላይ የሚተገበሩ እውነታዎችና መርሆዎች ግልጽነትና ሐቀኛነት የህዝብን እምነትን እጅግ በጣም ያሻሽላሉ። የእውነት መርሆዎችም የሚከተሉት ናቸዉ።

- ጥሬ ሀቆችን በትክክል ለህዝብ ይፋ ማድረግ፣
- ሃብትን በማስተዳደር ዙሪያ ሐቀኛ መሆን፣
- ማስረጃ-ተኮር-ውሳኔ አሰጣጥ፣
- የህዝብ ምርመራ የሚፈቅድ ግልጽ የውሳኔ አሰጣጥ እና የሃብት አስተዳደር፣
- ሙስናን የሚያጋልጡትን ከአደጋ መጠበቅ ናቸው።

**መልመጃ 2.5 የመወያያ ጥያቄ**

1. የእውነት መርሆዎች ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸውን ፋይዳ አስረዱ።

### 3. ለጋራ ጥቅም ማገልገል

ህብረተሰቡ አንድ የመንግስት ሰራተኛ መደበኛ የስራ ሃላፊነቱን ተጠቅሞ የህዝብ ጥቅምን ለማስጠበቅ ያለበትን የሞራል ግዴታውን እንዲያሟላ መጠበቅ አለበት። የአንድ የህዝብ አገልጋይ ክብርና መለያዉ ለብዙሃን ጥቅም በሚሰጠዉ እጅግ በጣም ጠቃሚና የተዋጣለት አገልግሎት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ መርህ ለመንግስት ተቋማትም ሆነ ለግለሰብ በእኩል መጠን ተግባር ላይ ሊዉል የሚችል ነው። መሠረታዊ ምግባር እሴት ለሆነዉ ለብዙሃን ጥቅም በግልሰብም ሆነ በተቋም ደረጃ ያለ ቁርጠኝነት የውስጣዊ ተነሳሽነት ምንጭ ነው። ይህም ማህበራዊ ለውጦችንና ልማትን ለማበረታታት ብዙውን ጊዜ የሚያስፈልጉትን ጥረቶችና ቁርጠኝነት ዘላቂ ለማድረግ ያስችላል። አንድ የመንግስት ሰራተኛ መደበኛ የስራ ሃላፊነቱን የራሱን ጥቅም ለማራመድ ከተጠቀመ ለዉጤታማ አስተዳደር በጣም አስፈላጊ ግባአት የሆነዉ ህዝባዊ እምነትን ሊያጠፋ ይችላል።

በመልካም ስሜት የተቃኘና ውጤታማ አገልግሎት ለህብረተሰቡ መስጠት የህዝብ አመኔታ መሰረት ነው። የብዙሃን ጥቅም ምንድን ነዉ በሚለዉ ላይ ስምምነትን መፍጠር ቀጣይ ሂደት ነው። የብዙሃን (የጋራ) ጥቅም በአጠቃላይ በጋራ እሴቶች ላይ የሚወሰን ሲሆን እነዚህም በጊዜ ሂደት ስለሚቀያየሩ በብዙሃን ጥቅም ላይ ያለዉ የጋራ መግባባቱም ይለዋወጣልና ሊሻሻል ይችላል። በህብረተሰብ ውስጥ የሞራል አመራርነት ከፍተኛ ሚና የሚገለፀዉ የብዙሃን ጥቅምን በሚገልፁ ዋና ዋና የጋራ እሴቶች ላይ የጋራ መግባባት መድረስ መቻሉ ላይ ነው። አንድ የህዝብ አገልጋይ ለጋራ ጥቅም እና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት የሞራል ግዴታ አለበት። ለብዙሃን ጥቅም የመቆም መርሆዎችም የሚከተሉት ናቸዉ።

- የብዙሃን ጥቅም ምንድን ነዉ በሚለዉ ላይ የጋራ ስምምነት ግንባታ፣
- የሰብአዊ ልማት አመልካቾች መተግባበር፣
- የህዝብ አገልግሎቶች ሁሉን ያካተተ መሆን አለባቸው፣
- የአገልጋይነት መንፈስ፣
- ሰብአዊ ክብርን ማክበር።

**መልመጃ 2.6 የመወያያ ጥያቄ**

1. ለብዙሃን ጥቅም የመቆም መርህ ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያለውን አስተዋጽኦ በምሳሌ እያስደገፋችሁ አብራሩ።

## 4. ዉክልና

መልካም አስተዳደር በህዝብ አመኔታ ላይ የተመሰረተ ነዉ። አንድ የመንግስት ተቋም ያለበቂ ህዝብ አመኔታ የተጣለበትን ሃላፊነት በሚገባ መወጣት አይችልም። ይህ የህዝብ አመኔታ የሚሰጠዉ ደግሞ ታማኝነት ላላቸዉ የመንግሰት ሰራተኞችና ተቋማት ነዉ። በህዝቡና በመንግሰት ሰራተኞች መካከል ያልተጻፈ ማህበራዊ ቃል-ኪዳን ወይም ሞራላዊ ስምምነት አለ። ይህም ስምምነት ክፍል አለዉ። የመጀመሪዉ የመንግሰት ሰራተኞች በህዝቡ ሀብት ላይ ዉክልና እንደተሰጣቸዉ አካላት ስልጣናቸዉን፣ ሃይልንና ሀብትን ሲጠቀሙ ታማኝ እንዲሆኑ

ማህበረሰቡ መጠበቁ ነዉ። ህብረተሰቡ በበኩሉ በታማኝነት ለሚያገለግሉ የመንግሰት ሰራተኞች እዉቅና በቂ ጥቅማጥቅም መስጠት ይጠበቅበታል። የዉክልና መርሆዎችም የሚከተሉት ናቸዉ።

- አገልግሎት ለመስጠት በመንግስትና በመንግሰት ሰራተኞች መካከል የሚደረግ ህጋዊ ዉል፣
- ኃላፊነት የተሞላበት የህዝብ ሀብት አጠቃቀም፣
- ዉጤታማና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ የህዝብን ፍላጎት ማሟላት፣
- ሊያጋጥሙ በሚችሉ የጥቅም ግጭቶች ላይ ግልጽ መሆን፣
- ለብቃት እዉቅና መስጠትና በቂ ጥቅማ ጥቅም።

**መልመጃ 2.7 የመወያያ ጥያቄ**

1. በመጣችሁበት ተቋም ውስጥ ከስነ-ምግባር እሴቶች ማወቀሪያ አምዶች የመነጩ የስነ-ምግባር እሴቶች እንዳሉ ግለጽ።
2. ከስነ-ምግባር ማዋቀሪያ አምዶች የመነጩ እሴቶች ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸውን ፋይዳ አስረዱ።
3. የስነ-ምግባር መርሆዎችን ለመቅረጽ የሚደረገው ጥንቃቄ መልካም አስተዳደርን በማረጋገጥ ላይ ያለውን እንድምታ አስረዱ።

## ትምህርት ሦስት

### 2.2.3 የሥነ-ምግባር ደንብና የሥራ ሥነ-ምግባር

**የሥነ-ምግባር ደንብ፡** ተቀጣሪ ሰራተኞችን ሥነ-ምግባራዊ ባህርይ አቅጣጫ ለማስያዝ የሚዘጋጅ ሰነድ ነው፡፡ በአንድ ፕሮፌሽን ወይም ድርጅት ውስጥ ያሉ ሰራተኖች የቀን ተቀን ስራቸውን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ሊከተሏቸው የሚገቡ ሥነ-ምግባራዊ ባህርይን አደራጅቶ የያዘ ሰነድ ነው፣ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የተሰባሰቡ አባላት ለጋራ ደህንነታቸው ሲሉ ወይም የጋራ ደህንነታቸውን የሚጎዳ ባህርይን ለመከላከል ወይም ለማስወገድ ስልታዊ በሆነ መንገድ የሚያወጡት መመሪያ፣ ህግ ወይም መርህ ነው፡፡

የስነ-ምግባር ደንብ ተግባራዊነት ጠንካራ የቡድን ስራ መንፈስ ይፈጥራል፣ምርታማነት ይጨምራል፣ ቅጣት፣ወይም ማስጠንቀቂያ እንዲወገድ ያደርጋል፤ ልዩነትን (በመልክ፣ በዘር፣ እሴት፣ በአመለካከት…ወዘተ) ባግባቡ ማስተናገድ ያስችላል፣ ተቋማዊ የስራ ባህል እንዲዳብር ያደርጋል፣ በግልና በቡድን መካከል መተማመን እንዲፈጠር ያደርጋል፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን የተበቀ እንዲሆን ያደርጋል፣ መልካም አስተዳደር እንዲጎለብት ያደርጋል፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል ይቻላል፡፡

በስራ ቦታ መልካም ሥነምግባር እንዲጎለብት በየደረጃው ያሉ መሪዎች በመልካም ሥነ ምግባራቸው አርአያ ሊሆኑ ይገባል፤ መሪዎች የተናገሩትን ሆነው በመገኘት አርአያ ሊሆኑ ይገባል (የተናገሩትን ሳይሆኑ የቀሩ መሪዎችን እንደምሳሌ ማንሳት ትችላለህ)፣ የስራ ላይ ስነ- ምግባርን በተመለከተ ስልጠና መስጠት ይገባል፣ መልካም ሥነ-ምግባር የሚያሳዩትን ማበረታታት፣ ሲኒየር ወይም ቀደምት ሰራተኞች እና የስራ ሃላፊዎች ሮል ሞዴል ሊሆኑ ይገባል፣የስነ-ምግባር ደንቦችን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ (ለ ethical dilemma የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን በደንቡ ውስጥ በተቻለ መጠን ማካተትና ኢቲካል ዳይለማ ሚከሰትበትን ሁኔታ ለመቀነስ መሞከር)፤ ስነ-ምግባራዊ ውሳኔዎች ላይ በርካቶች እንዲሳተፉበት ማድረግና ውሳኔ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ፣ ስነ-ምግባራዊው ውሳኔዎችን ሁሉም እንዲያወቁት ማድረግ፣ የስነ-ምግባራዊ ጉዳዮችን ከሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳስር ለምሳሌ በሚቀረጹ እሴቶች ላይ ከአስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳሰር፣በሰው ሃብት አመራር ውስጥ ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ከስነ-ምግባር ጋር ማስተሳሰር…ወዘተ ጠቃሚ ነው፡፡

በመንግስት ተቋማት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በዚያ ተቋም ውስጥ የሚገኝ

***ማንኛውም የመንግስት አካልም ሆነ ግለሰብ ሁልጊዜ ከህዝብ ጥቅም አኳያ ሊሰራ ይገባዋል፡፡ ፖሊሲዎችና ህጎች የሚጠይቁትን ሁሉ ወጥ በሆነ መንገድ መተግበር አለባቸው፡፡ የግል ፍላጎታቸውን ሊያስወግዱም ይገባል፡፡ የህዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የተቋሙን ፍላጎት ሁሉ መሞገት ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ የተገልጋይን ፍላጎት ማርካት ድምር ውጤት የህብረተሰብን ጥቅም ማርካትን ያመጣል፡፡***

**መልመጃ 2.9**

ከዚህ በታች በአንድ ተቋም ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሰራተኞች ባህርይ ቀርቧል፤ ባህርያቸው ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ላይ ያለውን ተጽእኖ አስረዱ፡፡

1. በተቋሙ የሚፈጸሙ ማናቸውም ነገሮች እኔን አስካልነኩ ድረስ ምን ቸገረኝ ብሎ የሚያልፍ ነው፤
2. ስራውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ያከናውናል ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ቢሮ ውስጥ አይገኝም፤
3. ስራውን ይሰራል ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ኢሜል እና ፌስቡክ ያዘወትራል፤
4. ከመስሪያ ቤት አይቀርም ነገር ግን ለሻይ እረፍት ከወጣ ብዙ ጊዜ አጥፍቶ ይመለሳል፤
5. ስራውም ሆነ ስነ-ምግባሩ መልካም ነው አለባበሱ እና ጸጉር አቆራጡ ግን ዘመናዊ ለመሆን ስለሚፈልግ የዘመኑን ዘይቤ የሚከተል ነው፡፡

## ትምህርት አራት

## 2.2.4 የሥነ-ምግባር ደንቦች ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸው ጠቀሜታ

የሥነ-ምግባር ደንቦች ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ማእቀፍ (Frame work) ሆነው ያገለግላሉ፤ አንድ ሰራተኛ ስራውን በምን ዓይነት አኳኋን መስራት እንዳለበት ይጠቁማል ብልሹ ስነ-ምግባርን ለመከላከል ይረዳል፤ በሰራተኞች መካከል የጋራ የስራ መግባባት እንዲኖር ያደርጋል፤ ብልሹ አሰራርና ሙስናን ይከላከላል እንዲሁም የጥቅም ግጭትን በማስወገድ በተቋም ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡ ስለዚህ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መውጣቱ ብቻ ሳይሆን የወጣው የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም የስነ-ምግባር ደንቦች ተግባራዊነታቸውን ለማጠናከር ደንቦቹ በተቻለ መጠን ኢቲካል ዳይለማ የሚፈጥር ሁኔታዎችን የሚያስወግድ እንዲሆን ማድረግ፤ በሥነ-ምግባር ደንቦቹ ዙሪያ ተከታታይ ስልጠና መስጠት፤ ለአዲስ ተቀጣሪ ሰራተኞችን ደንቡን ማስተዋወቅ ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔዎችን ለሁሉም ይፋ ማድረግ፤ደ ንቡን ከሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳሰር ከመስሪያ ቤቱ እሴት፣ ከቅጥርና እድገት ጋር ማስተሳሰር… ወዘተ ይጠቅማል፡፡

የስነ-ምግባር ደረጃዎችን ጠብቆ ለማቆየት/ለማረጋገጥ ተቋማት የስነ-ምግባር ደንብ ካወጡ በኋላ በስልጠና ሊያዳብሩት ይገባል፡፡ በስራ አፈጻጸም ግምገማ ወቅትም ተገቢ የሥነ-ምግባር ደረጃ ያላቸውን በማበረታታት፣ የስነ-ምግባር ጉድለት ያለባቸውን ደግሞ በማረም ማጠናከር ይገባል፡፡ የመስሪያ ቤቱ ከፍተኛ ሃላፊዎች ተቋማቸው በስነ-ምግባር ደረጃ ባለው አቋም መርካት አለመርካታቸውን በአመታዊ ወይም በግማሽ አመት ሪፖርታቸው ውስጥ አካተው ሊቃኙት ይገባል፡፡ ተቋሙ በሚያከናውናቸው የግዥ ሂደቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር ደረጃዎች መጠበቃቸውን አገልግሎት ከሚሰጣቸው ወይም በግዥ ጉዳይ አገልግሎት ከሚፈልጉ ተገልጋዮች መረጃዎችን በመሰብሰብ የሥነ-ምግባር ደረጃውን ሊፈትሽ ይገባል፡፡

**መልመጃ 2.10 የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የአንድ ተቋማ እሴቶች በምሳሌነት ወስዳችሁ ለተቋሙ መልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያላቸውን አስተዋጽኦ ገምግሙ
2. የሥነ-ምግባር ደንቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ የተቋም መሪዎች ባላቸው ሚና ላይ ተወያዩ

## የክፍል ሁለት ማጠቃለያ

*የሥነ-ምግባር መርሆዎች በተቋም ውስጥ ያሉ ሰዎች ለጋራ ደህንነት ሲሉ ተስማምተው የሚቀርጻቸው የስነ-ምግባር እሴቶች ናቸው፡፡ የእነዚህ እሴቶች በጥንቃቄ መቀረጽ በተቋሙ ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን በመልካም ስነ-ምግባር ለማከናወን ትልቅ ፋይዳ አላቸው፡፡ እንዲሁም እነዚህ የተለዩት እሴቶች ወይም መርሆዎች በስነ-ምግባር ደንብ ውስጥ በመግባት እንደ መመሪያ ሆነው ስለሚያገለግሉ ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ እነዚህ መርሆዎች ለግብር ከፋይ ህብረተሰብ ሚፈልገውን ጥያቄ በአግባቡ ምላሽ እንዲያገኝ የሚያስችሉ የስነ-ምግባር መሰረቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ለስነ-ምግባር መረጋጋት ፋይዳቸው ከፍተኛ ነው፡፡*

*የስነ-ምግባር ደንቦችም እንዲሁ ዜጎች በመልካም ስነ-ምግባር የታጀበ አገልግሎት ለማግኘት ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ደንቦቹ ከተቀረጹ በኋላ በተቋም ውስጥ ህያው ሆነው እንዲያገለግሉ ከሌሎች የመስሪያ ቤቱ አሰራሮች ጋር ሊተሳሰሩ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተቋሙ ሃላፊዎች ደንቡን ለማስተሳሰርና መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ ግንባር ቀደም ሊሆኑ ይገባል፡፡*

## ክፍል ሶስት

## 2.3 በህዝባዊ ተቋማት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚጠቅሙ ቁልፍ ጉዳዮች

### የክፍል ሶስት አጭር መግለጫ

የህዝባዊ ተቋማት የተሰጣቸውን ተልእኮ ለማሳካትና የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት የሚመሩበትን ህግና ፖሊሲ ጠብቀው እንዲሰሩ ከፍተኛ አደራ የተጣለባቸው ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ በሚሰጡት አገልግሎትና አገልግሎት ለመስጠት በሚያደርጉት እንቅስቃሴዎች መልካም አስተዳደር በሰፈነበት ማዕቀፍ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም በዚህ ትምህርት ክፍል የህዝባዊ ተቋማት መልካም አስተዳደር ለማስፈን የሚያስፈልጉና የሚጠቅሙ ቁልፍ ጉዳዩች ቀርቧል፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

የሥልጠናው ተሳታፊዎች ከክፍል ሶስት ትምህርት በኂላ:

- ☞ ምሉእነት ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያለውን ፋይዳ ያስረዳሉ፤
- ☞ የስነ-ምግባር እሴቶችን ለመፈጸም የሚደረግ ቁርጠኝነት ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያለውን ፋይዳ ያብራራሉ፤
- ☞ ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ኢንተግሪቲያቸውን ለመጠበቅ ይወስናሉ፤
- ☞ ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ቁርጠኛ ለመሆን ግንዛቤ ይይዛሉ፡፡

**የመነሻ ተግባር 2.4**

1. በአንድ ተቋም ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ኢንተግሪቲ ወይም ምሉእነት የዜጎችን የአገልግሎት ፍላጎት በማርካት መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ ያለው ፋይዳ ምንድን ነው?
2. በተቋማት ውስጥ በየደረጃው ያሉ የህዝባዊ ተቋማት የሥራ ሃላፊዎች የሥነ-ምግባራዊ እሴቶችን ለመጠበቅና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚያደርጉት ቁርጠኝነት ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያለውን አስተዋጽኦ አብራሩ?

የህዝባዊ ተቋማት ከህብረተሰቡ ከታክስ ከሚሰበሰበው ብሄራዊ ሃብት ውስጥ በርካታ የሚሆነውን በጀት ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡበት ባግባቡ የማስተዳደር ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡ የመንግስት ተቋማት በሀላፊነት ከተሰጣቸው ገንዘብ ውስጥ ተጠያቂ የሚሆኑት ምን ያህሉን ተጠቅመውበታል በሚል ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የተሰጣቸውን ገንዘብና ቁሳቁሶች እንዴት ተጠቅመውበታል የሚለውንም ባግባቡ በመመለስ ተጠያቂ

ይሆናሉ። የመንግስት

ተቋማት የተሰጣቸውን ተልእኮ ለማሳካትና የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት የሚመሩበትን ህግና ፖሊሲ ጠብቀው እንዲሰሩ ከፍተኛ አደራ የተጣለባቸው ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ በሚሰጡት አገልግሎት እና አገልግሎት ለመስጠት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ቅንነት በተሞላበት መንገድ የቻሉትን ያህል የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘይቤ ተጠቅመው እንዲያገለግሉ ያስገድዳቸዋል፡፡ እንዲሁም እሴቶች ለመጠበቅ ህግን ጠብቆ ለመስራት የሚያስችል ጠንካራ ቆራጥነት እንዲኖር ስልቶች ሊቀይሱ ይገባል፡፡

### 1. ቅንነትን ማረጋገጥ

በአንድ ተቋም ውስጥ የህብረተሰቡን ፍልጎት አክብሮ መስራት ባህል ወይም የዘወትር ልማድ እንዲሆን የመስሪያ ቤቱ ሃላፊዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ በተቋሙ ውስጥ ላሉ የስነ- ምግባር እሴቶች መከበር እየኖሩ ማሳየትን ከመሪዎች ይጠበቃል፡፡ እነዚህ እሴቶች ቀላል እና ማንም በቀላሉ ሊረዳቸው የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች ደግሞ በህግ ከሚጠበቅ ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃ ከፍያሉና በህብረተሰቡ ህይወት ውስጥ በተጨባጭ ሊታዩ በሚችሉ መርሆች ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ለማሳሌ ታማኝነት፤ ራስ ወዳድ አለመሆን፣ ተጨባጭ መሆን (የሚፈለገውን ነገር በግልጥና በሚጨበጥ ሁኔታ ማስረዳት)፤ እነዚህ መርሆች ህብረተሰቡ አገልግሎት ከሚፈልግብት ተቋሙ፤ በተቋሙ ውስጥ ካሉ ቡድኖች (የስራ ክፍሎች)፤ ከግለሰቦች የሚጠብቃቸውን ባህርያት (የአገልግሎት አሰጣጥ መንፈስ) የሚያንጸባርቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የስራ ሃላፊዎች እነዚህን ባህርያት በመጠበቅ በሚወስኑት ውሳኔ እና በሌሎች ድርጊቶቻቸው አርአያ ሆነው ሊገኙ ይገባል፡፡ እነዚህ እሴቶች የተቋሙ ጠባብሮ የመስራት ባህል እንዲሆኑ በልዩ ልዩ ስልቶች መሬት ሊወርዱ ይገባል፡፡ ከስልቶቹ መካከል እነዚህን እሴቶች ከመቅረጽና ከማስተዋወቅ ጀምሮ በተቋሙ የስነ-ምግባር መርሆችና ደንቦች ሆነው እንዲተገበሩ ማድረግ፣ ምሳሌያዊ አኗኗር በመኖር እንዲሁም በሥራ አፈጻጸም ወቅት የሚደረግ ሽልማትና ማበረታቻ ሊጠቀሱ ይችላል፡፡

### 2. ለሥነ ምግባራዊ እሴቶች መጠበቅ የሚደረግ ጠንካራ ቁርጠኝነት

*ሥነ-ምግባራዊ* እሴቶች ወይም *የሥነ-ምግባር* ደረጃዎች በተቋሙ ውስጥ የሚተገበሩና በተቋሙ ውስጥ ለሚተገበሩ *ፖሊሲዎች*፤ የስራ *መመሪያዎች*፣ ለማንኛውም እንቅስቃሴ እና በተቋሙ ውስጥ በማናቸውም ደረጃ ላሉ ፈጻሚዎችና ሃላፊዎች ግላዊ ባህርይ መነሻ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የሚጠበቁ የስነ-ምግባር ደረጃዎች ማውጣት እያዩ ደግሞ ማሻሻል

እንዲሁም እያንዳንዷ ኮድ ለእያንዳንዱ የተለየ ሁኔታ ምን ትርጉም ወይም እንድምታ እንዳለው ማስገንዘብ

ሀ/ ተቋሙ በምን ሁኔታ ትግበራን ማከናወን እንዳለበት ለ/ በተቋሙ ውስጥ እየተተገበሩ እንዲሁም ሐ/ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር እንዴት ሃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚችሉ ግልጽ ያደርጋል፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖር ባለድርሻ አካላት ተቋሙ ለሥነ-ምግባር እሴቶች

ዋጋ እንደሰጠ ያስገነዝባሉ፡፡ የህብረተሰብን ፍላጎት ለማርካት በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ በተለያየ ደረጃ ያሉ አገልግሎት ሰጪዎች ጥቅም ግጭት ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡ የህብረተሰብን አመኔታ ለማረጋገጥ ወይም ለማጠናከር ከሚታወቅም ሆነ ከሚገመት የጥቅም ግጭት ራስን ማግለል ተገቢ ይሆናል፡፡

አንዳንድ ጊዜ የስነ-ምግባር ችግር በተቋም ውስጥ እስካልተከሰተ ድረስ ተቋሙ በአመራር፣ በስነ-ምግባር እና በስነ-ምግባራዊ ባህል ምን ደረጃ ላይ እንዳለ መለካት ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ይሁንና ተቋማት ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ራሳቸውን ሊፈትሹ ይገባል፡፡ የሰራተኞች ቅኝት ወይም ሰርቬይ በማድረግ፣ በስራ አፈጻጸም ግምገማ እንዲሁም በአመራር ግለ ግምገማ አማካኝነት መፈተሽ ይገባል፡፡ የባለ ድርሻ አካላት ግብረ መልሶችም ተቋሙ በስነ-ምግባራዊ እሴቶቹ፣ በአመራሩ እና በስራ ባህሉ ምን ደረጃ እንዳለ ሊያመለክቱ ይችላል፡፡ ከአስተያየት መስጪያ የሚሰበሰቡ ግብረ መልሶች በጊዜውና በአፋጣኝ ሊታዩና ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል፤ እንዲሁም ከእነሱም የገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ለማሻሻል፣የሥነ-ምግባር ደረጃን ለማሻሻል ተሞክሮዎችንም መውሰድ ይጠቅማል፡፡ የሥነ-ምግባር ጉድለትንም ለመከታተል የጥቆማ ስርአት ማቋቋም ተገቢ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ስርአት ሲዘረጋም ጠቋሚዎች የቂም በቀል እርምጃ እናዳይወሰድባቸው ተገቢ ጥበቃ ወይም ከለላ የሚያገኙበትንም ሁኔታ ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

### 3. የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ጠንካራ ቁርጠኝነት

ተገቢ የህግ ማእቀፎች ከአድሎ የነጻና ገለልተኛ የፍትህ ስርአት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች አስተማማኝ ጥበቃ ያላቸው እንደሆኑና ያለ ስጋት ተማምነው እንዲኖሩ በማድረግ የለ ማህበረሰብ ግንባታ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ተቋማት እነዚህ ህጎች በማውጣት በማስፈጸም የራሳቸው ድርሻ አላቸው፡፡ ታዲያ ይህን ሃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ የሞራል ልዕልና ሊጎናጸፉ ይገባል፡፡ ህግ ተላላፊዎችን ለማረም ወደ ተገቢው መስመር ለማስገባትም ልዩ ልዩ ስልቶች ሊዘረጉ ይገባል፣በዚያው አግባብ ተቆጣጣሪ አካላትንም ማደራጀት ይገባል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሚሰሩ ተቋማትም ለተለያዩ ጉዳዮች የሚወጡ ህጎች ተግባራዊነትና ለህግ የበላይነት ቁርጠኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡፡ ሙሉ ሃይላቸውን የህዝብን ጥቅም ለማረጋገጥ ሊያውሉት ይገባል፡፡ ሌሎች የመንግስት ተቋማትም ሆነ በውስጡ ያሉ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች በህግ አውጭው ሚወጡ ህጎችንና እነሱን የሚመለከታቸውን ህጎች ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሲተገብሩ ለህግ የበላይነት የራሳቸውን ድርሻ ተወጥተዋል ማለት እንችላለን፡፡

በህዝባዊ ተቋማት የቅንነት የቁርጠኝነት (ለሥነ-ምግባራዊ እሴቶች እና ለህግ የበላይነት) መኖሩን ለማረጋገጥ የሚጠቅም ቼክ ሊስት

- ☞ ከሥነ-ምግባር ጉድለት የተነሳ ሊገጥሙ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎች ተለይተዋል?
- ☞ ሁሉም የተቋሙ አባላት እና ሰራተኞች የሚስማሙበትና የሚያከብሩት ከአባላቱ ሚጠበቁ ባህርያትን የሚያሳይ መደበኛ የስነ-ምግባር ደንብ አለው?
- ☞ የስራ ሃላፊዎች የስነ-ምግባር ደንቡን እየኖሩት ወይም የየእለት ኑሯቸው አድርገውት ደንቡ ትክክለኛ ድምጸት ያለው መሆኑን ያሳያሉ?
- ☞ በአመራር ደራጃ ያሉ የስራ ሃላፊዎች የተቋሙን አላማ እና እሴት የሚያንኳስስበት ሁኔታ/መንገድ ይኖራል ወይ?
- ☞ በመስሪያ ቤቱ በአመራር ደረጃ ያሉ ሰዎችም ሆነ ሌሎች ሰራተኞች በጥቅም ግጭት ወይም በአድልዎ ተጽእኖ ውስጥ እንዳይወድቁ የሚያስችሉ ተገቢ ስልቶችን ዘርግተዋል?

- ☞ በማኔጅመንት አጀንዳዎች ላይ የስነ-ምግባር ጉዳዮች በመደበኛነት ይታያሉ?
- ☞ የመስሪያ ቤቱ ዋና ሃላፊ በራሱ አካባቢ ላሉ የስራ ሃላፊዎቸ ወይም ሰራተኞች የሥነ- ምግባር ደረጃ ራሱ ሃላፊነት ይወስዳል?
- ☞ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች በስራቸውና በመስሪያ ቤቱ እንቅስቃሴዎች እንዲያንጸባርቋቸው የሚጠበቁ ባህርያት ምንድን ናቸው? እነዚህ ባህርያት ባግባቡ ተመዝግበውና ሰራተኛው እንዲውቃቸው ተደርገዋል?
- ☞ ተቋሙ የጸረ-ሙስና ፖሊሲ አለው? በትክክልስ ተተግብሯል?
- ☞ የተቋሙ ሰራተኞች በሙሉ በስነ-ምግባር ጉድለት፤ በሙስና ወይም በማጭበርበር ቢጠረጠሩ ምን ሊደርስባቸው እንደሚችል ያውቃሉ ወይ?

## 4. የጥቅም ግጭትን መለየትና መቆጣጠር

በጥቅም ግጭት ጉዳይ ላይ አስቀድሞ ሊጠየቅ የሚገባው ጉዳይ አንድን ተግባር እንዲያከናውን ሃላፊነት የተሰጠው አካል ወይም ሰራተኛ ከዚያ ጉዳይ ጋር በጥቅም የሚያገናኘው ጉዳይ አለ ወይስ የለም የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ አብዛኞች የዚህ አይነት ጉዳዮች ግልጽ የሆነ የጥቅም

ግጭት ማሳያ ልናገኝላቸው ይችላል፡፡ ይሁንና እንዲህ አይነት አጠራጣሪና ለመወሰን የሚያስቸግር ደብዛዛ ጉዳይ ሲያጋጥም ተግባሩን ሊያከናውን በላው ባለሞያ እና በጉዳዩ መካከል የጥቅም መተሳሳር/ግጭት መኖሩን እንዲያረጋግጡ ጉዳዩን አውጥቶ ለሌሎች ባለሞያዎች በመናገር ጉዳዩ የጥቅም ግጭት እንዳለውና እንደሌለው እንዲመረምሩ ማድረግ ዝም ብሎ ተግባሩን ከማከናወን ይልቅ ተመራጭ ይሆናል፡፡

## 5. ግልጽነት

የመንግስት ተቋማት የህብረተሰብን ፍላጎት ለማርካት የተቋቋሙ እንደ መሆናቸው በሚሰሩት ስራ ሁሉ ግልጽነት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንዲሁም ከዜጎች ጋር ከደንበኞቻቸው እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ስለ አገልግሎታቸውና ስለሚሰሯቸው ስራዎች የሚመካከሩበት ስራቸውን የሚያሳውቁበት አመኔታን ያተረፈ የመገናኛ/ኮሚኒኬሽን መድረክ ወይም ዘዴ/ቻነል ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ተቋማት በሚያገለግሉት ህብረተሰብ ፍላጎት መሰረት እየሰሩ መሆኑን ለማሳየት የሚሰሩለትም ህብረተሰብ በእነሱ ላይ አመኔታ እንዲኖረው ለማድረግ የተቻላቸውን ያህል ግልጽ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት ተቋማት የሚወስኑት ውሳኔ፣ እቅዳቸውና ሚያከናውኑት ተግባር፣ የሪሶርስ አጠቃቀማቸው፣ እና ያስመዘገቡት ውጤት ግልጽ ሆኖ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የስራ ሃላፊዎች የሚወስኗቸው ውሳኔዎች በሙሉ ተመዝግበው መያዝ አለባቸው፤ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለባለድርሻ አካላት የውሳኔቸውን አመክንዮ በግልጽ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡

መረጃ ለመከልከል የሚያስችል በቂ ምክንያት እስከሌለ ድረስ መረጃዎች ግልጽ መሆን አለባቸው፤የሚከለከሉ መረጃዎች በህግ የተከለከሉና የብሔራዊ ደህንነትን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ፣ከሌሎች አገራት ጋር ያለውን የውጭ ግንኙነት እንዲሁም አለም አቀፍ ግንኙነትን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ብቻ ሊሆኑ ይገባል፤ እነሱም በቁጥር የሚታወቁና ውሱን መሆን አለባቸው፡፡

### 6. ዜጎችንና የተቋሙን ተገልጋዮች ማሳተፍ

ተቋሙ የሚሰጡት አገልግሎት ሊያሳኩ የሚፈልጉትን ግብ ሊያመጣላቸው እንደሚችል ከዜጎችና ከተቋሙ ተገልጋዮች ጋር የሚመካከሩበት ግልጽ የሆነ አቅጣጫና ፖሊሲ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ልዩ ልዩ ዳራ ወይም የስራ ልምድ ካላቸው ሰዎች ወይም ተቋማት አስተያየት የሚሰበስብበትና የሚገመግምበት ሂደት መኖሩንም እርግጠኛ መሆን አለበት፡፡ መረጃ በሚሰበሰብበትና በሚገመገምበት ጊዜም ተደማጭነታቸው የጥቂት አካላት ፍላጎት ብቻ ገኖ በሌሎች ላይ ተጽእኖ እንዳያሳርፍ ሚዛናዊ መሆን ይገባል፡፡ ግምገማዎች የመጪውን ትውልድ ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡ ለምሳሌ በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እና አመቺነት ላይ በቀጥታ ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑ ደንበኞች ላይ ያላቸውን አስተያየት መጠየቅ ይቻላል፡፡ እንዲህ አይነቱ አስተያየቶች ወይም መረጃዎች በልዩ ልዩ መንገድ ሊሰበሰቡ ይችላል፤ለምሳሌ በሰርቬይ/ቅኝት፣ በዌብሳይት፣ ወይም በቀጥታ ግብረ መልስ በመጠየቅ፣ ወይም ከተገልጋዮች ጋር በሚደረግ መደበኛ ስብሰባ፤ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚዘጋጀው ፖሊሲ እንዚህ ግብአቶች እንዴት ለውሳኔ አሰጣጡ እንደሚጠቀምባቸው በግልጽ ሊያስቀምጥ ይገባል፤ እነዚህኑ ግብአቶች ተጠቅሞ እንዴት ውሳኔ እንደወሰነም መልሶ ለህብረተሰቡ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

**መልመጃ 2.11 የመውያያ ጥያቄዎች**

1. አንድን የምታውቁትን ተቋም በምሳሌነት በመውሰድ ኢንተግሪቲን ለማረጋገጥ በሚጠቅመው ቼክ ሊስት መሰረት ግምገማ አድርጉ፤ በግምገማችሁ ውጤት መሰረትም በተቋሙ መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ የመፍትሄ ሃሳብ አቅርቡ።

---

## የክፍል ሶስት ማጠቃለያ

*በአንድ ተቋም ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ ወሳኝ የሆኑና ከከፍተኛ የስነ-ምግባር ደረጃ ሚመነጩ ቁልፍ ጉዳዮች አሉ። እነሱም የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ መሆን፤ ዘወትር የሚናገሩትን ሚጽፉትና ለህብረተሰብ ተስፋ ሚገቡትን ጉዳይ በተግባር ለማሳየት ቅንነትን መጠበቅ፤ አመኔታ ያተረፈ የግንኙነት ስርአትን መዘርጋት፣ ግልጽነትና ራስን ሁልጊዜ መፈተሽና የመሳሰሉት ናቸው። ተቋማት የእለት ተለት ስራቸው ቀጥሎ ስለ ተከናወነ ምንም አይነት የስነ-ምግባር ችግር አላጋጠመንም የምንሰጠውም አገልግሎት ህብረተሰቡን ያረካ ነው ብለው መቀመጥ የለባቸውም፤ ይልቁንም በተለያየ መንገድ መረጃዎችን በመሰብሰብ ራሳቸውን የሚፈትሹበት ቼክሊስት በማዘጋጀት ራሳቸውን እየፈተሹ አገልግሎታቸውን እያሻሻሉ መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።*

# ክፍል አራት

## 2.4 ሥነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎች እና መልካም አስተዳደር

### የክፍል አራት አጭር መግለጫ

*በማንኛውም የስራና የሙያ መስክ የተሰማሩ ሰራተኞች በየእለቱ ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ክህሎት የሚጠይቁ ፈታኝ ሥነ-ምግባራዊ ጉዳዮች ይገጥማቸዋል፡፡ እነኝህን ለሚገጥሟቸው ሥነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎች ተገቢና ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያግዝ ክሆሎቶችን ማዳበር እና ለውሳኔያቸው መሰረት ሊያደርጓቸው የሚገቡ ሥነ-ምግባራዊ ውሰኔ አሰጣጥ ሂደቶች ጋር ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ሲባል በዚህ ክፍል ሥነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎች ከመልካም አስተዳደር ጋር በማሰተሳሰር ቀርቧል፡፡*

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

*የሥልጠናው ተሳታፊዎች ከክፍል አራት ትምህርት በኋላ:*

- ☞ *ሥነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎችን ይረዳሉ፤*
- ☞ *ለሥነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎች የተሻለ ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ ይሰጣሉ፤*

**የመነሻ ተግባር 2.5**

1. ከዚህ በፊት ውሳኔ ለመስጠት የተቸገሩበት የስነ-ምግባር ጉዳይ ገጥምዎት ያውቃል፤ ከሆነ ለውሳኔዎት እንዲረዳዎ የተጠቀሙባቸው መስፈርቶች ምንድን ናቸው?
2. ለሚገጥሙ ስነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎች የምንሰጣቸው ምላሾች በመልካም አስተዳደር ላይ ምን አይነት ተጽእኖ ይኖረዋል?

*በማንኛውም የስራና የሙያ መስክ እና የሃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ ሲቪል ሰርቫንት ደረጃው ይለያይ እንጅ ሁላችንም በምንሰራበት ተቋም የተሰጠን ተግባርና ሃላፊነት አለብን፡፡ ሃላፊነታቸው ደግሞ ለህዝብ አገልግሎት ከመስጠትና ፍላጎትን ከሚሟላት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለህዝብ አገልግሎት ለመስጠት ከተገልጋዮች ጋር በሚኖር ግንኙነት፣ እንዲሁም እንድናስተዳደረውና እንድንጠቀምበት በተሰጠን ሀብት፣ ንብረትና የሰው ኃይል ጋር በተያያዘ በየቀኑ ውሳኔዎችን ይወስናሉ፡፡*

*በውሳኔ አሰጣጥ ወቅት የሚጋጥሙትን ፈታኝ ሁኔታዎች በማቃለል የተሻለ እና ትክክልኛ ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚያግዙ መርሆዎች፣ በውሳኔ*

አሰጣጥ ሂደት ልንከተላቸው የሚገቡ ቅደም ተከተሎችን ተግባራዊ ማድረግ ለምሳሌ፤ ፈታኝ ሁኔታ ሲያጋጥም ስነ-ምግባራዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚከተሉትን ሂደቶች እንድናልፍ ይመከራል፡

- በተቻለ መጠን ውሳኔ ልሰጥበት ባልነው ጉዳይ ላይ በቂ መረጃ አግኝቻለሁ?
- በዚህ ጉዳይ ላይ ግብአት ሊሰጡኝ የሚችሉ አካላት በሙሉ ተሳትፈዋል?
- በውሳኔው በጣም ተጠቂ ወይም ተጎጂ ሊሆኑ የሚችሉ አካላትን በሙሉ ከግምት ውስጥ አስገብቻለሁ?
- እኔ ውሳኔ በሚሰጠው ሰው ቦታ ብሆን አሁን የሚሰጠው ውሳኔ ፍትሃዊ ነው ብዬ ልወስድ እችላለሁ?
- እንዲህ አይነት ውሳኔ በሁሉም ስፍራ በሁሉም ቦታ ቢሰጥ ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ?
- ይህ ውሳኔዬ በጓደኞቼ ፊት ወይም በአደባባይ ይፋ ቢሆን ምንም የምሸማቀቅበት ነገር አይኖርም?

**መልመጃ 2.12 መወያያ ጥያቄ**

**ኬዝ 2**

እርስዎ በንግድ ሥራ ለተሰማሩ ደንበኞች የመጨረሻውን የታክስ የክሊራንስ ማረጋገጫ የሚሰጡ ነዎት፣ ዛሬ ክሊራንስ የሚፈልጉ በርካታ ደንበኞች ወደ እርሶ እየጎረፉ፣ ከዚያ መካከል ዘግይቶ የመጣው የርሶ ወንድም ነው፣ ዘግይቶ በመምጣቱ ደግሞ የክሊራንስ ማረጋገጫው ዛሬ የሚደርሰው አይመስልም፣ በዚህ ምክንያት በርካታ ገንዘብ ሊያገኝበት የሚችለው ጨረታ ሊያልፈው ነው። የግብር ክሊራንሱ የሚያስገባውን ጨረታ ሙሉ ያደርገዋል፣ የተወዳደረው ጨረታ የመዝጊያ ቀንም ዛሬ ነው። ይህን ጉዳይ በስልክ አጫወተዎት፤

1. እርስዎ ቢሆኑ ምን ያደርጋሉ?
2. በዚህ ኬዝ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በመልካም አስተዳደር ላይ የሚያሳርፈው ተጽእኖ እንዴት ይገለጻል?

**መልመጃ 2.13 መወያያ ጥያቄ** **ኬዝ 3**

እርስዎ የአንድ መስሪያ ቤት ስራ አስኪያጅ ነዎት፣ የመስሪያ ቤቱ ምክትል ስራ አስኪያጅ መኪናው ስለተበላሸበት ለርሶ የተመደበችልዎትን መኪና ይዞ ለስራ ወጥቷል፣ አሁን በስራ ቦታ ያለው ሶስት ሰዎች ወደ ሚካፈሉበት አውደ ጥናት ለመውሰድ የተዘጋጀ መኪና ብቻ ነው ያለው። ልጆችዎ ደግሞ ሰርቪስ አምልጧቸዋል፤ ዛሬ ደግሞ የፈተና ቀናቸው ነው፤ እናም መኪና እንዲልኩላቸው ስልክ ደውለውሎታል።

1. እርስዎ ምን ይወስናሉ?
2. የዚህ ኬዝ ውሳኔ በመልካም አስተዳደር ላይ የሚፈጥረው ተጽእኖ ምንድ ነው?
3. እንዲህ አይነት ፈታኝ ሁኔታ ካጋጠማችሁ ለተሳታፊዎች ሁኔታውን እና የሰጣችሁትን ውሳኔ ለተሳታፊዎች አካፍሉ?

## *የክፍል አራት ማጠቃለያ*

***አንዳንድ ጊዜ በተቋም ውስጥ በስነ-ምግባር ደንብ ወይም በመስሪያ ቤቱ አስተዳደር ደንብ የማይፈቱ ሥነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎች ይገጥሙናል። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ጉዳዮች ከሁለት ጥሩ መካከል የተሸለ ጥሩን እንድንመርጥ አንዳድንድ ጊዜ ደግሞ ከሁለት መልካም ማይመስሉ ብዙ ጉዳት የማያደርሰውን እንድንመርጥ የምንገደድበት ሁኔታ ሊያጋጥመን ይችላል። ለእነደዚህ ዓይነቱ ፈታኝ ሁኔታዎች የምንሰጣቸው መልሶች በመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ላይ የራሳቸውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ያሳርፋሉ። በመሆኑም ውሳኔዎችን የተለያዩ አቅጣጫዎች እያዩ ሚዛናዊ ውሳኔ መስጠት ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ትልቅ ትርጉም አለው።***

## ዋቢ መጽሃፍት


- African Development Bank (March 2009), FDRE of Ethiopia, Country Governance Profile, OSGE,
- African Development Bank Group (1999), Bank Group Policy on Good Governance,
- Bowman, James S. (2001). From Codes of Conduct to Codes of Ethics: The ASPA Case. In Handbook of Administrative Ethics. Ed. Terry L. Cooper. New York, Basel: Marcel Dekker, Inc.
- B.C.Smith (2001), Globalization and the State, Good Governance and Development
- Bruce, Willa (Ed.) (2001). Classics of Administrative Ethics. Colorado, Oxford: Westview Press.
- Caiden, Gerald E. (1983). Public Service Ethics: What should be done? In Ethics in the Public Service: Comparative Perspectives. Eds. Kenneth Kernaghan & O.P. Dwivedi. Brussels: International Institute of Administrative Sciences.
- Cheema, G. Shabbir (2004) Building Democratic Institutions: governance reform in developing countries, Bloomfield: Kumarian press.
- Dhameja, Alka, 2003, "Role of Ethics in Public Administration" in Ramesh K Arora, and Tanjul, Saxena (Eds.), Ethics and Accountability in Government and Business: Aalekh, Jaipur.
- Economic Commission for Africa (2004): Governance Profile for Ethiopia,
- World Bank (May 2007), EthiopiaEnhancing Human Development Outcomes Through Decentralized Service Delivery
- Ed. Hugh LaFollette (2000), Ethical Theory, Massachusetts, Oxford: Blackwell Publishers.
- Frimpong, K and Jacques, G. (1998) Corruption, Democracy, and Good Governance in Africa: essays on accountability and ethical behavior, Dublin: Institute of PA.
- Getachew H. and Common R., ( 2006). Civil Service Reform in Ethiopia: Success in twoministries at http://www2.hull.ac.uk/hubs/pdf/memorandum59.pdf

- Kettle, Donald F (1996) Civil Service Reform: building a government that works, Washington, D.C.: Brookings Institution Press.
- I.M.F (2002) The I.M.F approach to promoting Good Governance and combating corruption.
- IMF (1997). Good governance: the IMF's role. Washington, USA.
- Institute of Educational Research (2002), Corruption Survey in Ethiopia, Addis Ababa,
- Michael Johnston, "Good governance: Rule of law, Transparency and accountability," Colgate University New York. (2004). Available at: http://unpan1.un.org/intradoc/groups/public/documents/un/unpan010193. pdf
- Plant, Jeremy F. (2001). Codes of Ethics. In Handbook of Administrative Ethics. Ed. Terry L. Cooper. New York, Basel: Marcel Dekker, Inc.
- Semahegn G. (2007). Impediments of good governance in Ethiopia
- Smith B,C, (2007) Good Governance and development, CPI Antony Rowe Great Britain.
- Rohr, John A, 1978. Ethics for Bureaucrats: An Essay on Law and Value, Marcel Dekker, New York.
- Rose-Ackerman, Susan. 1999.Corruption and Government. New York: CambridgeUniversity Press.
- The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission,The FEAC Annual Performance Report, 2015 Budget Year, Addis Ababa.
- United Nations (2000). Good Governance. Available on the Internet: http://unhchr.ch.